# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ | 81ኛ ዓመት ቁጥር 332 ነሐሴ 2 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# «የኢትዮጵያ ጠላቶች ከልማት ይልቅ የጸጥታ ችግር አጀንዳ እንዲሆን አቅደው እየሠሩ ነው»

-ኡስታዝ ካሚል ሽምሱ
የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል



**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ጠላቶች ከልማት ይልቅ የጸጥታ ችግር አጀንዳ እንዲሆን አቅደው እየሠሩ ነው ሲሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ኡስታዝ ካሚል ሸምሱ ተናገሩ፡፡

ኡስታዝ ካሚል በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ እያደገችና እየጠነከረች በሄደች ቁጥር ጠላቶቿም እየበዙ መምጣታቸው አይቀሬ ነው። እነዚህ ጠላቶች ደግሞ በአካባቢው የፀጥታ ችግሮችን በመፍጠር ሕዝብ ስለደህንነቱ ብቻ እንዲጨነቅ የማድረግ ፍላጎት አላቸው።

በብሔር፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ልዩነትና በድንበር ሽፋን በአገሪቱ የሚከሰቱ የጸጥታ ችግሮች ሲጠቃለሉ ዓላማቸው በአገሪቱ ሁሌ የሰላም

«የኢትዮጵያ ጠላቶች... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






አቶ ገመቺስ መላኩ

## የገበያ መዳረሻዎችን የማስፋት አማራጭ መወሰዱ የወጪ ንግድ ውጤታማ እንዲሆን ማስቻሉ ተገለጸ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ከአሜሪካ የአፍሪካ ከቀረጥ ነፃ የንግድ ቀጠና ተጠቃሚነት የኢትዮጵያን መከልከልና ሌሎች የገበያ ተፅዕኖዎችን ለመቋቋም በተደረገ ጥረት የወጪ ንግድ የገበያ መዳረሻዎችን የማስፋት አካሄድ ከኤክስፖርት የሚገኘውን ገቢ ውጤታማ ማድረግ መቻሉን ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የውጭ ንግድ መሪ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ገመቺስ መላኩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በጀት ዓመቱ ኢትዮጵያ ከአሜሪካ የአፍሪካ ከቀረጥ ነፃ የንግድ ቀጣና ተጠቃሚነት መከልከልና ሌሎች የገበያ ተፅዕኖዎች ስር የነበረችበት ጊዜ

የገበያ መዳረሻዎችን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የትምህርት ቤቱ ማርሽ ባንድ ከ43 ዓመታት በኋላ ሥራ ጀመረ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሙዚቃና ማርሽ ባንድ ከ43 አመታት በኋላ ሥራ መጀመሩን የዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የኪነ ጥበብ ክበብ ኃላፊ አቶ ፍቃዱ እሸቱ ገለጹ።

እንደ አቶ ፍቃዱ ገለፃ፣ የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት በኢትዮጵያ የማርሽ ባንድ ከነበራቸው አራት ትምህርት ቤቶች መካከል አንዱ ነው። በትምህርት ቤቱ ከ43 ዓመታት በፊት ተቋርጦ የነበረው የትምህርት ቤቱ የተማሪዎች የሙዚቃና ማርሽ ባንድ ዘንድሮ ትንሳኤውን ማግኘት ችሏል ብለዋል።

ከ43 ዓመታት በፊት ከአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ለውጥ በኋላ በነበረው የፖለቲካ ሁኔታ ምክንያት መቋረጡን ያስታወሱት የትምህርት ቤቱ የኪነ ጥበብ ክበብ ኃላፊ መምህር ፍቃዱ፣ የሙዚቃ ሙያተኛ እና መምህር የሆኑት ሌተናል ኮሎኔል ሲሳይ ፍቃዱ ለትምህርት ቤቱ የሙዚቃና ማርሽ ባንድ ትንሳኤ ምክንያት ሆነዋል ብለዋል።

ሙያተኛው የግል የሙዚቃ መሣሪያቸውን ተማሪዎች በነፃ እንዲጠቀሙባቸው በማድረግ እና ስልጠና በመስጠት የተማሪዎች ማርሽ ባንድ እንዲጠናከር ሰፊ ጥረት በማድረግ ላይ እንደሚገኙም ተናግረዋል፡፡

በሙዚቃና በማርሽ ባንድ መሣሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኙት መሣሪያዎቹ ረጅም ጊዜ ሲያገለገሉ የቆዩ በመሆናቸው አሁን ላይ እነዚህን መሣሪያዎች እንደገና በማደስ እየተገለገሉበት እንደሆነም ገልጸዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ከ43 ዓመታት በፊት የሙዚቃ ትምህርትን በማጠናከር ተማሪዎች በፍላጎታቸው በትምርት ቤት ውስጥ የተቋቋሙ የተማሪ የሙዚቃ እና ማርሽ ባንዶችን እንዲቀላቀሉ በማድረግ በዘርፉ ለአገር ፈርጥ የሆኑ ታዋቂ ሙዚቀኞችን ማፍራት መቻሉን ተናግረዋል።

ከዚህ ትምህርት ቤት የወጡ ታዋቂ የሙዚቃ ባለሙያዎችና የኪነጥበብ ሰዎች እንዳሉ የሚናገሩት መምህር ፍቃዱ፣ አሁን ላይ የማርሽ ባንድ ትምህርት ቤቱ 50 ተማሪዎችን በማሰልጠን ሥራ መጀመሩን አስታውቀዋል። ተማሪዎችን በፍላጎታቸው መሠረት በመመልመል በነን ስልጠና በመስጠት ላይ መሆናቸውንም አሳውቀዋል።



መምህር ፍቃዱ እሸቱ የዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የኪነ ጥበብ ክበብ ኃላፊ

መምህር ፍቃዱ አክለውም ተማሪዎች ባገኙት ስልጠና መሠረት በተማሪዎች ማርሽ ባንድ መቋቋም ላይ የድርሻቸውን እየተወጡ ይገኛሉ።በሌሎች ትምህርት ቤቶች ላይም እንዲስፋፋ በትኩረት ሊሠራበት እንደሚገባም አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያነጋገራቸው የማርሽ ባንድ አባል የሆኑ ተማሪዎችም በስልጠናው ደስተኛ መሆናቸውን በመግለጽ ለማርሽ ባንዱ ድጋፍ ላደረጉ አካላት ምስጋና አቅርበዋል፡፡

ይህ የሙዚቃና ማርሽ ባንድ ከ43 ዓመታት በኋላ ሥራ መጀመሩ ከትምህርታቸው ጎን ለጎን ክህሎታቸውን የሚያዳብሩበት ሁኔታን የሚፈጥር ነው ሲሉም ተማሪዎቹ ተናግረዋል።



## ‹‹በውጭ የሚገኝ የትግራይ ተወላጅ ሕወሓትን ከመደገፍ ይልቅ ችግር ውስጥ ያለውን ሕዝብ መታደግ አለበት››

አቶ ናትናኤል አስመላሽ
አክቲቪስት

**መሰረት ገ/ዮሐንስ**

አዲስ አበባ፡- በውጭ አገር የሚገኝ የትግራይ ተወላጅ የተሻለ ገንዘብ የማግኘት ዕድል ስላለው በትክክል ለትግራይ ሕዝብ የሚያስብ ከሆነ ሕወሓትን ከመደገፍ ይልቅ ችግር ውስጥ የገባውን የትግራይ ሕዝብ መታደግ እንዳለበት አቶ ናትናኤል አስመላሽ ገለፁ፡፡

አክቲቪስቱ አቶ ናትናኤል አስመላሽ ከወጋሕታ ጋዜጣ በነበረው ቆይታ እንደገለፀው፤ የሚያሳዝነው ነገር የትግራይ ሕዝብ በረሀብ ውስጥ እያለ፣ በመድኃኒት እጥረት እየተሳቃየ የሕወሓት ደጋፊዎች ግን ሰባ አምስት

‹‹በውጭ የሚገኝ የትግራይ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# የአማራ ፓይፕ ፋብሪካ በኤሌክትሪክ መቆራረጥና በዶላር እጥረት በሙሉ አቅሙ እያመረተ አለመሆኑን ገለጸ

**ሙሳ ሙሐመድ**


አቶ ወርቁ ባዬ


የአማራ ፓይፕ ፋብሪካ የፓይፕ ምርት

ባህርዳር፡- የአማራ ፓይፕ ፋብሪካ በኤሌክትሪክ መቆራረጥና በዶላር እጥረት ምክንያት በሙሉ አቅሙ ማምረት እንዳልቻለ አስታወቀ።

የፋብሪካው ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ወርቁ ባዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ ፋብሪካው ጥሬ ዕቃዎችን ከውጭ ለማስገባት የዶላር እጥረት ሳነካ ሆኖበታል።የኤሌክትሪክ መቆራረጥም ፋብሪካው ባሉት ውስን ጥሬ ዕቃዎች በሙሉ አቅሙ ልዩ ልዩ ቱቦዎች(ፓይፕ) እና ለአበባና ፍራፍሬ አምራቾች የሚያገለግሉ የግሪን ሃውስ ፊልሞች ማምረት እንዳይችል አድርጎታል፡፡

ፋብሪካው ጥራት ያላቸው ለመጠጥ ውሃና ለመስኖ ፕሮጀክቶች የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ ቱቦዎችን (ፓይፕ) ምርቶችንና ለአበባና ፍራፍሬ አምራቾች የሚያገለግሉ የግሪን ሃውስ ፊልሞች እያመረተ ከአገር ፍጆታ አልፎ ለምሥራቅ አፍሪካ አገራት ተደራሽ ለማድረግ እየሠራ እንደሚገኝ ጠቁመው፤ የዶላር እጥረትና በሥራ ሰዓት የሚከሰተው የመብራት መቆራረጥ ፋብሪካው በሙሉ አቅም እንዳያመርት አድርገውታል።በእነዚህ ችግሮች ሳቢያም ፋብሪካው ምርቱን ለምሥራቅ አፍሪካ አገራት ለማዳረስ የሚያደርገው ጥረት እየተደናቀፈ ነው ብለዋል።

በዶላር አቅርቦት እጥረት ጫና ውስጥ ቢሆንም የሚገቡት ውስን ጥሬ ዕቃዎች ወደ ምርትነት ለመቀየር በሚደረገው ሂደትም የሚከሰተው የኤሌክትሪክ መቆራረጥም ፋብሪካውን ለጥሬ ዕቃና ምርት ብክነት እየዳረገው ነው ያሉት ሥራ አስኪያጁ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ችግሩን በቅርቡ ለመቅረፍ ከኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር እየተነጋገረ መሆኑን ጠቁመዋል።የዶላር አቅርቦት ችግርም በመንግሥት በኩል እንዲፈታ እንፈልጋለን ብለዋል፡፡

ፋብሪካው የፕላስቲክ ቱቦዎችንና ለአበባና ፍራፍሬ አምራቾች የሚያገለግሉ የግሪን ሃውስ ፊልሞችን ማምረት የሚችሉ ዘመናዊ የማምረቻ ማሽኖች አሉት ያሉት አቶ ወርቁ፣ እነዚህ ዘመናዊ ማሽኖች ከውጭ ይገቡ የነበሩትን የፕላስቲክ ቱቦዎችንና የግሪን ሀውስ ላስቲኮችን በአገር ውስጥ ምርት መተካት በመቻሉ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬን ማደን እንደተቻለ ገልጸዋል።

ፋብሪካው ለክልሎችና ለፌዴራል የመስኖና የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ምርቶቹን እያቀረበ እንደሚገኝ አመልክተው፤ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ጥሩ የሚባል የገበያ ትስስር እንዳለውም አውስተዋል፡፡

የ2014ዓ.ም ፋብሪካው ለአፋር፣ ለጋምቤላ፣ ለኦሮሚያ፣ ለቤኒሻንጉል ጉሙዝና ሶማሌ ክልሎችና ለአዲስ አበባ አስተዳደር ምርቶቹን በጥራት አምርቶ ማቅረብ መቻሉን ተናግረዋል፡፡

ፋብሪካው የሚያመርታቸው ምርቶች የጥራት ልክንና ምን ዓይነት ምርቶችን እንደሚያመርት በሚዲያ የማስተዋወቅ ሥራ እንደሚቀረው የጠቆሙት አቶ ወርቁ፣ በቀጣይ የሚያመርታቸውን ምርቶችና የጥራት ልኩን ለማስተዋወቅ ከሚዲያዎች ጋር እንደሚሠራ ተናግረዋል፡፡

የአማራ ፕይፕ ፋብሪካ ምርቶቹን ከአገር አልፎ ለአጎራባች አገሮች ለመላክ ዕቅድ መያዙን የተናገሩት አቶ ወርቁ፣ የዶላር እጥረቱ በቅርብ ጊዜ ከተቀረፈም ከሶማሊላንድ ጋር በደረሱት ስምምነት መሠረት ልዩ ልዩ የፕላስቲክ ቱቦዎችንና ለአበባና ፍራፍሬ አምራቾች የሚያገለግሉ የግሪን ሃውስ ፊልሞችን መላክ እንደሚችሉ አመልክተዋል፡፡

እንደ አቶ ወርቁ ገለጻ፣ ፋብሪካው የጥሬ ዕቃ የሚያስመጣው ከዱባይ፣ ከኮሪያ፣ ከእሥራኤልና ከሕንድ ነው።የዱባይ አቡዲያቢው ቡርጂ ፋብሪካ ሥራ አስኪያጅ በአካል መጥቶ በመጎብኘት የጥሬ ዕቃ እስከ ወደብ ድረስ በነፃ ትራንስፖርት ለማቅረብ ተስማምቷል፡፡

ፋብሪካው በ2003ዓ.ም ሲቋቋም 70 በመቶ በአማራ ክልል መንግሥትና 30 በመቶ በጎልደን ትሬድ በሚባል የውጭ ድርጅት የባለቤትነት ድርሻ ሲሆን በአሁኑ ወቅት 84 በመቶ ድርሻ የመንግሥት መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ፋብሪካው ሥራ ሲጀምር በአምስት የውጭና 40 የአገር ውስጥ ሠራተኞች እንደነበሩት ያወሱት አቶ ወርቁ፣ በአሁኑ ጊዜ ከ500 በላይ ቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኞች እንዳሉት ታውቋል፡፡





# ባለሥልጣኑ በ1 ሺህ 360 ሕንፃዎች የመኪና ማቆሚያ ቦታ አጠቃቀም ኦዲት ማድረጉን ገለፀ

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ በበጀት ዓመቱ በ1 ሺህ 360 ሕንፃዎች ላይ የሕንፃ ውስጥ የመኪና ማቆሚያ ቦታ አጠቃቀም ኦዲት መደረጉን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አስታወቀ። ከተፈቀደላቸው ውጭ የመኪና ማቆሚያን ለሌላ አገልግሎት ያዋሉ 23 ሕንፃዎች ላይ እርምጃ ተወስዶባቸዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ አረጋዊ ማሩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ እንደገለፁት፣ በመዲናዋ በበጀት ዓመቱ በተደረገ የሕንፃዎች የፓርኪንግ አጠቃቀም ፍተሻ 58 ሕንፃዎች የመኪና ማቆሚያን በከፊል ለሌላ አገልግሎት ያዋሉ ናቸው።

ከእነዚህም 35 የሚሆኑ ሕንፃዎች በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ማስተካከያ ማድረግ ቢችሉም ቀሪ 23 ሕንፃዎች በጊዜ ገደቡ ማስተካከል ባለመቻላቸው እርምጃ እንዲወሰድባቸው እና የንግድ ፈቃዳቸው እንዲታገድ ለሚመለከተው ቢሮ መላኩን አስታውቀዋል፡፡

በክፍለ ከተሞች ደረጃም ከ1 ሺህ 100 በላይ ሕንፃዎች የመኪና ማቆሚያ ቦታ አጠቃቀም ኦዲት እንደተደረገ ዳይሬክተሩ ተናግረዋል፡፡

በ2015 በጀት ዓመትም በማዕከልና በክፍለ ከተማ ከ2 ሺህ 600 በላይ ሕንፃዎች የሕንፃ ውስጥ የመኪና ማቆሚያ ቦታ አጠቃቀም ኦዲት ለማድረግ ዕቅድ የተያዘ መሆኑን አቶ አረጋዊ ማሩ አመላክተዋል፡፡


በሌላ በኩል በ2014 በጀት ዓመት ብቁና ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመፍጠር በተሠሩ ሥራዎች አበረታች አፈጻጸሞች መመዝገባቸውንም ገልጸዋል።

ባለሥልጣኑ በ2014 በጀት ዓመት በመዲናዋ ብቁና ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመፍጠር ለ4 ሺህ 639 የሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች እና ባለሙያዎች እንዲሁም ለ44 የኮንስትራክሽን መሣሪያ አከራዮች የምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት መሰጠቱንም ጠቁመዋል፡፡

የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች በተሰጣቸው ብቃት ማረጋገጫ መሠረት መሥራታቸውን ክትትል ከማድረግ ጋር ተያይዞ በ325 የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በ375 ላይ ክትትል ማድረግ እንደተቻለም አቶ አረጋዊ ጠቁመዋል፡፡

በ2015 በጀት ዓመትም ከዚህ የተሻለ አፈጻጸም እንዲመዘገብ ቅንጅታዊ አሠራር መዳበር እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

ዜና



# «እያንዳንዱ ዜጋ በትብብርና በአንድነት በመሥራት ለልጆቹ ምቹ ኢትዮጵያን መፍጠር ይጠበቅበታል»

## የቀድሞው የኢትዮጵያ የእግር ኳስ ቡድን አሰልጣኝ ሰውነት ቢሻው

ጌትነት ምህረቴ

አዲስ አበባ፡- እያንዳንዱ ዜጋ በትብብርና በአንድነት በመሥራት በአትሌቲክሱ የተገኘውን ድል በልማቱም በመድገም ለልጆቹ ምቹ ኢትዮጵያን መፍጠር ይጠበቅበታል ሲሉ የቀድሞው የኢትዮጵያ የእግር ኳስ ቡድን አሰልጣኝ ሰውነት ቢሻው ገለጹ።

አሰልጣኝ ሰውነት ቢሻው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በስፖርቱ የተመዘገባውን ድል በኢኮኖሚ ልማቱም ለመድገም ሁሉም ኢትዮጵያዊ በያለበት በኅብረትና በቅንጅት ጠንካራና የተናበበ ሥራ መሥራት ይኖርበታል። ቅራኔዎችና አለመግባባቶች ቢኖሩም እንኳን በሰለጠነ መንገድ በውይይት በመፍታት በትብብርና በአንድነት በመሥራት ለልጆቹ ምቹ ኢትዮጵያን መፍጠር ይጠበቅበታል።

እንደ አትሌትክሱ ሁሉ በሁሉም መስክ ድል ማስመዝገብ ይቻላል የሚሉት አሰልጣኝ ሰውነት፤ ድል የሚገኘው አንደኛ ጠንክሮ በመሥራት፤ ሁለተኛ ትብብርንና አንድነትን በማጠናከር በስፖርቱ የተገኘውን አንጸባራቂ ድል በሰላምና በልማት ሥራዎችም ማስመዝገብ እንደሚቻል ተናግረዋል።

«ስፖርት ሁሉንም ሕዝብ የሚያገናኝ ነው። የሚጋጨውና የሚነታረከው አገሩ ሲያሸንፍ ይደሰታል። ከዚህ አኳያ ስፖርት የአንድነት ቋጠሮን ማጥበቅ የሚያስችል ትልቅ መሣሪያ ነው» ያሉት አሰልጣኝ ሰውነት፤ የአትሌትክሱ ድል የአንድነትና ጠንክሮ የመሥራት ውጤት ማሳያ መሆኑን በመገንዘብ ዘላቂ ሰላምና ልማት ለማምጣትም እጅ ለእጅ ተያይዘን ጠንክረን መሥራት ይኖርብናል ብለዋል።

እንደ አሰልጣኝ ሰውነት ገለጻ፤ የሰው ልጅ ለአጭር ጊዜ የሚኖርበትን ዓለምም ሆነ አገር አጥፍቶ መሄድ የለበትም፤ ይልቁንስ ለተተኪው ትውልድ አልምቶና ምቹ አድርጎ መሄድ ይኖርበታል፤ ይህን ለማድረግ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በትብብርና በአንድነት በመሥራት ለልጆቹ ምቹ አገር መፍጠር ይጠበቅበታል።

ቅራኔና አለመግባባቶች ቢኖሩም በውይይት በመፍታት ለትውልዱ ምቹ አገር መፍጠር እንደሚገባ ገልጸው፤ ሁሉም በኅብረትና በአንድነት የአገሩን ኢኮኖሚ ለማሳደግና ልማት ለማስፋፋት ጠንክሮ መሥራት ከቻለ በስፖርቱ የተመዘገባውን ድልና ደስታም በኑሮአችንና በአገራችን ላይ ማምጣት ይቻላል ብለዋል።

# በወንጀል የተገኘ ከ88 ሚሊዮን ብር በላይ ገንዘብ እና 10ሺህ ካሬሜትር ይዞታ መወረሱን ሚኒስቴሩ ገለጸ

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- በ2014 ዓ.ም በወንጀል የተገኘ ከ88 ሚሊዮን ብር በላይ ጥሬ ገንዘብ እና 10 ሺህ ካሬ ሜትር ይዞታ በፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲወረስ መደረጉን ፍትህ ሚኒስቴር ገለጸ።

በሚኒስቴሩ ፕሬስ ሴክሬታሪ ዳይሬክተር አቶ አወል ሡልጣን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በወንጀል የተገኘ 88 ሚሊዮን ብር እና 10 ሺህ ካሬ ሜትር ይዞታ በፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲወረስ ተደርጓል።

በተጨማሪም ሚኒስቴሩ አንድ ተሽከርካሪ እና የዋጋ ግምቱ ብር አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ብር የተገመተ ቤት ለመንግሥት ገቢ ማድረጉንም አመልክተዋል።

እግድን አስመልክቶም ከወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዘ በበጀት ዓመቱ ውስጥ 10 ድርጅቶች፣ 702 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ገንዘብ እና 745 ሚሊዮን ሼር የተገዛበት የገንዘብ መጠን እንዲታገድ ማድረጉን ተናግረዋል።

155 ቤቶች፣ 364 ልዩ ልዩ ተሽከርካሪዎች፣ 617 ማሽነሪዎች እና 41 ሺህ 194 ካሬ መሬትም በተመሳሳይ መታገዳቸውን ጠቁመዋል።

በፍርድ ቤት ከሚሰጡ የገንዘብና የእስራት ቅጣት ማስፈፀም ጋር ተያይዞም በወንጀል ጉዳይ የገንዘብ ቅጣት ከተሰጠባቸው ውስጥ ሰባት ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ገቢ መደረጉን ነው አቶ አወል የተናገሩት፡፡

በበጀት ዓመቱ አራት ሕጎችን የማርቀቅ ሥራ ለመሥራት ዕቅድ ተይዞ 12 ሕጎችን የማርቀቅ ሥራ መሠራቱን እና ተጀምረው ያልተጠናቀቁ ሦስት ረቂቅ ሕጎችን የማጠናቀቅ ሥራ መሠራቱንም አመልክተዋል።

ከ1934 ጀምሮ የሚገኙ ሕጎችን ማሰባሰብና የማጠቃለል ሥራ መሠራቱን የተናገሩት አቶ አወል፤ የህትመት ሂደቱም የ10ሩ ቅጾች ህትመት ተጠናቆ ስርጭት መጀመሩንና 11ኛው ሕትመት ላይ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።



አቶ አወል ሡልጣን

ተደራሽነትን ከማሳደግ አንፃር ዘመናዊ አሠራርን በመከተል ከ1934 እስከ 2014 ዓ.ም ድረስ ያሉ የተጠቃለሉ ሕጎችን በቴክኖሎጂ የመጫን ሥራ በማከናወን ለተገልጋዮች መመሪያዎችንና ደንቦችን ተደራሽ ማድረግ መቻሉንም ተናግረዋል።

ከወንጀል መዛግብት ጋር ተያይዞ የወንጀል ተጠርጣሪዎችን ማፈላለጊያ ገፅ በመፍጠር ጥቆማ መስጠት የሚቻልበትን ገፅ ልማት በማጠናቀቅ ለሥራ ዝግጁ መሆኑንም አመልክተዋል።

የተደራጁና ድንበር ተሻጋሪ፣ የኢኮኖሚ እና የሙስና ወንጀሎች የወንጀል ምርመራ መዛግብትን የመወሰን አቅም አፈጻፀም በተመለከተም ለዐቃቤ ሕግ ከደረሱት አራት ሺህ 582 የምርመራ መዝገቦች መካከል አራት ሺህ 242 የምርመራ መዝገቦች ላይ የተለያዩ ውሳኔዎች እንደተሰጠባቸው ጠቁመዋል።ቀሪዎቹ 340 መዝገቦች በዐቃቤ ሕግ እጅ እንደሚገኙም ተናግረዋል።

አጠቃላይ በሦስቱም የወንጀል ዓይነቶች በክርክር ላይ በነበሩ ሦስት ሺህ 299 ተከሳሾች መካከል ሁለት ሺህ 615 በሚሆኑት ተከሳሾች ላይ ዐቃቤ ሕግ ጥፋተኛ እንዲባሉ ያደረገ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ 684 ተከሳሾች በነፃ እንዲሰናበቱ የተደረጉባቸው መሆኑም ተገልጧል።

በምስክር አለመቅረብ ምክንያት 135 መዛግብት፣ በተከሳሾች አለመቅረብ ምክንያት ደግሞ 363 መዝገቦች የተቋረጡ መሆናቸውንም አመልክተዋል።

# የመኸር ግብርና ዝግጅት - በምርታማው የባሌ ዞን

ጌትነት ተስፋማርያም



መሬቱ የሰጡትን ይቀበላል፤ የዝናብ ሁኔታውም ለግብርናው ሥራ ምቹ ነው። እኛም የበልግ ክንውናችንን አገባደን የመኸር ወቅት እርሻችንን በዘር ለመሸፈን በቂ ዝግጅት አድርገናል የሚሉት በኦሮሚያ ክልል የባሌ ዞን ሲናና ወረዳ አርሶአደሮች ናቸው፡፡

የሲናና ወረዳ አርሶአደር የሆኑት አቶ አህመድ ቃዱ እንደሚሉት፣ በዘንድሮው ዓመት የመኸር ወቅት አንድ ሄክታር መሬት በዘር በመሸፈን የተሻለ ምርት ለማግኘት አቅደዋል፤ ለዚህም የስንዴና የገብስ ማሳቸውን ሦስት አራት ጊዜ ደጋግመው አርሰዋል፡፡

የግብርና ባለሙያዎች እገዛ ከዓመት ዓመት ለምርት መሻሻል አስተዋፅኦ ማድረጉን የሚናገሩት አርሶአደሩ፤ እገዛው ጥሩ ቢሆንም በአካባቢያቸው ያለውን የማዳበሪያ ግብዓት ዕጥረት መፍታት ከተቻለ ደግሞ ሥራቸው የበለጠ ያማረ እንደሚሆን ይናገራሉ።

የዘር አቅርቦቱ በወቅቱ የደረሰላቸውን ያህል የማዳበሪያ አቅርቦቱን በሚፈለገው ልክ ስላላገኙ ስጋት ቢያድርባቸውም፤ ግብዓቱን በቅርብ ቀናት እንደሚያገኙ ከአካባቢው የግብርና ባለሙያዎች ስለተነገራቸው የእርሻ ሥራቸው እንደማይስተጓጎል ተስፋ አድርገዋል።

በቀጣይ ሳምንት ማዳበሪያውን እንዳገኙ ማሳቸውን በዘር ለመሸፈን ውጥን የያዙት አርሶአደር አህመድ፤ ካለው ምቹ የአየር ንብረትና የግብርና ሥራ ዝግጅት አንጻር የተሻለ የስንዴና ገብስ ምርት በአካባቢው እንደሚገኝ ግምታቸውን ያስቀምጣሉ።

ኑሮአቸውን በግብርና ሥራ የሚመሩት ይሁኔ ዋቆና ሐጂ ሙክታር ተማም በበኩላቸው፤ እያንዳንዳቸው አራት አራት ሔክታር የእርሻ መሬት እንዳላቸው ይናገራሉ።

መሬታቸውን በመስኖ ስንዴ ሲያለሙበት እንደነበር በመግለጽ አሁን ላይ ለመኸር ወቅት እርሻ እያዘጋጁ መሆኑን ነው የሚጠቁሙት አርሶአደሮቹ፤ ለምርት ዘመኑም ከ60 በላይ አርሶአደሮች በክላስተር ግብርና አሠራር አንድ ላይ መጣመራቸውን ያስረዳሉ።

«የባሌ ዞን በስንዴ ምርትና በቢራ ገብስ እንዲሁም በተለያዩ ሰብሎች ምርት ይታወቃል። እኛም በዘመናዊ መሣሪያዎች እገዛ የግብርና ሥራ ዝግጅታችንን እያከናወንን ይገኛል። በክላስተር የምናለማውን እርሻ በትራክተር አሳርሰን ድጋሚ በበሬ እርሻ እያለሰለስን ነው» ይላሉ አርሶአደሮቹ።

አርሶአደሮቹ «በቀጣይ ቀናት አስፈላጊውን ግብዓት ተጠቅመን እንዘራለን፤ ጥቂት የሚያሳስበን ግን በአካባቢው ያለው የስንዴ ዋግ በሽታ ነው» ይላሉ፤ ለችግሩም ዘላቂ መፍትሄ የሚሰጥ መድኃኒት ያስፈልገናል ሲሉ ከወዲሁ ኬሚካል ሊቀርብ እንደሚገባ አሳስበዋል።

በኦሮሚያ ክልል የባሌ ዞን ግብርናና ተፈጥሮ ኃብት ቢሮ ኃላፊ አቶ አሊዩ መሀመድ በበኩላቸው፤ እንደአገር በምግብ እራስን ለመቻል በሚደረገው ጥረት የባሌ ዞን ግብርና ትልቅ አስተዋጽኦ አለው ይላሉ።

በዞኑ ቆላማ አካባቢዎች ላይ በቆሎ፣ ሰሊጥና የተለያዩ የቅባት እህሎች፣ ጤፍ፣ ማሾና ሌሎችም ይመረታሉ። ደጋማው አካባቢ ደግሞ ስንዴና የቢራ ገብስና ቡና በብዛት እንደሚመረቱ ነው የተናገሩት።

አሁን ላይ በቆላማ አካባቢ ያለውን ምርት በኮምባይነር እገዛ እያጨድን በደጋማው አካባቢ ደግሞ በትራክተር እያረስን በመዝራት ላይ ነን። የዘር ክንውኑም እስከ መስከረም ወር ድረስ ይቀጥላል ሲሉ ያስረዳሉ።

በአርሶአደሮች ጥያቄ መሠረት ለምርቶች የሚሆን አስፈላጊው ዝግጅት ሲከናወን ቆይቷል ያሉት አቶ አሊዩ፤ የዘር አቅርቦት፣ የበሽታ መከላከያ ኬሚካሎችና የማዳበሪያ አቅርቦት እየተዳረሰ ይገኛል፤ በቀጣይ ቀናትም በስፋት እንደሚቀርብ ይገልጻሉ።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ ለትራንስፖርት አስቸጋሪ በሆኑና ራቅ ባሉ ቀበሌዎች ላይ የማዳበሪያና አስፈላጊው የግብዓት እጥረት ሲከሰት በአቅራቢያቸው ከሚገኝ የህብረት ሥራ ማህበራት ጋር በመነጋገር በወቅት እንዲደርስ ጥረት ይደረጋል። 290 ሺህ ኩንታል በላይ ማዳበሪያም ለአርሶአደሮች እየተሰራጨ ይገኛል።

ከዚህ ባለፈ የተፈጥሮ ማዳበሪያዎችን አርሶአደሩ አዘጋጅቶ እንዲጠቀም የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ሲካሄዱ ቆይተዋል። በተጨማሪም በክላስተር ግብርና አርሶአደሩ እንዲደራጅ በመደረጉ የግብርና ሥራውን በሜካናይዜሽን ለማከናወን አመቺ ሁኔታ ተፈጥሯል ሲሉ ያስረዳሉ።

መንግሥት የማሽነሪ አቅርቦት ያደርጋል አርሶ አደሮችም በእራሳቸው የሚገዙት አለ፤ ከ285 በላይ ትራክተሮችንም መንግሥት በብድር ለአርሶአደሮች አቅርቧል። ይህም ጊዜና ጉልበትን በመቀነስ ምርታማነትን ለመጨመር ዓይነተኛ አማራጭ እንደሚሆን ይታመናል።

እንደ አቶ አሊዩ ከሆነ፤ በአጠቃላይ በባሌ ዞን ያለው የግብርና ሥራ በቂ ዝግጅት የሚደረግበት፣ በሜካናይዜሽን የተደገፈና በክላስተር የሚለማ በመሆኑ እንደአገር የሚታሰበውን የምግብ ዋስትና የማረጋገጥ አላማ ከግብ ለማድረግ ትክክለኛው መንገድ ላይ ነው ብሎ መናገር ይቻላል።

# የሐረሪ ክልል የሥራ ውጤታማነትን፣ ብቃትና ሥነ ምግባር መነሻ ያደረገ የአመራር ምዘና እንደሚያካሂድ አስታወቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በዋናነት የሥራ ውጤታማነትን፣ ብቃትና ሥነ ምግባር መነሻ ያደረገ የአመራር ምዘና እንደሚያካሂድ የሐረሪ ክልል መንግሥት አስታወቀ።

የሐረሪ ክልላዊ መንግሥት ትናንት ባወጣው መግለጫ በየደረጃው ያለው የመንግሥት መዋቅር የሥራ ኃላፊነቱን እየተወጣ መሆኑን በየጊዜው ማረጋገጥና የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል ብሏል።

በመሆኑም በሐረሪ ክልል መንግሥት በዋናነት የሥራ ውጤታማነትን፣ ብቃትና ሥነ ምግባር መነሻ ያደረገ የአመራር ምዘና ለማካሄድ በቂ ቅድመ ዝግጅት መደረጉ ተገልጿል።

በመግለጫው መሠረት፤ ዜጎችም ያለምንም አድሎና እንግልት መንግሥታዊ አገልግሎት የማግኘት መብት አላቸው። በመንግሥትና በሕዝብ መካከል ያለው መሠረታዊ ግንኙነት የአገልጋይና የተገልጋይ ግንኙነት ነው። በመሆኑም በየደረጃው ያለው የመንግሥት መዋቅር ለሕዝቡ ፍትሐዊ ቀልጣፋና ጥራት ያለው መንግሥታዊ አገልግሎት ለሁሉም ዜጋ ማቅረብ ይጠበቅበታል።

ለዚህም አስፈላጊው የአመራር ምዘና እንደሚደረግ ያሳወቀው ክልሉ፤ የምዘናው ሂደቱንም ግልጽ በሆኑ መስፈርቶች እና ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ለማካሄድ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ በጥብቅ ዲሲፒሊን ይመራል ሲል ገልጿል።

መግለጫው እንዳመለከተው፤ ሁሉም አካላት ለሕዝብ ካበረከቱት አስተዋፅኦ እና ካገኙት ተጨባጭ ውጤት አንጻር የማስተካከያ እርምጃዎች ይወሰዳል። በዚህም በሥራ ድክመት፣ በብቃት ማነስ ወይም በሥነ ምግባር ብልሽት ሕዝብ የሚጠብቅባቸውን አገልግሎት መስጠት ባልቻሉ አካላት ላይ ተገቢው እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል።

ሆኖም ግን አንዳንድ አመራሮች በሥልጣን ዘመናቸው ያላስታወሱትን ሕዝብ ግምገማና ምዘና ሲጀመር ውጤታማ ሥራ ባለመሥራታቸው ቁጭት ሊሰማቸው ሲገባ ሕዝቡን «በእናንተ ምክንያት ነው ከወንበሬ የተነሳሁት» ይላሉ ሲል ክልሉ አስታውቋል።

በስርቆትና ምዝበራ የሕዝብ ሀብትን ለግል ጥቅማቸው ሲያጋብሱ የነበሩትም ድርጊታቸው ወደ ሕግ ሲያመራና ተጠያቂ ሲሆኑ «ማንነቴን»፣ «ብሔሬን» ወይም «ሃይማኖቴን» መነሻ ያደረገ ጥቃት ነው የሚሉም መኖራቸውን ጠቁሟል።

ለመደበኛ ሥራቸው ምንም ጊዜ ሳይሰጡ፣ ተቋማቸውን በአግባቡ ሳይመሩ፣ ጊዜው ባመጣው ማህበራዊ ሚዲያ ብቻ ለገጽታ ግንባታ እያዋሉ የሚገኙ አመራሮችም የሥልጣን ጥማታቸውን በፌስቡክ ጋጋታ ለማርካት ይሞክራሉ ሲል የሐረሪ ክልል ገልጿል።

ደግነቱ ሕዝብ እና የጥቅም ተጋሪ ይለያያል። ሕዝቡ ማን ምን እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቃል። በሥልጣን ዘመንህ ሕዝብ የሚፈልገውን ግልጋሎት ሳትሰጥ ቆይተህ ከሥልጣን ስትነሳ አድኑኝ ብትል አይሰማህም። ከሕዝብ ሰርቀህና መዝብረህ ለሕግ ስትቀርብ «የእናንተ ተወላጅ ስለሆንኩኝ ነው» ብትልም ጆሮ አይሰጥህም ሲል ክልሉ አሳስቧል።

ክልሉ እንዳስታወቀው፤ የቀድሞ ጥፋትን በተለያዩ ሽፋኖች ከማለባበስ ይልቅ ችግሮችን ወደ ውስጥ በማየት የራስ ስህተትን ማረም ተገቢ ነው፣ ሁለተኛ ዕድልም ያስገኛል። ስለዚህ ዛሬ ላይ ሆነህ ነገ የማይቆጨበት ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህም ሕዝብን በፍትሐዊነትና በሀቀኝነት ማገልገል ተገቢ ነው።

# የገበያ መዳረሻዎችን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ነው።በዓለም አቀፍ እና የውስጥ ችግር የተፈተነችው ኢትዮጵያ የወጪ ንግድ የገበያ መዳረሻዎችን በተለያዩ አገራት በማስፋፋት ኤክስፖርቱን ውጤታማ ማድረግ ችላለች።

ኢትዮጵያ ገበያዋን አስፋፍታ ተጠቃሚ የሆነችባቸውን አገራት በየዘርፉ ከፍለው የተናገሩት አቶ ገመቹስ፤ እሥራኤል፣ የተባበሩት አረብ ኤሜሬቶች፣ ቬትናም፣ ሲንጋፖርና ቱርክ ከኢትዮጵያ የቅባት እህሎችን በከፍተኛ ደረጃ ሲቀበሉ የነበሩ አገራት ናቸው ብለዋል፡፡

በተመሳሳይ ሕንድ፣ ኢንዶኔዥያ፣ የተባበሩት አረብ ኤሜሬቶች፣ ፓኪስታንና የመን ከ10 ሺህ ቶን በላይ የኢትዮጵያ የጥራጥሬ ሰብሎች የተቀበሉ አገራት መሆናቸውን ጠቅሰዋል።በበጀት ዓመቱ ሶማሊያና ጅቡቲ ከፍተኛ የጫት መጠን ከኢትዮጵያ በመቀበል የተመዘገቡ አገራት ሆነዋል፡፡

በ2014 በጀት ዓመት ስድስት የአገሪቱ ምርቶች በወጪ ንግድ አፈፃፀም ከ100 በመቶ በላይ አፈፃፀም ታይቶባቸው እንደነበር አቶ ገመቹስ ገልፀዋል።የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ምርቶች፣ ታንታለምና ቡና እንዲሁም ሥጋ፣ የወተት ተዋፅዖ፣ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ እና የምግብ መጠጥ ምርቶች ከ101 በመቶ እስከ 199 በመቶ አፈፃፀም የታየባቸው ናቸው ብለዋል።

እንደ አቶ ገመቹስ ገለፃ፤ ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ የብዕርና አገዳ እህሎች፣ የቅባት እህሎች የጥራጥሬ ሰብሎች፣ ባህርዛፍና ኤሌክትሪክ አበረታች ውጤቶች የተገኙባቸው የኤክስፖርት ዘርፎች ናቸው።በሌላ በኩል የቅባት እህሎች፣ የጥራጥሬ ሰብሎች፣ ጫትና የቁም እንስሳት የወጪ ንግድ ዘርፍ አፈፃፀም ላይ ከ60 በመቶ በታች አፈፃፀም የታይባቸው ሆነዋል።

የቅባት እህሎች የወጪ ንግድ አፈፃፀም ላይ ዝቅተኛ የኤክስፖርት መጠን መታየቱን የገለፁት አቶ ገመቹስ፤ ለዚህም እንደምክንያት የተቀመጡትን አንስተዋል።የሰሊጥ እህል የአገር ውስጥ ዋጋ በመናሩ ምክንያት በወቅቱ ለዓለም አቀፍ ገበያ በተወዳዳሪ ዋጋ ማቅረብ አለመቻል።በላኪዎች በክምችት በመያዙ ምክንያት በወቅቱ ለውጭ ገበያ ባለመቅረቡ በኤክስፖርት አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል ብለዋል፡፡

የኑግ እህልን አስመልክቶም በነበረው የሰላም እጦት እና አለመረጋጋት ምክንያት ምርቱን በወቅቱ ወደ ገበያ ቀርቦ ግብይት ለመፈጸም፣ ለማጓጓዝና ለማዘጋጀት በንግድ እንቅስቃሴ ላይ ስጋት በመፍጠሩ፣ በወቅቱ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ባለመቻሉ መሆኑን ጠቅሰው፤ የለውዝ ምርት በአፍላቶክሲን ምክንያት ገዥ አገሮች በምርት ጥራት ጉደለት ምክንያት ፍላጎት አለመኖር መሆኑን ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ ገመቹስ ገለፃ፤ ለወቅታዊ የውጭ ገበያ ችግሮች የመዳረሻ ገበያዎችን ለማስፋት የተደረገው ጥረት ጎን ለጎን በአገር ውስጥ የነበሩ አሳሪ አሠራሮችን የማሻሻል ተግባር መከናወኑ እና ከላኪ ነጋዴዎች ጋር ተደጋጋሚ ውይይት መደረጉ ለወጪ ንግዱ መጨመር አስዋፅዖ አበርክቷል፡፡

ለአብነትም ከጫት ጋር የነበሩ የኤክስፖርት ክፍተቶችን ለማረም ሰፋፊ ሥራዎች መሠራታቸውን፤ ከሰብልና ከቅባት እህሎችም በተያያዘ ከላኪዎች ጋር በተደጋጋሚ ውይይት በማድረግ በእጃቸው የያዙትን ምርቱን ወደ ውጭ ማውጣት የሚችሉበትን ሁኔታ መመቻቸቱን ገልፀዋል።ሁኔታዎች ተመቻችተው እያሉ ለአሻጥር እና በሌሎች ምክንያቶች ምርቶችን ይዘው የቆዩት ላይም አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ተደርጓል ብለዋል፡፡

# ‹‹በውጭ የሚገኝ የትግራይ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሺ ዶላር በማውጣትና አዳራሽ በመከራየት ፌስቲቫል ‹‹መኸተ ሰለስተ›› በማለት ሲያካይዱ ሰንብተዋል፡፡

በውጭ አገር ያሉት የትግራይ ተወላጆች በትክክል የትግራይ ሕዝብን የሚያስቡለት ከሆነ በገንዘባቸው ሕዝቡን ከገባበት ችግር ሊያስወጡት ይገባል ያለው አቶ ናትናኤል፣ ይሁን እንጂ በውጭ አገር ያሉት አብዛኞቹ የትግራይ ተወላጆች ሕዝቡን እየደገፉት አይደለም ብሏል፡፡

ይህ ፌስቲቫል ሲዘጋጅ በትግራይ ውስጥ ፖለቲካዊና ማህበራዊ መፍትሔ ያመጣል ብሎ የሚያስብ የትግራይ ተወላጅ ወይም ግለሰብ ካለ የማይታሰብ ነገር ነው ያለው አቶ ናትናኤል፣ ፌስቲቫል ሲካሄድ ሁሌም ከመጨፈርና ከማጨብጨብ ያለፈ ሌላ ለትግራይ ሕዝብ የሚያመጣለት ጥቅም የለም ሲል ገልጿል፡፡

በፌስቲቫሉ አንዳንድ ጥያቄዎች ያላቸው የትግራይ ተወላጆች ሓሳባቸውን ቢያቀርቡም እንደ የትግራይ አንድነት አፍራሽ ተወስዶ ጥያቄዎቹን ሳይቀበሉና መልስ ሳይሰጡ የነበረውን ስብሰባ ያለ ሰዓቱ ዘግተዋል ብሏል፡፡

ሕወሓት በተፈጥሮም ዴሞክራሲያዊ አይደለም ያለው አቶ ናትናኤል፣ በውጭ አገር የሚኖረው አብዛኛው የትግራይ ተወላጅም ይህንን የሕወሓት ባህርይ በአግባቡ ሳይገነዘብ የሚከተል እንጂ ሕዝቡን የሚያስብ አይደለም ሲል ተችቷል፡፡

በትግራይ ውስጥ ያሉት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጠንክረው መታገል አለባቸው ያለው አቶ ናትናኤል፣ አንድ ዓይነት ኣቋም በመያዝ አዲስ ትውልድ በመፍጠር ትግራይ ወደ ነበረችበት ሰላምና ልማት እንድትመለስ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል ብሏል፡፡

በተለይ የሽመገሉ እና ከዓለም ፖለቲካ እኩል መራመድ የማይችሉትን የሕወሓት መሪዎች፣ የትግራይ ሰራዊት ከስልጣን በማውረድ በአዲስ ትውልድ መተካት እንዳለበት መክሯል፡፡

ዴሞክራሲ የማይሰጥ፣ ሚድያ የሚከለክል ጠላት ሕወሓት ነው ያለው አቶ ናትናኤል፣ የትግራይ ተወላጆች ወንዝ እየተሻገርን የሌላ ፖለቲካ ከመውቀስ ይልቅ በውስጣችን ያለውን ጠላት መታገል አለብን ብሏል፡፡

አቶ ናትናኤል «የትግራይ ሁኔታ እየተባባሰ የሚሄድ ችግር እንጂ የሚሻሻል ነገር የለውም፣ በመሆኑም በውጭ ያለው የትግራይ ተወላጅ ሕወሓትን ከመደገፍ ወጥቶ ለውጥ የሚያመጣውን መንገድ መከተል አለበት» ሲል ምክረሃሳቡን ለግሷል፡፡

# «የኢትዮጵያ ጠላቶች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እጦት መኖሩን ማሳየትና የፀጥታ ጉዳይ ቀዳሚ አጀንዳ እንዲሆን ከመፈለግ የሚመነጭ ነው ሲሉም ገልጸዋል።

በ21ኛው ክፍለ ዘመን ኃያላን አገራት ቀይ ባህር አካባቢን ለመቀራመት የሚደርጉት ፉክክር በኢትዮጵያ ላይም የራሱ ተጽዕኖ ይኖረዋል ያሉት ኡስታዝ ካሚል፤ ኃያላን አገራቱ ደካማ መንግሥት በመፍጠር አላማቸውን በቀላሉ ማስፈፀም ይፈልጋሉ ብላዋል። ከዚህ ባለፈ ኢትዮጵያ በመልካምድር አቀማመጧና በአየር ንብረቷ ምቹነት ተመራጭ በመሆኗ አገራቱ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ መኖሩን ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያን በውል ያልተገነዘቡ ጠላቶች ከጥንት ጀምሮ በተሳሳተ ግንዛቤ በኢትዮጵያውያን መካከል የከፋ ክፍፍል እንዳለ ይረዳሉ። ይሁንና ኢትዮጵያን ለማዋረድና ለማጥቃት በመጡበት ጊዜ ሁሉ በተባበረ ክንድ ሲደፈቁና ሲዋረዱ ቆይተዋል። በቅርብ ጊዜ እንኳን በተሳሳተ ግንዛቤ የኢትዮጵያን ክብር ለመንካት ሰተት ብሎ የገባው የአልሸባብ ታጣቂ ቡድን ተመሳሳይ ዕድል ገጥሞት ተገቷል ብለዋል፡፡

ኡስታዝ ካሚል እንዳሉት፤ ጠላቶቻችን በተለያዩ ጊዜያት በድብቅ ሲያደርጉ የነበረውን ጥቃት አሁን በገሃድ ጭምር በማሳየት በጦርነት ሊፈትኑን ሞክረው አልተሳካላቸውም። ኢትዮጵያውያን በአገር ክብርና የውጭ ወራሪ ኃይል ላይ ያላቸው የሚደነቅ የጋራ አቋም በሰላሙ ጊዜ በውስጥ ጉዳያቸው ላይ ሊደገም ይገባል። በሰላም ጉዳይ የጋራ አቋም ከያዝን ዛሬ በየቦታው የሚያጋጥመን የጸጥታ ችግር ቦታ አይኖረውም።

እንደ ኡስታዝ ካሚል አስተያየት፤ የውስጥ ልዩነታችን እየሰፋ ከሄደና አገሪቱ የጠላቶችን ሴራ በማክሸፍ ላይ ከተጠመደች በጊዜ ሂደት መልካም እሴቶቻችን ተሸርሽረው ይበልጥ ደካማ እንዳንሆን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

በመሆኑም አሁን ያለው ለውጥ መስመሩን ጠብቆ እንዲጓዝ ማድረግና የጠላቶችንን ሴራ ማክሸፍ ይገባል። የውጭ ጠላቶች ለውጡ ዳር እንዳይደርስ በድንበር ጉዳዮችና በህዳሴ ግድብ ዙሪያ እንዲሁም በተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ እጃቸውን በመቀሰር ችግር እንደሚፈጥሩ አስረድተዋል።

እንደ ኡስታዝ ካሚል ማብራሪያ፤ ችግሮችን በመንቀስ በሕዝቡ መካከል መርዝ እየረጩ መሆኑ በውል በመገንዘብ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

በፖለቲካ አለመግባባት ምክንያት በአገሪቱ ውስጥ አንዱ የገነባውን ሌላው የሚያፈርስ፣ አንዱ ሰላም ሰባኪ ሌላው ግጭት ጠንሳሽ የሚሆንበት ሁኔታ ለአገር ህልውና ትልቅ ፈተና ሆኗል፡፡ በመሆኑም አገሪቱ ከገጠሟት ፈርጀ ብዙ ችግሮች ለመላቀቅ የአንድ ወገን ብቻ ሳይሆን የሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡

«ጥያቄ አለኝ» የሚሉ ወገኖች ሁሉ ጥያቄያቸው በእውነቱ የራሳቸው ወይስ የውክልና የሚለውን ለመረዳት ሁሉንም ወደ አንድ ጠረጴዛ በማምጣት መነጋገር ጊዜው አሁን ነው ያሉት ኢስታዝ ካሚል፣ ለዚሁ ደግሞ ለአገራዊ ምክክሩ ትልቅ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

በአጠቃላይም የጠላትን ሴራ በጥንቃቄ ማክሸፍ፣ ለአገር ፍቅር በህብረት መቆምና ሃሰተኛ መረጃዎችን ማጋለጥ እንዲሁም የጸጥታና ደህንነት ሥራዎችን በማጠናከር የጠላቶቻችንን አላማ በየጊዜው ለመግታት በአድነት መቆም ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ታላቅ የምስራች…!

መንግስት የግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የግብርና ምርምር ተቋማት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ የሚያስችሉ አዳዲስ ዝርያዎችን እንዲያፈልቁ፣ እንዲያላምዱና ለአርሶ አደሩ እንዲዳረሱ፤ ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያና የመሳሰሉት የሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎችን በማቅረብ ሲሰራ ቆይቷል፤ እየሰራም ይገኛል። ይህን ተከትሎም የግብርናው ምርትና ምርታማነት እየጨመረ ቢሆንም፤ ግብርናው ካለው እምቅ አቅም እንዲሁም ከሀገሪቱና ህዝቧ ፍላጎት አኳያ ሲታይ እድገቱ የሚፈለገው ደረጃ ላይ አልደረሰም። ኢትዮጵያ ስንዴ ከውጭ ስታስገባ መኖሯ እና አሁንም የእህል ዋጋ በየጊዜው እየጨመረ መሆኑ ለእዚህ ማሳያዎች ናቸው። ግብርና ለኢኮኖሚ መዋቅር ያበረክታል የተባለውን አስተዋጽኦ በሚፈለገው ደረጃ ማበርከት አለመቻሉም ሌላው ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

መንግስት ይህን ችግር የሚፈቱ እርምጃዎችን በመውሰድ ምርትና ምርታማት ላይ በትኩረት መስራት ዋናው መፍትሄ መሆኑን በማመን ለግብርናው ዘርፍ የሚሰጠውን ትኩረት ከወትሮውም በላቀ መልኩ አጠናክሮ ቀጥሏል። በግብርናና በምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ዘንድ ሲነሳ የኖረው የአርሶ አደሮችን አነስተኛ ማሳ ይዞ ስለሜካናይዜሽን እንዴት ይታሰባል የሚለው ጉዳይ በኩታ ገጠም እርሻ እውን መሆን መፍትሄ እያገኘ ነው። የግብርና ማሽነሪዎች ከቀረጥ ነጻ መግባትም ጀምረዋል። በመንግስት እርሻዎችና አንዳንድ የግል ባለሀብቶች ማሳዎች ብቻ ይታዩ የነበሩት ትራክተሮች አርሶ አደሩ መንደር መግባት ጀምረዋል። ይህ ትልቅ እርምጃም፤ የምስራችም ነው።

የብሄራዊ ፕላን ሚኒስትር ዶክተር ፍጹም አሰፋ ሰሞኑን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በአዳማ ከተማ ባዘጋጀው ሰባተኛው ስለኢትዮጵያ የፎቶግራፍ አውደርዕይና የፓናል ውይይት ላይ እንዳስታወቁት፤ መንግሥት ግብርናውን በማዘመን ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ከትራክተር ጀምሮ አነስተኛ የግብርና የግብዓት መሣሪያዎች ከቀረጥ ነፃ ከውጭ እንዲገቡ እያደረገ ነው። ይህም መንግስት ለሜካናይዜሽን የሰጠው ትኩረት አንዱ ማሳያና ትልቅ ውሳኔ ነው። በአሁኑ ጊዜም በሀገር ደረጃ እየተከናወነ ባለው የግብርና ሥራ የግብርና ሜካኔይዜሽን ተግባር ላይ እያዋለ ሲሆን፤ ይህን ተከትሎም 30 በመቶ የሚሆነው የእርሻ መሬትም በዘመናዊ የግብርና ማረሻ መሳሪያዎች (ትራክተር) መታረሳቸውን የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲን መረጃ ያሳያል።

የግብርና ሚኒስቴር መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በአሁኑ ወቅት ስምንት ሺህ ትራክተሮች በአርሶ አደሩ ቀዬ ግብርናውን እያሳለጡ ይገኛሉ። የሜካናይዜሽን ባለሙያዎችን በማሰልጠንና የጥገና ማእከላትን በማደረጃት እየሰራ ነው። የየክልሎች መረጃዎችም ይሄንኑ ነው የሚያስረዱት። ለምሳሌ፣ በኦሮሚያ ክልል ብቻ በአሁኑ ወቅት አምስት ሺህ ትራክተሮች በእርሻ ስራ ላይ ናቸው። በአማራ ክልልም ከሶስት መቶ በላይ ትራክተሮች ያሉ ሲሆን፣ እስከ አንድ ሺህ ትራክተሮችን ለማቅረብም እየተሰራ ነው። ደቡብ ክልል ብቻ በዚህ የመኸር ወቅት 288ሺ ሄክታር መሬት በትራክተር ለማረስ ታቅዶ እየተሰራ ነው። በሌሎች ክልሎችም ተመሳሳይ ተግባሮች መከናወን ጀምረዋል።

እነዚህ መረጃዎች በአንዳንድ ህብረት ስራ ማህበራት በኪራይ ትራክተሮችና ኮምባይነሮች እጁን ያሟሸው ግብርና፤ ሰፉ ወዳለ የሜካናይዜሽን ተጠቃሚነት እየተሸጋገረ መሆኑን ይጠቁማሉ። የሜካናይዜሽን መሳሪያዎችን ከቀረጥ ነጻ መፈቀዱ፣ አርሶ አደሮችና መንግስት ለትራክተርና ሌሎች ሜካናይዜሽን መሳሪያዎች ያላቸው ጽኑ ፍላጎት ሲታሰብ ደግሞ ቀጣዩ ዘመን የግብርናው ዘርፍ እምርታ የሚታይበት ነው ያሰኛል።

ለግብርናው ከፍ ያለ ትኩረት በተሰጠበት ጥቂት አመታት ውስጥ በእዚህ ልክ በትራክተር ማረስ ከታቻለ በእርግጥም የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት በማረጋገጥ ባጠረ ጊዜ ውስጥ ግብርናውን መለወጥ ይቻላል። ምክንያቱም ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ መጠቀም እንዲሁም በኩታ ገጠም እርሻ ማረስ ምን ያህል ውጤታማ መሆን እንደሚያስችል ባለፉት አመታት መመለከት ተችሏል። እናም 30 በመቶው የእርሻ መሬት በሜካናይዜሽን /ትራክተር/ እየተከናወነ ባለበት በተያዘው የምርት ዘመንም በግብርናው ምርትና ምርታማነት ትርጉም ያለው ለውጥ እንደሚመጣ ይጠበቃል።

አርሶ አደሩ በትራክተር እንዲያርስ የሚፈልገው መንግስት ብቻ አይደለም፤ አርሶ አደሩም በእጅጉ ይፈልጋል። የግብርና ባለሙያዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የዘመናት ጥያቄውም ይሄው ነው። የሜካናይዜሽን ማሽኖች ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ መደረጉ በቀጣይም በርካታ ትራክተሮችና ኮምባይነሮች እንዲሁም ሌሎች የግብርና ማሽነሪዎች ወደ አርሶ አደሩ መንደር እንደሚዘልቁ ይጠበቃል። የፋይናንስ ተቋማትም ለአርሶ አደሩ ብድር ወደ ማቅረብ በመሸጋገር የመንግስትን ሸክም ማገዝ ይኖርባቸዋል። እነሱ ይህን ሃላፊነት መውጣት ሲጀምሩ ደግሞ ለውጡ ከፍተኛ እንደሚሆን ይታሰባል።ምክንያቱም ግብርናው ሲሰጡት ይበልጥ የሚሰጥ መሆኑ በተጨባጭ ታይቷል። አብዝቶ ሰጥቶ ብዙ መጠበቅ ይቻላልና አሁንም ከግብርናው ብዙ ለማግኘት አርሶ አደሩን የሜካናይዜሽን ተጠቃሚ ለማድረግ የተጀመረውን ጥረት ይበልጥ ማጠናከር ይገባል።

መንግስት እንደ እስከ አሁኑ ሁሉ ግብርናውን ከኋላ ቀር አስተራረስ ለማውጣት የያዘውን ርብርብ ሲያጠናክር ለውጡን ሊያፋጥኑ የሚችሉትን የፋይናንስ ተቋማት እንዲቀላቀሉት በማድረግ ጭምር መሆን ይኖርበታል። ተቋማቱም ገጠሩን ማእከል ያደረጉ አሰራሮችን በመቀየስ መስራት ይጠበቅባቸዋል። የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ለሆነው ግብርና ፋይናንስ እንዲያቀርቡ በማድረግ በኩል መንገዱን ማሳየት የመንግስት ሃላፊነት ይሆናል። በዚህም ግብርናውን ለዘመናት ከኖረበት ኃላቀር አስተራረስ ዘይቤ በማውጣት እና ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ለኢኮኖሚ ሽግግሩ ዋና መሳሪያ ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህም የግብርና የሜካናይዜሽን ማሽነሪዎችን ለአርሶ አደሩ በማድረስ በግብርናው ዘርፍ ላይ የታየው ታላቅ የምስራች ከምስራችም ባሻገር እንዲሆን በዘርፉ ላይ መስራቱን አጠናክሮ መቀጠል ይገባል።

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# ለዓለም "አንድ መንደርነቷን' የመጠነ ርዕዮት እናበርክት

ግርማ መንግሥቴ

አሁን አሁን አለማችን የምትገለፅበት ቋንቋ ከወትሮው የተለየ ነው። ምናልባትም ዘመን አፈራሹ ቴክኖሎጂ የፈጠረው፤ አልያም የዲፕሎማሲው ጉዳይ ብቻ አለማችን እየ"ጠበበች" (ወደ አንድ መንደርነት እየመጣች) እንጂ እየሰፋች አይደለም። "አለም አንድ መንደር ሆናለች" የሚለው አባባል በሁሉም ዘንድ ማለት በሚቻል ደረጃ እየተለመደ ብቻ ሳይሆን እየተዘወተረ ይገኛል። በፊት "ሶስተኛው አለም" (አፍሪካን)፣ "የሰለጠነው አለም" (ምእራቡን)፣ "መካከለኛው ...." ወዘተ እየተባለ እንዳልተሸነሸነ ሁሉ፤ ዛሬ (ቢያንስ በሰነድ፣ በቃል ደረጃ) "አለም አንድ መንደር ሆናለች" ወደ'ሚለውና አብረን እንስራ፣ አብረን እንሁን፣ የጋራ ደህንነታችንን እናስጠብቅ፣ የጋራ ተቋማት እንገንባ ... ወዘተ የሚለው ነገር የመንግስታት የእለት ተእለት ተግባርና አሳሳቢ ጉዳይ ሆኗል።

ረቂቁና የአንድን ወገን የበላይነት ለማስቀጠል ታስቦ የተወጠነ መሆኑ የሚታመንለት "አዲሱ የአለም ስርአት" (New World Order) እንኳን በማይዘወተርበት ደረጃ "አለም አንድ መንደር ሆናለች" የሚለው ሰፊውን የአየር ሰአት ይዞ ነው የምናገኘው። ታዲያ ይህ ሁሉ ይባል እንጂ አንድ መንደርነቷን መቀበል የማይፈልጉ፤ የተከፋፈለች አለምን መፍጠር የሚፈልጉ አካላት የሉም ማለት አይቻልም። አለምን ቀርቶ አገርን ሳይቀር ለማፍረስና ፍርስራሿንም እያነደዱ መሞቅ የሚፈልጉ ድኩማን የሉም ማለትም አይቻልም።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን "አለም አንድ መንደር ሆናለች" ከሚለው ብዙም መሰረታዊ ልዩነት በማይታይበት ደረጃ "ግሎባላይዜሽን" የሚለው ፅንሰ ሀሳብም መቀንቀን ከጀመረ ሰነባብቷል። ምንም እንኳን በጥንቃቄ ካልያዙት፣ በብልሀት ካላስተናገዱት በኒዎሊብራል አስተሳሰብና ፍላጎት መዋጥን ያስከትላል የሚለው ነገር አስፈሪ ቢሆንም፤ ቢያንስ በአስተሳሰብና ፅንሰ ሀሳብ ደረጃ የሚያስተላልፈው መልእክት ቢኖር ቀደም ሲል ያልነውን፤ "አለም አንድ መንደር ሆናለች" የሚለውን ባልተነጣጠለ አለም ውስጥ ስለሚኖረው አንድ ህዝብ ነውና ይዘን ከተነሳነው ሀሳብ ጋር የሚጣላ አይደለም።

"አለም አንድ መንደር ሆናለች" ከሚለው እሳቤ በተጓዳኝ ደግሞ፤ አለማችን ወዴት እየሄደች እንደሆነና አንዳንዶቻችን በተቃራኒው ወዴት እየሄድን እንደሆነ ማየቱ ተገቢ ይሆናል። ምክንያቱም ዛሬ አለማችን አንድ መንደር ሆናለች ቢባልም፤ አንድ በሆነችው መንደር ውስጥ ይህች መንደር የምትመራበት የተለያየና የተበጣጠሰ ርዕዮት እየናጣት መሆኑን በመገንዘብ ነው።

እንደሚታወቀው፣ አለማችን ከኃይማኖትም፣ ከባህልም፣ ከጎበዝ አለቃም ... አመራር ተላቅቃ ለፖለቲካው እጇን ከሰጠች ቆየች። ፖለቲካውም በስመ ዲሞክራሲ በምሎ በመገዘት አለምን የመምራት ሀላፊነቱን ከተረከበ ቆየ። ችግሩ የመረከብና ማስረከብ፤ ወይም፣ የመረካከብ ጉዳይ አይደለም። ችግሩ ያለው ፖለቲካው ዘመኑን በመጠነ መልኩ መምራት አለመቻል/መቻሉ ላይ ነው።

እንደሚታወቀው፣ አለማችንን ሊመራት የሚገባው ፖለቲካው ነው፤ ፖለቲካውም መመራት ያለበት በፖለቲከኞች ነው፤ የሚል አስተሳሰብ አለ። ይህንን ተከትሎም በዛን ዘመን የነበሩ ቅን አሳቢዎች አዎ ፖለቲካና ፖለቲከኞች የመሪነት ስፍራውን ሊይዙ ይገባል (ፕሌቶ (Republic) እና ተከታዮቹ ባይደግፉትም – "philosopher king"ን ያስታውሷል) አሉ። ይሁን እንጂ አማራጭ ፖለቲከኞችና አማራጭ ሀሳቦች ያስፈልጋሉ። ይህም የሀሳብ ፍጭትን በመፍጠር የተሻለና ህዝብን የሚጠቅም ስራ ይሰራ ዘንድ ያበረታታል። በመሆኑም ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች መኖር አለባቸው የሚል "ድምዳሜ" ላይ ተደረሰ። ተደርሶም ወደ ተግባር ተገባ። ይህ እሳቤ እንዳለ ቢሆንም፤ በአሁኗ የአለማችን ይዞታ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን የማያስተናግድ አገርም ሆነ ሕገ-መንግስትና መንግስት' በአጭር አገላለፅ ዲሞክራት መንግስታት አይደሉም፤ ወይም አምባገነን ስርአት/አገዛዝን በህዝባቸው ላይ የጫኑ ፀረ-ዲሞክራት ኃይሎች ናቸው የሚል የጋራ ግንዛቤ ነው ያለው።

ችግሩ ይህ አይደለም። እኔም ይሄን ለመሞገት አይደለም። ምክንያቱም አስቀድመን ከላይ እንዳልነው፣ "አለም አንድ መንደር ሆናለች"። ባትሆንም እንኳን ወደ'ዛው እየሄደች ነው ተብሎ ይታሰባል። ዩሮ (ገንዘብ) የዚህ አንዱ ማሳያ ነው። ቻይና እየገነባች ያለችው የባቡር መስመርም (ሮድ ኤንድ ቤልት) ሁለተኛው ነው። አፍሪካን አንድ የማድረግ ጥረትና እንቅስቃሴውም እንደዛው።

የዚህ ጽሑፍ ዐቢይ አላማ ተቃዋሚነት ከዘመናዊነት ጋር ለምን ይጣላል? ለምንስ በተቃራኒ ይቆማል? በተቃራኒ ቆሞስ ለምን ከሰላም ይልቅ ተቃርኖን ያነግሳል? ተቃውሞው ለፉክክር መሆን ሲገባው ተቃውሞው ለምን ለመበላላት፣ ለመጨራረስ... ይሆናል? እና የመሳሰሉትን ትዝብትና ብስጭት አዘል ጥያቄዎችን ለማንሳትና የሚመለከታቸው እንዲያስቡበት ለማሳሰብ ነው። ገጣሚው "... ምናልባት ቢያስፏጨው" እንዳለው ማለት ነው።

ከላይ ለ"አለም አንድ መንደር ሆናለች" ማሳያ ይሆነን ዘንድ ከመልካም ተግባራት መካከል በሁሉም ሰው ዘንድ ይታወቃሉ ያልናቸውን አቅርበናል። ይሁን እንጂ፣ ከእነዚህ መልካም ካልናቸው ተግባራት የበለጠ አለማችን አንድ መንደር መሆኗን፤ ህዝቦቿም አንድ ህዝብ መሆናቸውን የሚያመለክቱ በርካታ መከራዎች ነበሩ፤ አሉም። ወደፊትም ይኖራሉ፤ እንደ አንዳንዶች ትንበያ የወደፊቶቹ ይብሳሉ።

ከእነዚህ "አለም አንድ መንደር" መሆኗን ከሚያሳዩ መከራዎች መካከል ሊጠቀሱ የሚገባቸው በርካታ መከራዎች ቢኖሩም፣ ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ ሰዎች ግን የሚጠቅሷቸው የቅርብ ማስረጃዎች አሏቸው። አንዱና የዘመናችን የሰው ልጅ መቅሰፍ የሆነፍ ኮቪድ-19 (ኮሮና) ነው። በዚህ ባለንበት ዘመን እንደዚህ ቫይረስ የአለምን ህዝብ አንድ ያደረገ፤ በአንድ ሳንባ እንዲተነፍስ፣ በአንድ አንደበት እንዲናገር፣ ለአንድ መፍትሄ እንዲረባረብ፤ ለአንድ መመሪያ እንዲገዛ፣ በአንድ መመሪያም እንዲተዳደር፣ ለአንድ ነገር እንዲተጋ፣ አንድ ነገርንም እንዲያደርግ... ያደረገ የጋራ ጠላት (ቫይረስ) የለም። ኤችአይቪ/ኤድስ... እና ሌሎችንም ከዚሁ ጋር አያይዞ መግለፅ ይቻላል።

ይህ ብቻም አይደለም፤ "አለም አንድ መንደር ሆናለች" ሲባል መገለጫውም ሆና ማሳያው ብዙ ሲሆን፤ ከብዙዎቹም ጥቂቶቹ የአየር ንብረት ለውጥ፤ ሽብርተኝነት፤ ፅንፈኝነት፤ ወንጀለኛነት፣ የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ መሄድ፣ የስፖርት መስፋፋት... ወዘተርፈ ናቸው።

እነዚህና ሌሎች አሁን እኛ የማናውቃቸው ሁሉ አለምና የአለም ሕዝብ፣ ወደደም ጠላም እጅ ለእጅ እንዲያያዝ፤ ትከሻ ለትከሻ እንዲደጋገፍ፣ ሀሳብ ለሃሳብ እንዲረዳዳ፣ በድንበርና ማንነት ስም እንዳይታጠር፣ ተነጣጥሎ ሳይሆን በጋራ እንዲቆም... የሚያደርጉ ናቸው። ጥያቄው እነዚህን ሁሉ ለመቋቋም፤ መፍትሄያቸውንም ለማፍለቅ.... የሚበጀው ባልተነጣጠለ አለም ውስጥ ያልተበጣጠሰ ርእዮት አለምን በማራመድ ነው።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ያስፈልጋሉ ወይ? ብለን ከጠየቅን ወደድነውም ጠላነውም መልሱ "አዎ፣ ያስፈልጋሉ" ነው። ችግሩ ምን አይነት ርእዮት የያዙት ይምጡልን የሚለው ነው። ወደዱትም ጠሉትም እኛ የምንፈልገው ከዘመኑ ጋር የዘመነና "አለም አንድ መንደር" መሆኗን ከልቡ የተረዳውን የፖለቲካ ፓርቲ (ተቃዋሚም ይሁን ሌላ) እንጂ አንድ በሆነ ህዝብ ውስጥ የተበጣጠሰ ርእዮት አራማጅን አንፈልግም (እንደ Croly (The Rise and Fall of Political Parties in Americaን አንብብ) አይነት አስወጋጅ አቀቋምን ባንይዝ እንኳን)። እኛ ብንፈልገው እንኳን ሄዶ ሄዶ በራሱ ጊዜ የሚጠፋ (የሚከስም) ነውና እኛ ባንለው እንኳ እራሱ ሊያስብበት ይገባል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ሙያና ሙያተኛው ያልተገናኙበት የፋሽን ዘርፍ

**ተገኝ ብሩ**

አንድ ተግባር ውጤታማ እንዲሆን ተግባሩን በትክክል በሚረዳውና ለዚያ ተግባር በቂ የሆነ እውቀት፣ ክህሎትና ሙያዊ ስነምግባር ባለው ሰው መከወን ይኖርበታል። ተግባር በእውቀት ካልታገዘ ፍሬ አልባ፤ ስራ በክህሎት ካልተሟሸ ለዛ ቢስ፤ ክንውን በሙዊ ስነ ምግባር ካልታጀበም ጎዶሎ ይሆናል። ለዚህ ነው አንድ ሙያ የሙያውን ክብር በሚመጥን መልኩ መተግበርና ሙያውን ጠንቅቆ በሚያውቀው ሰው መመራት ወይም መተግበር ይገባዋል የሚባለው።

የፋሽን ዲዛይነርነት ጥልቅ ጥበብ የተላበሰ፣ ፈጠራና የነጠረ እይታ ከስሜት ጋር መላበስን የሚፈልግ ትልቅ ሙያ ነው። በእርግጥ የሙያውን ትልቅነት ተረድተው የሚገባውን ትኩረት የሰጡት አገራት ዘርፊ ብዙ ጠቀሜታን አግኝተውበታል። በአንጻሩ በፋሽን ዘርፍ ያለውን ዘርፊ ብዙ ጠቀሜታ ዘግይተው የተረዱ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገራት ላይ ዘርፉ የእድገት ውስንነት ይታይበታል።

ከተሰራበት ሰፊ የስራ እድል መፍጠር እና ለኢኮኖሚያዊ እድገትም ትልቅ አበርክቶ ሊኖረው የሚችለው የፋሽን ኢንዱስትሪ የሚያበረክተውን ፋይዳ ያህል ትኩረት የተሰጠው አይመስልም። የፋሽን ዲዛይን፤ ምርት በስፋትና በጥራት በማቅረብ በአገር ውስጥ ብሎም በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን ያስችላል። በዚህም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን ለማሳደግ ይቻል ዘንድ ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል። ለዚህም የዘርፉን አስፈላጊነት መረዳት፣ ለእድገቱ ምን ያስፈልገዋል የሚለውን ለመለየት፣ ጥናት ማድረግና ወሳኝ የመፍትሄ እርምጃዎች መውሰድ ወደ ውጤት ያቃርባል።

የፋሽን ዲዛይን ሙያ በኢትዮጵያ አዲስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በርካታ ውስንነቶች እንደሚታዩበት የዘርፉ ባለሙያዎች ይጠቁማሉ። ለፋሽን ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ሰፊ ገበያ ያላት ኢትዮጵያ፤ ኢንዱስትሪውን አጠናክራና ትኩረት ሰጥታ መስራት ትርፋማ እንደሚያደርጋትም ይታመናል። ኢትዮጵያ ባላት ምቹ አጋጣሚ ዘርፉ የውጪ ምንዛሬ ማመንጫና ሰፊ የስራ ዕድል መፍጠሪያ ማድረግ እየቻለች በተለያዩ ምክንያቶች ወደፊት መራመድ ተስኗታል።

ለዚህ ዘርፍ ወሳኙና ዋነኛው ተግባር መሆን የሚገባው




በቂና ብቁ የሆነ የሰው ኃይል ማፍራት ነው። በፋሽን ዲዛይን ባለሙያዎችም ለዘርፉ እድገት ማነቆ የሆነው የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖር መሆኑን እንደምክንያት ይጠቅሳሉ። በባለሙያዎች በቂ የሆነ የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖር፣ የዘርፉን ትልቅነትና ስፋት ያህል ማሰልጠኛ ተቋማት በወጉ አለመደራጀታቸውና የዘርፉ ተዋናዮችም የሙያውን ስነምግባር ያሟላ የአገልግሎት አሰጣጥ አለመከተላቸው ነው። እንደ አጠቃላይ ዘርፉ ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑ በአገር ደረጃ ተጽዕኖ ፈጣሪ እንዳይሆን አድርጎታል።

እንደ ዘርፉ ትልቅነትና ገበያው ላይ እንዳለው ሰፊ ፍላጎት አንጻር ትኩረት ተሰቶ ቢሰራበት የሚያስገኘው ትልቅ ፋይዳ እንዳለ የምትናገረው ዲዛይነር ሜሮን ኃብተጊዮርጊስ ናት። ስልጠና የሚሰጡ ተቋማትም ሙያዊ ስልጠናዎችና ግብዓቶችን አሟልተው መቅረብ አለባቸው ትላለች። ከዚህ ጋር ተያይዞ ለዘርፉ ወሳኝ የሆኑት የፋሽን ዲዛይን ባለሙያዎች ሙያቸውን ለማሳደግ ሙያዊ ስነምግባር ተላብሰው ቢሰሩ የተሻለ ውጤት ማግኘት እንደሚችልም ታስረዳለች።

የፋሽን ዲዛይን ሙያ በፊት ከነበረው አንጻር የተሻለ ደረጃ ላይ ቢገኝም እጅግ ውስብስብ ችግሮች ያሉበት በመሆኑ የሚጠበቀውን ውጤት ለማምጣት አዳጋች እንደሆነ የምታስረዳው ሜሮን፤ ሙያዊ እውቀትና ክህሎት ሳይላበሱ ራሳቸውን "ዲዛይነር ነኝ" በሚል ወደ ስራው የሚገቡ ግለሰቦች መበራከታቸውን ታስረዳለች። ይህም ሙያው እንዳይከበርና ከጅምሩ እድገት እንዳይኖረው እንቅፋት ፈጥሯል።

በሌላ በኩል ሙያተኛውን የሚያሰለጥኑ ተቋማት ቢኖሩም የሚሰጡት ስልጠና በቂ አለመሆኑን ትገልጻለች። ዋነኛ ችግር ያለባቸው ተቋማት ደግሞ የግሉ ዘርፍ እንደሆኑ በማስረጃነት ትጠቅሳለች። በቂ የሆነ ሙያዊ ስልጠና ከሚሰጡ ተቋማት የሚወጡ ባለሙያዎች ከገበያው ስፋትና ከዘርፉ ተፈላጊነት አንጻር ቁጥራቸው ውስን ስለሆነ ተጽዕኖ መፍጠር አይችሉም።

የፋሽን ኢንዱስትሪው የሚያበረክተው ታላቅ አስተጽዖ የገባቸው አገራት ለዘርፉ በሰጡት ከፍተኛ ትኩረት ተጠቃሚ ሆነዋል። ከአንድ መቶ ሚሊዮን በላይ ህዝብ ያላት ኢትዮጵያ የፋሽኑ ዘርፍ ላይ ትኩረት አድርጋ ብትሰራ ነገር ግን የፋሽን ውጤቶችን ወደ ውጪ ባትልክ አገራዊ ፍጆታዋን መሸፈን ከቻለች ትልቅ ድል መሆኑንም ዲዛይነር ሜሮን ትጠቁማለች።

ዲዛይነር ሄለን አየነው ‹‹ሄሉ ፋሽን ዲዛይን›› የተሰኘና በዲዛይኒግ ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ ድርጅት አላት። በዚህ ድርጅት ውስጥም ራስዋን ጨምሮ ሶስት ጓደኞችዋ ከደንበኞቻቸው የተቀበሉትን ትዕዛዝ በማዘጋጀት እንዲሁም በአዳዲስ ዲዛይኖች የተዘጋጁ አልባሳትን ለገበያ ያቀርባሉ። ሁለት ዓመታትን ሙያውን በመማር፤ ላለፉት ሶስት ዓመታት ደግሞ በፋሽን ዲዛይን ባለሙያነት የሰራችው ሄለን፤ሙያው ላይ ችግር እንዳለ ትስማማለች። የባለሙያዎችን የብቃት ችግር የፈጠረውም ሙያው ለአገራችን አዲስ በመሆኑ እንደሆነ ታስረዳለች።

በገበያው ላይ ‹‹ዲዛይነር ነን›› ብለው የሚሳተፉ ግለሰቦች ሁሉ ዲዛይነር እንዳልሆኑ የምትገልጸው ሄለን፣ አንድ ሰው ዲዛይነር ለመሰኘት የሚያስፈልገውን ሙያዊ ብቃትና ክህሎት መሆኑን ትገልጻለች። እንዴት አንድ ስፌት ብቻ የሚችል ግለሰብ "ዲዛይነር ነኝ" ብሎ እራሱን ሙያተኛ ያደርጋል? በማለትም ጥያቄ ታነሳለች። ይህም ፈጽሞ ተገቢ እንዳልሆነና የዘርፉን እድገት ወደኋላ እንደሚመልሰው ሙያቸውን አክብረው ለሚሰሩት ባለሙያዎችም እንቅፋት እንደሚፈጥር ታስረዳለች። የፋሽን ዲዛይነር ነኝ ከማለታቸው በፊት ሙያተኞቹ እራሳቸውን በሙያው ላይ ብቁ ማድረግ ይኖርባቸዋል በማለትም አስተያየትዋን ትሰጣለች።

የፋሽን ዲዛይን ሙያ የተሻለ ደረጃ ላይ መድረስ እንዲችል ባለ ሙያዋ ወሳኝ ጉዳዮች ታነሳለች። የመጀመሪያው በሙያው ላይ ተሳታፊ የሆኑ ዲዛይነሮች ለሙያው ክብር መስጠት፣ የፋሽን ዲዛይን ሙያ ዕውቀትና ክህሎት ተላብሶ የሚሰራ መሆኑን መረዳትና የስልጠና ተቋማትንም ማዘመን እንዲሁም የሚቀበሉዋቸውን ተማሪዎች በጥራት አሰልጥነው ማስመረቅ፣ ለዘርፉ መንግስታዊ ትኩረት መስጠት መሆኑን ታስረዳለች።

የሰለጠነና በስነምግባር የታነጸ ሙያተኛ በማፍራት ትልቅ ሚና ያላቸው የፋሽን ዲዛይን ትምህርት ቤቶች ናቸው። እነዚህ ውስን ትምህርት ቤቶች የፋሽን ዲዛይን ትምህርት ደረጃውን በጠበቀና ጥራት ባለው መልኩ መስጠት ይጠበቅባቸዋል። የልብስ ስፌት ሙያ ያላቸው ግለሰቦች ዲዛይነር ነኝ ብለው ወደስራው እንደሚገቡ የምትገልፀው ዲዛይነር ሄለን፣ አንዳንድ የልብስ ስፌት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቻቸውን ሲያሰለጥኑ የልብስ ስፌት ከልብስ ዲዛይኒግ ጋር እጅግ የሰፋ ልዩነት ያለው መሆኑን ለሰልጣኞቻቸው ሊያሳውቁ ይገባልም ትላለች።

የፋሽን ዲዛይን ትምህርት ቤቶች መስፋፋት ለሙያው እድገትና መሻሻል ወሳኝ ጉዳይ ነው። ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ጨምሮ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ የመንግስትና የግል ተቋማት ላይ በዘርፉ ትምህርትና ስልጠናዎች ይሰጣሉ። ነገር ግን በተለይ የግል የፋሽን ዲዛይን ትምህርት ቤቶች ትምህርት በጥራት መስጠት ላይ ችግር እንደሚታይባቸው ባለሙያዎቹ ይስማማሉ።

# ማረፊያ

## መውደዳችን የቱጋ ነው ድንበሩ

**አቤል ገ/ኪዳን**

ብዙውን ጊዜ የብዙዎቻችን የውዴታም ሆነ የጥላቻችን ድንበር የቱጋር እንደሆነ አይታወቅም። ስንወድ ገድብ የለንም ፤ ስንጠላም እንደዛው። ስንወድ ከመላእክት መለስ አርገን ትንንሽ ማልአክት አድርገን እንስላለን ፤ ስንጠላ ደግሞ ከሰይጣንም የከፋ አድርገን እናስቀምጣለን። ስንወድ ከነግሳንግሱ ነው ፤ ስንጠላ ደግሞ ስንጥር የምታህል ጥፋትን እንኳን ከተራራ እናገዝፋለን። ስንወድ የሰውየውን የግል ህይወቱን እንኳ አናስቀርለትም ፤ ጠቅልለን እንወደዋለን። ስንጠላ ደግሞ የግል ጉዳዩ ነው የሚባል ነገር ሳይቀረን ሰውየውን ከነ ቤተሰቡ ከነ ዘመድ አዝማዱ አብረን እንጠላለን ፤ እንዘልፋለን። ይሄ በጣም አደገኛ ባህል ነው። ፍቅርም ሆነ ጥላቻ ከመስመራቸው ሲያልፉ የጥፋት ምንጭ ይሆናሉ።

ይህን ያልኩት ሰሞኑን ከተወዳጇ ድምጻዊት እጅጋየሁ ሽባባው ፎቶ ጋር በተያያዘ በተነሳው ውዝግብ ነው። በፎቶው ላይ ጂጂ በባቡር ውስጥ ሆና ትታያለች። ፎቶው ያለ እሷ ፈቃድ እንደተነሳ መናገር ይቻላል። ፎቶው ከመቅጽበት ፌስቡክን አጥለቀለቀው። በመጀመሪያ ብዙዎች ለድምጻዊቷ ያላቸውን አድናቆት እና ፍቅር ለመግለጽ ተጠቀሙበት። በኋላ ላይ ግን እንዴት የድምጻዊቷን ያለፍቃዷ የተነሳ ፎቶ ትለጥፋላችሁ የሚል ክርክር መጣ። ቀጥሎ ደግሞ ዝነኛ ሰው ስለሆነች ፎቶዋ መለጠፉ ምንም ችግር የለውም ፤ ደግሞም የዝነኛ ሰውን ምስል ለመውሰድ ፈቃድ አያስፈልግም የሚል ክርክር ተከተለው ነገሩ ተባባሰ።

ይህ ክርክር ቀላል ክርክር አይደለም። የህግም ፤ የፍልስፍናም ፤የሞራልም ፤ የባህልም ጥያቄ አለው። የህጉን ጉዳይ የህግ ባለሙያዎች የፍልስፍናውንም ጉዳይ እንደዚያው ባለሙያዎች ይነጋገሩበት። ዛሬ ልንታዘብ የምንወደው የሞራል እና የባህሉን ጉዳይ ነው። መጀመሪያ ከባህሉ ጉዳይ እንነሳ። አንዳንድ ሰዎች ታዋቂ ሰዎችን ፎቶ ማንሳት የተለመደ ነው እንዲያውም ሙብትም ነው ፤ በሌሎች ሀገራት ይህን ስራ የሚሰሩ ፓፓራዚ የሚባሉ ሰዎች ስላሉ ይሄ አዲስ ነገር አይደለም ፤ ስህተትም አይደለም አታካብዱ ሲሉ ተደምጠዋል። ይሄ ስህተት ነው። ሌሎች ሀገራት ስለተደረገ እኛም ሀገር መደረግ አለበት የሚል አመክንዮ አይሰራም። እኛ ከሌሎች ሀገራት ጋር የሚያመሳስለን ብዙ ነገር ቢኖርም የሚለየንም ብዙ ነገር አለ። ከሚለዩን ነገሮች መካከል አንዱ የፎቶ ጉዳይ ነው።

የኛ ህዝብ ፎቶን አክባሪ ነው። በጥንቃቄ ነው ፎቶ የሚነሳው። እንኳን ያለ ፍቃዱ በፈቃዱም ቢሆን እንኳ ፎቶ የሚነሳው ተጨንቆ ተጠብቦ ነው። አሁን አሁን ከስማርት ስልክ መበራከት ጋር ፎቶ የዘወትር ተግባር ሆነ እንጂ ድሮ ድሮ ፎቶ የክት ቀን ጉዳይ ነበር። ይሄ ከምእራቡ አለም ይለየናል። ለእነሱ ፎቶ መነሳት ተራ ጉዳይ ነው። ለዚህ ምክንያታቸው ብዙ ነው። ዋነኛው ጉዳይ ማህበረሰባቸው የተመሰረተው በነጻ አስተሳሰብ መሰረት ላይ በመሆኑ ነው። ይህ ነጻ አስተሳሰብ ሰዎች ራሳቸውን በፈለገው መልኩ እንዲገልጹ እድል ይሰጣል ፤ በሀሳብ ነጻነት ላይ ገደብ አያበጅም ፤ ለሚዲያ ነጻነት ሰፊ ቦታ አለው ወዘተ..። ይህ ከኛ በጣም ይለያል።

አንተ እንደፈለግክ እንድትሆን በሚለቅህ ፤ ሚዲያውም እስከቻለው መጠን እንዲበረብርህ በሚፈቅድ ስርአት ውስጥ የሚኖር ማህበረሰብን ተሞክሮ ለግለሰባዊ ነጻነት ጠንካራ አጥር ላበጀ እና የዳበረ ሚዲያ ለሌለበት ማህበረሰብ ለመጠቀም መሞከር አዋጭ አይደለም። በሌላ መልኩ እነሱ ጋር የተሰራበት ነገር በሙሉ አዋጭ አለመሆኑን ለማየት የልእልት ዲያናን ታሪክ ማስታወስ በቂ ነው። ለዲያና ሞት ዋነኛ መንስኤ ከሆኑት ነገሮች አንዱ እና ዋነኛው ፓሪስ ላይ ከፓፓራዚዎች ለመሸሽ ስታደርገው የነበረው ትግል ነው። የብዙ የምእራቡ አለም ዝነኞች ህይወት መበጥበጥ መንስኤው አላስፈለጊ የሚዲያ እይታ ነው። ስለዚህም ድርጊቱ መደረጉን ብቻ ሳይሆን የድርጊቱን ውጤትም መመልከት ተገቢ ነው።

ከሞራል አንጻር የሞራል ህግ ማጠንጠኛው አንተ ሊደረግብህ የማትፈልገውን ነገር በሌላው ላይ አታድርግ የሚለው ህግ ነው። እኛ ያለ ፈቃዳችን ሌላ ሰው ፎቶ ቢያነሳን እንወዳለን? ያለ ፈቃዳችን የህዝብ አጀንዳ ቢያደርግን ደስ ይለናል? ማናችንስ ብንሆን በማህበራዊ ሚዲያ ፎቶ ስንለጥፍ ከመቶ ፎቶ እኛ ቆንጆ የሆንበትን መርጠን አይደል የምንለጥፈው? ታዲያ እንዴት ነው እኛ በራሳችን ሊሆን የማንፈልገውን ነገር ለማድረግ የምንደፍረው? ይሄ ስህተት ነው።

እንዲያው ይህን የጂጂን ጉዳይ ሰሞነኛ ስለሆነ አነሳነው እንጂ ህዝባችንን በማይመለከተው ነገር ሲታመስ እንዲውል የሚያደርግ ብዙ ነው። የግለሰብ ትዳር ፤ የግለሰብ አለባበስ ፤ የግለሰብ የልደት አከባበር ፤ የግለሰብ የገንዘብ ጉዳይ ወዘተ ሁሉ ሲያነታርከን ነው የሚውለው። መሆን የነበረበት ግን ከዚህ በተቃራኒ ነበር። ብዙ ጊዜ ሊፈጅብን ይገባ የነበረው ማን ምን ለበሰ? ማን ምን በላ? ማን ከማን ጋር ዋለ? ሳይሆን የትኛው ተቋም እየተገነባ ነው ? የትኛው ተቋም እየፈረሰ ነው? የሚለው ነው። እንኳን የአርቲስቶች ቀርቶ ሀገሪቱን የሚመሩ ሰዎች አኳሀን እና ነገረ ስራ አብዝቶ ሊያሳስበን አይገባም። ሊያሳስበን የሚገባው የተቋማት ቁመና ነው። ሁሌም ዜና ሊሆኑ የሚገቡት ተቋማት ናቸው። ምክንያቱም ሀገር የምትቆመው በእነሱ ላይ ስለሆነ ነው። ሀገር ተቋም ከሌላት ግን ውይይታችን ሁሌም የሚሆነው እንዴት ከዚህች እየፈረሰች ካለች ሀገር እንውጣ በሚለው ላይ ነው።

ወደ ቀደመ ጉዳያችን ስንመለስ የምንወዳቸውን ሰዎች ስንወድም ሆነ ስንጠላ በልኩ እናድርገው። የምንወደው ነገር የሚመለከተንን ብቻ ይሁን ፤ የማይመለከተንን ለእነሱ እንተውላቸው። ድምጻዊ ከሆኑ ዜማቸው ፤ ፖለቲከኛ ከሆኑ ውሳኔያቸው ፤ አትሌት ከሆኑ ውጤታቸው ወዘተ ነው የሚመለከተን። ከዚያ ውጭ ያለው ጉዳይ የግል ጉዳያቸው ነውና ለእነሱ እንተውላቸው። ይህ ማለት እንደፈለጉ ይሁኑ ማለት አይደለም። ዝነኛ ናቸውና የእነሱ ውድቀትም ሆነ ስኬት ትርጉም ይኖረዋል። ሆኖም ግን የግል ህይወታቸውን በተመለከተ ሊገዙ የሚገባው ሌላው ሰው በሚመራበት ባህል እና ወግ እንዲሁም በሀገሩ ህግ ነው። መፍትሄው የድምጻዊውን ሙዚቃ እየሰማን ፤ የተዋናዩን ትወና እያየን ፤ነገር ግን ስለ እነሱ የግል ጉዳይ የምንከራከርበትን ጊዜ እና ጉልበት ለሁላችን የጋራ ወደሆኑት ወደ ተቋማት ማዞር አለብን።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

በቁምላቸው አበበ ደማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

# የሳይበር ጦርነት...! ?

**የሳይበር ጥቃት በተደጋጋሚ የሚሰነዘር ቢሆንም መከላከል እንደሚቻል የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ። ሆኖም 99 በመቶ የሚሆኑ ድርጅቶች ለሳይበር ጥቃት የተጋለጡ ናቸው። የሀገራችን ተቋማት ይህን ተጋላጭነታቸው መቀነስ ላይ አበክሮ መስራት ይጠበቅባቸዋል። በተለይ የደህንነት ፣ የፋይናንስ፣ የኤሌክትሪክ ኃይልና የሚዲያ ተቋማት ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል**

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በሀገራችን እየተካሄደ ያለው ጦርነት የመረጃ ፣ የውክልናና የዲፕሎማሲ ጦርነቶችን ያጃመለ የግራጫ ጦርነት ነው ሲሉ ይደመጣሉ። ሰሞነኛው ወቅታዊ የሀገራችን ሁኔታም ይህን የሚያረጋግጥ ነው። አልሻባብና ኦነግ ሸኔ ግንባር ፈጥረው በምስራቁ የሀገራችን ክፍል ተደጋጋሚ ጥቃት እየሰነዘሩ ሲሆን ፤ ሱዳንም ድንበር ጥሳ ወረራ መፈጸሟ የሚዘነጋ አይደለም። ሕወሓትም ቢሆን ከጥፋቱ የመማር ባህሪ ስለሌለው የሰላም ጥረቱን ቅድመ ሁኔታ በመደርደር ሊያንኮላሸው እየጣተነ ነው ። በሀገራችን ላይ እየተነዛ ያለው የመረጃና የዲፕሎማሲ ዘመቻ ጋብ አለ እንጅ አላበራም። ከዚህ ሁሉ ጀርባ ታሪካዊ ጠላታችን ግብጽ አለች። የኤል ጋህድ ፓርቲ መስራችና ሊቀመንበር አብድልአዚዝ ኑር ኢትዮጵያን በማተራመስ ለማዳከም እነ ሕወሓትን መጠቀም ይገባል ሲል በአደባባይ መናገሩ የግብጽ መንግስት ደህንነት በሀገራችን ላይ እየዶለተ ያለውን ሴራ ገላልጦታል። በሀገራችን ላይ እየተቃጣ ያለው የሳይበር ጦርነትም የዚሁ ደባ አካል ነው። በዚያ ሰሞን በኢትዮጵያ ላይ የተከፈተው የመረጃ ጦርነት በሳይበር ደሕንነትና ሌሎች ተቋማት የጋራ ጥረት እየተመከተ መሆኑን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ማስታወቁ ግብጽ መቼም እንደማትተኛልን ያረጋገጠ ሀቅ ነው። በዛሬው መጣጥፌም እዚህ ላይ አተኩራለሁ።

በሀገራችን ጥንታዊ ታሪክ እንደ ግብፅ ተደጋጋሚ ወረራ ፣ ጥቃትና ዘመቻ የከፈተብን ሀገር የለም ። ከዛ ሩቅ ዘመን አንስቶ ግብፅ ተኝታልን አታውቅም ። አንድ ጊዜ በሰሜን ፣ ሌላ ጊዜ በሰሜን ምዕራብና በምስራቅ ። ጊዜ ጦርነት ከፍታብናለች ። ይሁንና በሁሉም ወረራዎች በጀግኖች አባቶቻችን አከርካሪዋን ተመታ ፣ የውርደት ከሏን ተከናንባ ተመልሳለች ። ከቅርብ አመታት ወዲህ ደግሞ በእነ ሻዓብያ፣ ጀብሀ ፣ ወያኔ ፣ ኦነግ ፣ ኦብነግና ሶማሊያ የውክልና ጦርነት ስታደርግብን እንደነበር አይዘነጋም። የባህር በር እንድናጣ በዘር ተከፋፍለን እንድንዳከም ሌት ተቀን ሰርታለች። ድካሟ ከንቱ ሆኖ አልቀረም። እቅዷን አሳክታለች። የባህር በርና ቀይ ባህር ላይ ለእልፍ አእላፍ አመታት የነበረንን ባለቤትነት በእሷ በተቀነባበረ ሴራና ድጋፍ ማጣታችን ምን ያህል በቀጣናው ላይ የነበረንን ተፅዕኖና ጂኦ ፓለቲካዊ ሚዛን እንዳኮሰመነው ለማንም የተሰወረ አይደለም። በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ሳይቀር ለኤርትራ በገፍ የጦር መሳሪያ በማቅረብና ወታደራዊ እገዛ በማድረግ ተሳትፋለች።

ዛሬም በዲፕሎማሲያዊ መተላለፊያ / ኮሪደር / ከከፈተችብን የፈጠራ ክስና ሀገራችንን ከማሳጣት ዘመቻ ጎን ለጎን ፤ ባንዳዎቿን በውክልና በመጠቀም ሀገራችን ለማተራማስ ፣ ወደለየለት የእርስ በርስ ጦርነት ለመክተትና ለመበታተን ከመስራት አልቦዘነችም። በሱዳን ፣ በአልሻባብ ፣ በሕወሓትና በተላላኪዎቹ የውክልና ጦርነት እያካሄደችብን ትገኛለች። የዛሬ ትኩረቴ የሳይበር ጦርነቱ ላይ ስለሆነ ወደእሱ ልመለስ ። የሳይበር ጦርነት በአጭሩ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ እንደ ፋይናንስ ተቋማት ፣ መከላከያ ፣ ደህንነት ፣ ቴሌኮም ያሉ ተቋማትን የበይነ መረብ የመረጃ ስርዓቶችን ከጥቅም ውጭ ማድረግ ነው ። ስለላ ማካሄድም የጦርነቱ አካል ነው። ራሽያ ከዩክሬን ጋር ጦርነት ውስጥ በመግባቷ አኖኒመስ የተባለ የሀክቲቪስቶች ስብስብ በራሽያ ላይ የሳይበር ጦርነት እንዳወጀው ፤ ግብጽም በህቡዕ የሳይበር ጦርነት ከከፈተችብን ከራርማለች።

የኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ቆየት ባለ አንድ መግለጫው ፤ “...መሰረታቸውን ከግብጽ ያደረጉ የመረጃ መረብ ሰርሳሪዎች ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ተቋማት የመረጃ መረብ መዋቅር ላይ ጥቃት ለማድረግ ሞክረው ነበር።...” እንዳለው ተራ ሙከራ ሳይሆን የሳይበር ጦርነት ነው የተከፈተብን። በዋዛ ፈዛዛ ሙከራ በሚል ብቻ የሚታለፍ አይደለም። በሉዓላዊነታችን ፣ በደህንነታችንና በተቋሞቻችን የተቃጣ ጥቃት መሆኑ ሳይቃለል በልኩ ነው መታየት ያለበት። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በአንድ መድረክ በ21ኛው መክዘ ጦርነት የሚካሄድበት ጦርነት በየብስ ፣ በባሕርና በአየር ብቻ ሳይሆን በሳይበርና በስፔስ መሆኑን ጠቆም አርገው ነበር።

በebs የ” Tech Talk With Solomon “ አዘጋጅ ሰለሞን ሙሉጌታ ካሳ” ግርምተ ሳይቴክ “ በሚል ርዕስ በ2010 ዓ.ም ለንባብ ባበቃው መፅሐፍ ፤ “ የማይታየዉ ጦርነት “ በሚል ምዕራፍ ስር ገፅ 157 ላይ ፤ “...በ21ኛው ክፍለ ዘመን አዲስ አይነት ጦርነት ብቅ ብሏል ። ጦርነቱ የሚካሄደው በጥይትና በቦንብ ሳይሆን በሀከሮችና በኮምፒውተሮች ነው።... ይህ በአይን የማይታየው የሳይበር ጦርነት/ ዋርፌር / ነው። “ ሲል የጠቅላይ ሚኒስትሩን ሀሳብ ያጠናክራል። እሳቸው ያሉት ነገር እንደ ዋዛ ደረሰና ግብፅን በአየር ፣ በየብስ ስንጠብቃት ፤ ምን አልባት ባልጠበቅነውና ባልተዘጋጀንበት ስስ ብልታቸው ይሆናል ብላ በገመተችው በሳይበር ግንባር ጦርነት ከፍታብናለች ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለርዕያቸውና አርቆ አሳቢነታቸው ምስጋና ይግባቸውና በእሳቸው ሀሳብ አፍላቂነት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ /ኢንሳ/መሰረታቸውን ከግብጽ ያደረጉ የመረጃ መረብ ሰርሳሪዎች በሀገራችን ተቋማት የመረጃ መረብ መዋቅር ላይ ጥቃት ለመሰንዘር ያደረጉትን ሙከራ አክሽፏል።

በኤጀንሲው የወቅቱ መግለጫ መሰረት በሦስት የተለያዩ ቡድኖች አማካይነት የተሞከረው የመረጃ መረብ ጥቃት በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጫናን ለመፍጠር ያነጣጠረ ነበር ። የጥቃቱ ሙከራ ባደረጉት ቡድኖች ላይ አበክሮ ክትትል በማድረጉ በ13 የመንግሥት እና አራት መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ድረ-ገጾችን ኢላማ በማድረግ የተሰነዘሩ ከፍተኛ የመረጃ መረብ የጥቃት ሙከራዎችን በቁጥጥር ስር ማዋል ችሏል ። ኤጀንሲው ኃላፊነቱን ስለተወጣ በዚህ አጋጣሚ እውቅና ልንሰጠው ይገባል ። የመረጃ መረብ ጥቃት ሙከራው የተደረገው ሳይበር ሆሩስ ግሩፕ ፣ አኑቢስ ዶት ሃከር’ እና ሴኪዩሪቲ ባይ ፓስ በተባሉ መረጃ መረብ ሰርሳሪ ቡድኖች ነው ። የጥቃቱ ኢላማ የነበሩት ተቋማት በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የመንግሥት ተቋማት ፣ የደኅንነት መስሪያ ቤቶች እና የግል ድርጅቶች ድረ-ገጽ ላይ መሆኑን ኤጀንሲው በመግለጫው አብራርቷል። ሆኖም ባልተለመደ ሁኔታ በአገሪቱ ባሉ ተቋማት የመረጃ መረብ ላይ ጥቃት ለማድረስ የሞከሩ ቡድኖች በግልፅ ኃላፊነቱን መውሰዳቸው ግብፅ ለሀገራችን ያላትን ንቀትና እብሪት የሚያሳይ ሆኖ አግኝቸዋለሁ ። ሌላው ኤጀንሲዉ የሳይበር ጥቃቱ አላማ ፤ “ በኢትዮጵያ ላይ በሁሉም አቅጣጫ ተጽእኖ ለማሳደር ነዉ፤” የሚለው ግምገማው ጥቃቱን አሳንሶና አቅልሎ ያየው እንዳይመስል እሰጋለሁ ። በቅጡም ሊመዘን ይገባል ።

ምክንያቱም የሳይበር ጥቃቱ ተፅዕኖ ከመፍጠር በላይ ተጠናክሮ የሚቀጥል ጦርነት ነውና ። አስቀድሞ ቅድመ ዝግጅት በማድረጉ የመረጃ መረብ ጥቃቱ ኢላማ በነበሩት ተቋማት ላይ ጉዳት አልደረሰም ። ጥቃቱን ማክሸፍ ባይችል ኖሮ በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ፤ ፖሊቲካዊ እና ሥነ ልቦናዊ ጉዳት ሊያስከትል ይችል እንደነበር ኤጀንሲው መግለጹ የሳይበር ጥቃቱን አደገኝነት አጉልቶ ያሳያል። ቀጣዩ አውደ ውጊያ በሳይበር ግንባር ስለሆነ የጦር እቃውን ታጥቀን ፣ የራስ ቁሩን ደፍተን ፣ ጡሩሩን ለብሰን፣ ጦሩን እየሰበቅን ፣ ዘገሩን እየነቀነቅን ተጠንቅቀን ልንጠብቅ ይገባል ። ከዚህ በኋላ የማይቀርልን እዳ/ ዘ ኒው ኖርማል / ነውና ። ሰሞነኛው የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት መግለጫም ይሄንኑ የሚያረጋገጥ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። ግብጽ የሳይበር ጦርነቱን ቀጥላበታለች።

ለመሆኑ የመረጃ መረብ ጥቃት ሲባል ምን ማለት ነዉ? በሰለሞን ሙሉጌታ ካሳ “ ግርምተ ሳይቴክ “ መፅሐፍ ፤” የማይታየው ጦርነት “ በሚል ምዕራፍ ስር ገፅ 157 ላይ ፤ “... ሚስጥራዊ የሆነና ያልሆነን ዲጂታል መረጃን ከባለቤቱ ፈቃድ ውጭ መስረቅ ፣ ይዘቱን ማበላሸት ፣ ከእነ አካቴው ማጥፋት...” ሲል ይበይንና፤ ታሪካዊ ዳራውን እንዲህ ያብራራል ። “ከሙከራ ላብራቶሪ በዘለለ መልኩ የመጀመሪያው ‘ኤልክ ክሎነር’ የተባለ የግል ኮምፒዩተርን የሚያጠቃ ቫይረስ በ1982 ዓ.ም የ15 አመት ወጣትና የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ በነበረው አሜሪካዊው ሪቻርድ ስክሬንታ ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ በኮምፒዉተር መረጃዎች ያነጣጠረ ‘ሳይበር’ ጥቃት በመንግስታት መካከል ጭምር ሳይቀር የሚካሄድ የሳይበር ጦርነት / ሳይበር ዋር / አሀዱ ብሎ ጀመረ ። በወቅቱ ኢንተርኔት ገና ለሕዝብ ጥቅም ያልዋለበት ጊዜ ስለነበር ወንጀሉ በስፋት አልተስተዋለም ። በ1980ዎቹና 90ዎቹ አጋማሽ ድረስ ጥቃቱ በብዛት ይሰነዘር የነበረው እንደ ‘ ፍሎፒ ዲስክ ‘ እና ‘ ሲዲ ‘ በመሳሰሉ ተንቀሳቃሽ የመረጃ ማስቀመጫ ቁሶች አማካኝነት ቫይረስ ከአንድ ኮምፒዩተር ወደ ሌላ ኮምፒዩተር በማስተላለፍ ነበር ።

በ1990ዎቹ አጋማሽ በኋላ የኢንተርኔት አጠቃቀም እያደገ ሲመጣ ጥቃቱም መልኩን ቀይሮ ብቅ አለ ። በ2003 ዓም ገደማ የሳይበር ወንጀል ፍፁም አዲስ በሆነ መልኩ ድረ ገጾችን የማጥቃት አላማ ይዞ ተነሳ ። ይህ የሆነበት ምክንያት በወቅቱ የኢንተርኔት ‘ኢኮሜርስ ‘ ግብይት ስርዓቱ እየተጧጧፈ በመምጣቱ ነው ። በተለይ የክሬዲት ካርድ ቁጥሮችን በመስረቅ ላይ ያነጣጠረ የሳይበር ወንጀል በ2000ዎቹ ተጧጡፎ ቀጠለ ። ከ2005 እስከ 2007 ዓ.ም ባለው ጊዜ አልበርት ጎንዛሌዝ የተባለ አደገኛ አሜሪካዊ የኮምፒዩተር ሀከርና የሳይበር ወንጀለኛ የተለያዩ ግዙፍ የንግድ ኩባንያዎችን የኮምፒዩተር ሲስተሞችን በማጥቃት ፤ የግለሰቦችን ክሬዲት ካርዶችን ቁጥር በመመንተፍ 45 ነጥብ 7 ሚሊዮን ዶላር ዘርፏል ። ...” ዛሬ የሳይበር ጥቃት ምርጫን ፣ ኢኮኖሚንና ማህበራዊ ግልጋሎትን በማስተጓጎል ውድ ዋጋ እያስከፈለ ይገኛል ።

ከፍ ብዬ የጠቀስሁት ደራሲና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያ በመፅሐፉ ይበልጥ እንዲህ ያብራራዋል ። “...የመረጃ ፍሰቱ አለምን ማጥለቅለቁ ፤ መንግስታትም አሰራራቸውን በኢንተርኔትና በኮምፒዩተር ማድረጋቸው ፤ መሰረተ ልማታቸውን የሚያስተዳድሩት ፤ መረጃዎቻቸውን የሚያስቀምጡት ፤ አገልግሎት የሚሰጡት እንዲሁም ታላላቅ ወታደራዊና የደህንነት መረጃዎችን በዲጂታል መልክ መያዛቸው ለጥቃት አጋልጧቸዋል ። የእንግሊዝ የደህንነት ተቋማት እነ ኤም አይ ፋይፍና ኤም አይ ሲክስ እንዲሁም የአሜሪካው ኤፍ ቢ አይ የሳይበር ጥቃትን ከፍተኛ የጸጥታ ስጋት አርገው ወስደው መስራት ከጀመሩ ውሎ አድሯል ። ... “

እንደ መውጫ

የሳይበር ጥቃት በሚቀጥሉት ጥቂት አመታት እስከ ስድስት ትሪሊዎን ዶላር የሚደርስ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት እንደሚያስከትል ጥናቶች አበክረው ይተነብያሉ። ከአለማቀፍ ሽብርተኝነት ባልተናነሰ የደህንነት ስጋት እስከ መደቀንም ደርሷል ። አለም በሉላዊነት / ግሎባላይዜሽን / እና በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ወደ ትንሽ መንደርነት በተቀየረችበት የሳይበር ጥቃትና ጦርነት ለሀገራችንም ስጋት መሆን ከጀመረ ሰነባብቷል ። በንግድ ባንክ በተደጋጋሚ የተቃጡ ጥቃቶች ፤ የፈተና ስርቆት በተማሪዎች ስነ ልቦና እንዲሁም በጊዜያቸው ላይ ያስከተለው ጉዳት እንዳለ ሆኖ በሀገር ኢኮኖሚ እና በተቋማት አመኔታ ላይ ጥያቄ ማስነሳቱ አልቀረም ።

የሳይበር ጥቃት በተደጋጋሚ የሚሰነዘር ቢሆንም መከላከል እንደሚቻል የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ። ሆኖም 99 በመቶ የሚሆኑ ድርጅቶች ለሳይበር ጥቃት የተጋለጡ ናቸው። የሀገራችን ተቋማት ይህን ተጋላጭነታቸው መቀነስ ላይ አበክሮ መስራት ይጠበቅባቸዋል። በተለይ የደህንነት ፣ የፋይናንስ ፣ የኤሌክትሪክ ኃይልና የሚዲያ ተቋማት ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። የሳይበር ጥቃት ዋና መከላከያ ዘዴ ከጫፍ ጫፍ ሁሉንም ኔት ወርኮች ፣ ተንቀሳቃሽ ስልኮችንና የመረጃ መነሻና መዳረሻዎችንና ክላውዶችን ታሳቢ ያደረገ ተጋላጭነት የመቀነስ ስራ መከወን ነው። ጠንካራ የሳይበር መከላከያ ፣ ጥቃቱን መለየት ላይ ከማተኮር ይልቅ መከላከል ላይ በማተኮር ፣ ጥቃት ሊቃጣባቸው የሚችሉ አሰራሮችን በመከላከል ፣ የመጨረሻውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም እና ስለ ስጋት ምንጮች ወቅታዊ ግንዛቤ መጨበጥ ከዋና ዋናዎቹ የመከላከያ ዘዴዎች የሚጠቀሱ ናቸው።

ግብፅ ለከፈተችብን ተደጋጋሚ ወረራ ጀግኖች አባቶቻችን አይቀጡ ቅጣት ቀጥተው አሳፍረው እንደመለሷት ፤ ለሳይበር ጥቃቷም አስተማሪ የሆነ የመልስ ምት መስጠት ያስፈልጋል። አገልግሎቷ ፣ አሰራሯና የመረጃ አያያዟ ከእኛ በብዙ እጥፍ ዲጅታል ስለሆነ ለመልስ ምቱ የተመቸ ነውና።

ሀገራችን ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ፈጣሪ አብዝቶ ይባርክ ! አሜን።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

## የግብርናው ዘርፍ -በ‹‹ስለኢትዮጵያ›› መድረክ

ስምስም መንግሥቱ




የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በቅርቡ በአዳማ ከተማ ባዘጋጀው ሰባተኛው ስለ ኢትዮጵያ የፎቶግራፍ አውደ ርዕይና የፓናል ውይይት ላይ የመወያያ ርእሰ ጉዳይ ሆኖ በቀረበው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ውስጥ ከተንሸራሸሩት ሀሳቦች የግብርናው ዘርፍ አንዱ ነው፤ የመድረኩ ተሳታፊዎችም ሆነ በመድረኩ የመወያያ ጽሁፍ ያቀረቡት የፕላን ኮሚሽን ሚኒስትር ዶክተር ፍጹም አሰፋ፣የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር እዮብ ተካልኝና ባለሀብቱ አቶ በላይነህ ክንዴ ዘርፉ የነበረበትን፣ አሁን የሚገኝበትን ነባራዊ ሁኔታ እና ቀጣይ አቅጣጫዎችን አስመልክተው ማብራሪያ ሰጥተዋል።

የመድረኩ ተሳታፊዎችም በግብርናው ዘርፍ ላይ አስተያየት ሰጥተዋል፤ ጥያቄዎችንም አንስተዋል። የመድረኩ ተሳታፊ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ አማንይሁን ረዳ እንደተናገሩት፤ የግብርናው ዘርፍ የሥራ ዕድል በመፍጠርና ኑሮን ለማሻሻል፣ ለኢንዱስትሪዎች በቂ የጥሬ ዕቃ ግብአት ለመሆን፣ ለወጭ ንግዱ (ኤክስፖርት) በቂ ምርት በአይነት፣በብዛትና በጥራት ለማቅረብ የሚያስችል ሰፊ ዕድል እንዳለው ይታወቃል። 70 በመቶ የሚሆነው የወጭ ንግድ(ኤክስፖርት) ድርሻ የግብርናው ዘርፍ ሲሆን፣ የአብዛኛው ዜጋ ኑሮም የተመሰረተው በዚሁ ዘርፍ ነው። ህዝብ የመመገብ ድርሻውም ከፍተኛ ነው።

አቶ አማንይሁን በግብርናው ላይ የተሰራው ስራ ግን በቂ አለመሆኑን ይጠቁማሉ። ግብርናው በኢኮኖሚው ውስጥ እንዲያመጣ ከሚፈለገው ተልዕኮ አንጻር ሥርነቀል ለውጥ ተግባር መከናወን አለበት የሚል እምነት እንደሌላቸው ነው ሀሳብ የሰጡት።

መንግሥት ለገጠር ልማትና ለግብርናው የሚመድበው በጀትም በቂ ነው የሚል እምነት የላቸውም። አርሶ አደሩና በዘርፉ የሚሰማራው ባለሀብት የመሬት ባለመብት እንዲሆን አለመደረጉም በመንግሥት ቁርጠኝነት ላይ ጥያቄ እንደሚያስነሳም በመጠይቅ ይጠይቃሉ።

አቶ አማንይሁን ከሀገራዊ ለውጡ በኋላ መንግሥት በዘርፉ ያከናወናቸውንም ተግባራት አድንቀዋል። መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ እያከናወነ ባለው የኩታገጠም እርሻን በይሁንታ ያነሳሉ፤ በዚህ አሰራር በዘርፉ ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለመቅረፍ ጥረት እያደረገና እንቅስቃሴውም ውጤት እያስገኘ መሆኑን መገንዘባቸውን ይገልጻሉ። መንግሥት ከዚህም በላይ በመስራት ዘርፉ ሥርነቀል ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ እንዳለበት ይጠቁማሉ።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው እንደሚሉት፤ የግብርና ዘርፉ ለሀገር ዘርፈብዙ ጠቀሜታ እያስገኘ ቢሆንም፣ በመንግስት በኩል የሚደረግለት የፋይናንስ ድጋፍ አናሳ ነው። መንግሥት ለዘርፉ የሚሰጠው በጀትም ከፍ ማለት ይኖርበታል፤ ባንኮች ለዘርፉ የሚሰጡት የብድር መጠን ዘርፉ ከሚሰጠው ጥቅም አንጻር አነስተኛ ነው። በግብርናው ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚለቀቅ ገንዘብ መኖር አለበት። ለዘርፉ በብድር የሚሰጠው የወለድ መጠንም ቅናሽ እንዲኖረው ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል።

አቶ አማንይሁን፤በምግብ እህል ራስን መቻል የሉዓላዊነት ጉዳይ ተደርጎ መወሰድ እንዳለበት ያስገነዝባሉ። ኢትዮጵያን ማሳደግ ማለት የአርሶ አደሩንና የአርብቶ አደሩን ኑሮ መቀየር እንደሆነም በመጥቀስ፣ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ የኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ መሆን እንዳለባቸው ያስገነዝባሉ። ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪው ዘርፍ ተወዳድራ ልታመጣ ከምትችለው ውጤት በላይ በግብርናው ዘርፍ ማሸነፍ የምትችልበት ዕድል መኖሩን በመጥቀስም፣ በግብርና ምርታማነት ላይ መስራቱ አዋጭ እንደሆነ አመልክተዋል።

ህዝብን ለመመገብ የሚያስችል ምርታማነት እንዲኖርም የሥነህዝብ ጉዳይ ሊታሰብበት እንደሚገባም ነው የጠቆሙት። ባለፉት አራት አመታት የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት ከ11 ሚሊየን በላይ መጨመሩን ጠቅሰው፣ ይህ አሀዝ የስዊድን ህዝብ ብዛት ወይንም የቦትስዋናን ህዝብ አራት እጥፍ እንደሆነም ያብራራሉ። የህዝብ ዕድገቱ ካለው የተፈጥሮ ሀብትና የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር እንዲመጣጠን ማድረግ እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል።

ሌላው የመድረኩ ተሳታፊ የቡናና ሻይ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ አዱኛ ደበላ፤በልማት ውስጥ ምርትና ምርታማነት መጨመር አንዱ ተልዕኮ መሆኑን ጠቅሰው፤ የተመረተውን ተደራሽ ማድረግ ላይ በስርአት የመመራት ክፍተት እንደነበር አንስተዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ ለአብነትም በቡናው ዘርፍ የሚስተዋለውን ክፍተት አንስተዋል። የምርት አቅርቦት ብቻ ሳይሆን፣ወቅቱን በጠበቀ ሁኔታ ምርቱን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ከዘርፉ ለመጠቀም ያለው አሰራር ምቹ እንዳልነበር ጠቅሰው፣ የወጭ ንግድ ገቢ ላይ የተሻለ እድገት እንዳይኖር ተጽዕኖ አሳርፎ እንደነበር ያስታውሳሉ።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ በባለስልጣኑ በተወሰዱ የመዋቅርና የማሻሻያ እርምጃዎች ለውጭ ገበያ ይቀርብ የነበረውን ቡና ከሁለት መቶ ሺ ቶን አሁን ወደ ሶስት መቶ ሺ ቶን ማሳደግ ተችሏል። በቡና ላይ የተወሰደው የማሻሻያ እርምጃ ያስገኘውን ለውጥ በሌሎች የግብርና ውጤቶች ላይ በተሞክሮ በመጠቀም ተጠቃሚነትን ማሳደግ ይቻላል። የነበረው የፖሊሲ አቅጣጫም የተወሰኑት ብቻ ተዋናይ እንዲሆኑ ያደርግ እንደነበርም አስታውሰዋል።

ከመድረኩ ተሳታፊዎች ከቀረቡት ሀሳቦች አንዱ የሰው ሀብት አጠቃቀም ነው። በግብርና ሥራው ላይ ያለው ኃይል በዕድሜ የገፋው ብቻ እየቀረ፤ወጣቱ ከገጠር እየወጣ እንደሆነ የታዘቡ አስተያየት ሰጪ ጉዳዩ ተፈትሾ ከወዲሁ እልባት እንዲያገኝ ካልተደረገ በምርትና ምርታማነት ዕድገት ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድር ያላቸውን ስጋት ጠቁመዋል።

ያለፈው ሥርአት የግብርና መር ፖሊሲ የግብርናውን እንቅስቃሴ እንደ ጎዳውም ተጠቁሟል። አስተያየት ሰጪዎቹ፤ ፖሊሲው በሀገር ውስጥ የስንዴ ልማትን እያዳከመ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባውን ምርትና አገልግሎት ነበር የሚያበረታታው። በሀገር ውስጥ የቅባት እህል በየአካባቢው ይመረት የነበረውን የምግብ ዘይት በውጭ ምርት እንዲተካ ተደርጎ አቅርቦቱ በውጭ ላይ ብቻ እንዲገደብ ሆኗል። በአጠቃላይ በሀገር ላይ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወጭን በማስከተል ሀገርን በመጉዳት ተጽዕኖ አሳድሯል ሲሉ የፖሊሲውን ድክመት አመልክተዋል።

በመድረኩ ላይ ጽሁፍ ያቀረቡት የምግብ ዘይት በማምረት፣ የቅባት እህሎችን ወደ ውጭ በመላክ በአጠቃላይ ሰባት በሚሆኑ የኢንቨስትምት ዘርፎች ላይ በመሰማራት ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽኦ እያደረጉ ያሉት ባለሀብቱ አቶ በላይነህ ክንዴ ፣ ኢትዮጵያ ምቹ የአየር ፀባይ፣ሰፊ መሬት እያላት ግን በግብርናው ዘርፍ ትልቅ የሚባል ለውጥ አለማስመዝገቧንና በዚህም እንደሚቆጩ ገልጸዋል።

ባለሀብቱ በአነስተኛ ነገር ላይ በመጠመድ የሀገር ኢኮኖሚን የሚያሳድግ የግብርና ሥራ ተዘንግቷል ይላሉ። የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ሊለውጥ የሚችለው ግብርና እንደሆነም ጠቅሰዋል።

እርሳቸው እንዳሉት፤ መንግሥት ጥሩ የሚያሰራ ፖሊሲ ቢቀርጽም፣ ወደ መሬት አውርዶ መተግበሩ ላይ ብዙ ይቀራል። በሰሊጥ፣በቡና፣በሰብልና በሌሎችም የግብርና ዘርፎች በማልማት ላይ የተሰማራው ባለሀብት በየተሰማራበት ተደራጅቶ በመስራት መንግሥትን ማገዝ ይኖርበታል። አርሶ አደሩም ጠንክሮ እንዲሰራ ጉልበትና መሬት እንዲገናኝ ማድረግ ይገባል።

ቤንችማጂ ዞን እርሻ እንዳላቸው የጠቀሱት ባለሀብቱ፣ በቀን ከምግብ አቅርቦት በተጨማሪ አንድ መቶ ብር እየከፈሉ እንደሚያሰሩ ይናገራሉ። በተቃራኒው ከተማ ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሥራ አጥ መኖሩ ግራ የሚያጋባ እንደሆነም ይገልጻሉ። የሥራ ባህል መለወጥ እንዳለበት ያስገነዘቡት አቶ በላይነህ፣ የፌስቡክ አስተሳሰብ ወደ ልማት መቀየር አለበት ሲሉ ምክረሀሳብ ሰጥተዋል።

ከመድረኩ ተሳታፊዎች በአስተያየትና በጥያቄ በተነሱት ነጥቦች ላይ የፕላን ሚኒስትር ዶክተር ፍጹም አሰፋ በሰጡት ማብራሪያ፤ በለውጥ ሂደት ውስጥ በእቅድ የተያዙትን ነገሮች ከግብ ለማድረስ ተግዳሮቶች እንደሚያጋጥሙ ጠቅሰዋል። በታሰበው ልክ በጥራትና በፍጥነት ለማሳካት የማያስችሉ ነገሮች እንደሚያጋጥሙ ታሳቢ መደረግ እንዳለበት ገልጸው፣ ስለግብርና የተሰጠውን አስተያየትና በጥያቄ የቀረቡትንም እንደሚጋሩ ነው የተናገሩት።

እርሳቸው እንዳሉት፤ እንደ ሀገር በግብርናው ላይ ለመሥራት የሚያስችል አቅም አለ። የግብርናው ዘርፍ በትንሽ የትኩረት አቅጣጫ ብዙ የሚሰጥ ወይንም ብዙ የሚገኝበት ነው። ግብርና ላይ ኢንቨስት የሚደረገው አንድ በመቶ ድህነትን በእጅጉ ለመቀነስ ይጠቅማል። እንደ ኢትዮጵያ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኝ ህዝብ ለሚኖርባት ሀገር ግብርናው ድህነትን ለመቀነስ በእጅጉ አጋዥ ነው።

እንደ ሀገር ባለፉት አራት አመታት በዘርፉ በተከናወኑት ተግባራት ከነጉድለቱም ቢሆን ለውጥ ያስገኙ ውጤቶችን ማስመዝገብ ተችሏል ያሉት ሚኒስትሯ፣ ለእዚህ በአብነትም ግብርናውን በፋይናንስ ለመደገፍ የተደረገውን ጥረት ጠቅሰዋል። የመስኖ ልማትን ጨምሮ ለዘርፉ የተመደበው በጀት ከቀደመው ከ175 በመቶ በላይ ጭማሪ እንዳለውና ይሄም ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት አንዱ ማሳያ መሆኑን ያብራራሉ። በትኩረቱ ልክም ግብርናው ውጤታማ እያደረገን ነው ይላሉ።

በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ያ ሁሉ ጦርነት ተገብቶም፣ የሰሜኑ ክፍል በተለይም የትግራይ ክልል ከማምረት ሥራ ተስተጓጉሎም በዘርፉ የምርት መጨመርን ማየት በራሱ ግብ ሆኖ ሊወሰድ ይገባል ነው ያሉት።

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ ግብርናውን ለማዘመን የሚረዱ ለመካናይዜሽን የሚያግዙ እንደ ትራክተር እና የውሃ መሳቢያ(ፓምፕ) ያሉ የግብርና መሳሪያዎች ከውጭ በግዥ ሲገቡ ከቀረጥ ነፃ እንዲሆኑ መንግሥት ድጋፍ አድርጓል። ይህም ትልቅ የመንግሥት የፖሊሲ ውሳኔ ተደርጎ ይወሰዳል።

ከአነስተኛ መሳሪያዎች ጀምሮ ከቀረጥ ነፃ በገቡ የሜካናይዜሽን መሳሪያዎች በመጠቀም 30 በመቶ በላይ የሚሆነውን የእርሻ መሬት ለማረስ ተችሏል። በአሁኑ ጊዜም በሀገሪቱ በቁጥር ከስድስት ሺ በላይ ትራክተሮች ይገኛሉ። ይሄ በሀገሪቱ የግብርና ሥራ ታሪክ በተለይም ባለፉት አራት አመታት ጊዜ ውስጥ ያለውን ለውጥ ብቻ በማየት ውጤቱን መገምገም ይቻላል ሲሉ አብራርተዋል።

የውሃ መሳቢያ (ፓምፕ) በመጠቀም በአነስተኛ የግብርና ሥራ ውጤታማ የሆኑ አርሶአደሮች መኖራቸውን የጠቀሱት ዶክተር ፍጹም፣ ፓምፕ ላይ ኢንቨስት ማድረግ ትላልቅ የመስኖ ግድብ መሥራት ሳያስፈልግ በፓምፕ ከወንዞች ውሃ በመጥለፍ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚቻልበት ዕድል መፍጠር እንደሚቻልና ይህም እየሆነ መሆኑን ነው ያስታወቁት። በአሁኑ ጊዜ በጸሀይ ሀይል የሚሰሩ ከ20ሺ በላይ ፓምፖች ጥቅም ላይ መዋላቸውን ገልጸው፣ በጸሀይ ሃይል መስራታቸው በኃይል አጠቃቀም ላይም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው ሆኖ መገኘቱንም ጠቅሰዋል።

ሚኒስትሯ በኩታገጠም የአስተራረስ ዘዴ፣ የግብአት አቅርቦትና ሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮች ላይም መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ነው የተናገሩት። ይህም ለምርትና ምርታማነት መጨመር አስተዋጽኦ ማድረጉን አመልክተዋል። በኩታገጠም የማረስ ዘዴ የኦሮሚያ ክልል ብቻ 75 በመቶ በላይ ለመጠቀም መቻሉንና ይህም ከፍተኛ እመርታ እንደሆነ በማሳያነት አቅርበዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ማብራሪያ፤ የመሬት ፖሊሲ ጉዳይ ብዙ የሚያከራክር ቢሆንም፣ በዚህ ረገድም ተሰርቷል። መሬት የኢኮኖሚ መሳሪያ መሆን ካልቻለ፤የፖለቲካ መሳሪያ ብቻ ሆኖ እንዲያገለግል ከተደረገ ውጤት ሊያመጣ አይችልም። የመሬት ፖሊሲ ጉዳይ የሚያነጋግር ጉዳይ መሆኑ እንዳለ ሆኖ መሬትን የኢኮኖሚ መሳሪያ ለማድረግ ባለፉት አመታት ብዙ ርቀት ተሄዶ ተሰርቷል።

ለዚህም አርሶ አደሩ የመሬት ሰርተፍኬት (የምስክር ወረቀት) ማረጋገጫ እንዲኖረው በማድረግ የተሰራውን ሥራ ሚኒስትሯ ለአብነት ጠቅሰዋል። አርሶ አደሩ የማረጋገጫ ሰርተፍኬቱን በማስያዝ የባንክ ብድር እንዲያገኝ መቻሉ የፋይናንስ ችግሩ እንዲፈታለት ዕድል እንደሰጠውም ነው ያስረዱት።

60 በመቶ የሆነውን ከ30 አመት በታች ያለውን ወጣቱን ኃይል እንዴት የልማትና የእድገት ሚና እንዲኖረው ማድረግ እንደሚቻልም በፖሊሲ ለመመለስ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አመልክተዋል።

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታው ዶክተር እዮብ ተካልኝ፤ ስለግብርና ከንግግር ባለፈ ተግባራዊ ሥራ ውስጥ ተገብቷል ማለት እንደሚቻልና እየተገኘ ያለው ውጤትም በተለያየ መልኩ እንደሚገለጽ ነው የተናገሩት። ለበጋ መስኖ ልማት የተሰጠውን ትኩረት በመጥቀስም አነስተኛ የመስኖ ልማቶች ጭምር መንግሥት የፋይናንስ ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ጠቁመዋል። በተለይም በአነስተኛ የመስኖ ልማት ላይ የሚሰሩ ክልሎች እንዲበረታቱ እየተደረገ መሆኑን አመልክተዋል።ክልሎቹ የመስኖ ልማት ጥቅሙ ይበልጥ እንዲገባቸው እየተሰራ መሆኑንም ጠቅሰዋል። መንግሥት ለተሸከርካሪዎች ለሚውል ነዳጅ ያደርግ የነበረውን ድጎማ ወደ ግብርናው እንዲዞር ያደረገውንም ሌላው ማሳያ ነው እንደሆነም ዶክተር እዮብ ጠቅሰዋል።

# የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ግስጋሴ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**



ፎቶ፡ ኢዮብ ተፈሪ

**ዶክተር ቶላ** በሪሶ

እንደ አገር የትምህርት ተደራሽነቱ የሰፋ ቢሆንም የጥራቱ ጉዳይ ግን ሁሉንም የሚያነጋግርና የሚያሳስብ ከሆነ ሰነባብቷል። ከዚህ ጋር ተያይዞም ችግሩን የተረዳው የትምህርት ሚኒስቴር የተለያዩ ሥራዎችን እየከወነ ነው። ከእነዚህ መካከልም የአመራር ለውጥ ላይ መሥራትና ጥራት ያለው ትምህርትቤት መገንባት አንዱ ሲሆን፤ እንደ ክልል ተልእኮው ተሰጥቶ እየተከወነም ይገኛል። እኛም ለዛሬ ለትምህርት ጥራት አጋዥ የሆነውን ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት ቤት በመገንባት በብዛት ሲያስመርቅ ያየነውን የኦሮምያ ክልልን በመምረጥ ምን ምን ተግባራት እየተከወኑ እንዳሉ ለመዳሰስ ሞክረናል። በጉዳዩ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡን የክልሉን ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ቶላ በሪሶን የጋበዝን ሲሆን፤ ያደረግነውን ቆይታም እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

**አዲስ ዘመን፡- በኦሮሚያ ክልል ያለው የመማር ማስተማር አጠቃላይ ገጽታ ምን ይመስላል?**

**ዶክተር ቶላ፡-** አጠቃላይ ገጽታውን ለመግለጽ መጀመሪያ ቀደም ሲል የነበረውን ተግባርና እንቅስቃሴ ማንሳት ያስፈልጋል። በተለይ የለውጥ አመራሩ በ2010 ዓ.ም ከገባ በኋላ ምን ለውጦችን እያመጣ ሄደ የሚለውን መዳሰስ ግድ ይሆናል። ለዚህ ደግሞ መነሻ የሚሆነው አመራሩ ሲመጣ መጀመሪያ ምን ሰራ የሚለው ነው። እናም ለዚህ ጥያቄ ምላሽ የሚሆነው የቀደሙ ችግሮችን ለማወቅ ጥናት ያደረገ ሲሆን፤ ይህ ጥናትም የኦሮምያ ክልል የትምህርት ችግሮች በብዛት ያሳየና ለመፍትሄው ያነሳሳ ነው። ዋና ዋና የተባሉ ችግሮችን እንድንፈታ የሆንበትም ነው ተብሎ መወሰድ ይችላል።

ከችግሮቹ በመነሳት ከአመራር ለውጥ ጀምሮ ሥራዎች ተከናውነዋል። የመምህራንና የተማሪዎች ችግርም በስፋት ታይተው መፍትሄ የሚያገኙበት ሁኔታ ውስጥም ተገብቷል። ይህ ሥራ ሲሰራም የክፍል ደረጃን ጭምር በለየ መልኩ ነው። ማለትም ከቅድመ መደበኛ ጀምሮ እስከ መሰናዶ ድረስ ያሉት እንዲሁም ልዩ ትምህርትቤቶችና አዳሪ ትምህርትቤቶች ተቃኝተውበታል። በዚህም እንደ ክልል ብዙ ለውጦች የመጡበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

**አዲስ ዘመን፡-የትምህር ጥራትን ለማሻሻል እንደ ክልል ምን አይነት ተግባራት እየተከናወኑ ናቸው?**

**ዶክተር ቶላ፡-** የትምህርት ችግር ሰው አይቶ የሚረዳው አይደለም። እጅግ ውስብስብና ጥልቅ ነው። እናም ችግሮቹን ለመፍታት ጊዜና በጀት እንዲሁም የአመራር ጥበብን ይጠይቃል። በዚህም በዋናነት አራት ተግባራትን ለመከወን እቅድ ይዘን ወደ ተግባሩ ገብተናል። ለዚህ ደግሞ በጀት ዋነኛ ጉዳይ በመሆኑ 65 ቢሊዬን ብር እንደሚያስፈልገንም በጥናት አረጋግጠንም ነው የገባነው። ነገር ግን በወቅቱ ክልሉ እንኳን የተመደበለት በጀት 54 ቢሊዬን ነበር። ስለዚህም ለእኛ 65 ቢሊዮን ብር ሊመድብ አይችልም።በመሆኑም ስፋት ያላቸው ሥራዎችን ለማከናወን ሌላ አቅጣጫ መከተል ግድ መሆኑን አምነን በሁለት መንገድ ተግባሩ እንዲከናወን ሆኗል። በመንግስት አቅምና በማህበረሰቡ እገዛ።

የመጀመሪያ ትኩረት ያደረግነው ሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገቡ ተማሪዎች ላይ ሲሆን፤ በቁጥርም ሆነ በውጤት አናሳ ናቸውና ለምን ሆነ የሚል ጥያቄ ይዘን ተነሳን። ታችኛው ክፍል ላይ 10 ሚሊዬን የሚሆን ተማሪዎች አሉ። ሆኖም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪው ቢበዛ ሁለቱን ሚሊዬን ብቻ ነው የሚሸፍነው። ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ ተማሪዎች አንድ ሶስተኛውን የሚይዘው ክልል ኦሮምያ ነው። ነገር ግን በክልሉ የሚመዘገበው ከፍተኛ ውጤት በተለይ በሁለተኛ ደረጃ ላይ ከዘጠኝ አይበልጡም። ዩኒቨርሲቲ የሚገቡትም ጥቂቶች ናቸው። ስለዚህም ተማሪዎችን በጥራት ለማስተማር ጥራት ያላቸውን ትምህርትቤቶች መገንባት አንዱ የመፍትሄ መንገድ በመሆኑ ወደ ሥራ ለመግባት ችለናል። የትምህርትቤቶች ምቹ አለመሆንም እንዲሁ ተማሪዎች ውጤታማ እንዳይሆኑ የሚያደርጋቸው ነውና ይህንን ለመቀየርም ብዙ ተግባራት ተከናውነዋል። ለአብነት ብዙ የዳስ ትምህርትቤቶችን ወደ ትምህርትቤት መቀየርና የክፍል ተማሪ ጥምርታውን ማሻሻል አንዱ ነበርም።

ሌላው በጥናት የተለየው ችግር ከአንደኛ እስከ አምስተኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ጉዳይ ሲሆን፤ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ነበሩ። ለዚህ ደግሞ መንስኤው የቅድመ መደበኛ ትምህርትቤቶች በክልሉ ላይ አለመኖራቸው ነበር። ቢኖሩም በግል የሚሰሩ እንጂ በመንግስት የሚተዳደሩ አይደሉምና አቅም ለሌለው ሰው አይሆኑም። በዚያ ላይ በፖሊሲም አልተደገፈም። እናም ይህንን በመፍታትም በኩል ትልልቅ የሚባሉ ተግባራት ተከውነዋል።

ሌላው የተለየው መምህራን ላይ የነበረው ችግር ሲሆን፤ በወቅቱ 13 ኮሌጆች ቢኖሩም በማሰልጠኛዎቹ ውስጥ መምህራን ተገቢውን ስልጠና ሳያገኙ ይወጣሉ። ይህ ደግሞ መማር ማስተማሩን በእጅጉ ሲጎዳው የቆየ ጉዳይ ሆነዋል። በጣም ብዙ ቁጥር ያላቸው መምህራንን በኤክስቴንሽን ጭምር በማስገባት ይማራሉ ።ብቃታቸው ግን እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም። እንደውም ሲኦሲ ሲፈተኑ እንኳን የሚያልፉት በጣት የሚቆጠሩ ናቸው። ስለዚህም ኤክስቴንሽን የሚባል ነገር እንዲቆምና መምህራንም ወደ ስልጠና ተቋሙ ሲገቡ በብቃት ተለይተው መሆን እንዳለበት ተወስኖ ወደሥራ ተገብቷል። በዚህም 90 በመቶው ሲኦሲ እንዲያልፉ አድርጓል። ጥራት ያለው የመማር ማስተማር ሥራም ተፈጥሯል።

ትምህርት የጀመሩትን ምንም ማድረግ ስለማይቻል በተሸለ አካሂድ እየተመራ እንዲያጠናቅቁና ውጤታማ እንዲሆኑም ተደርጓል። ከሶስት ሺህ በላይ መምህራንም ማስመረቅ የተቻለው በዚህ መንገድ በመኬዱ ነው። አሁንም ቢሆን የቅድመ መደበኛ ትምህርትን የሚያስተምሩ ስድስት ሺህ መምህራንን በመመልመል እንዲሰለጥኑ እየተደረገ ነው። በተጨማሪ ቅድመ መደበኛ ትምህርትን የሚከታተሉ ተማሪዎች በእድሜም ሆነ በትምህርት ብቃታቸው የተሻሉ ሆነው እንዲወጡ ብዙ ማሻሻያዎች ተደርገዋል። አንዱ ሁለት ዓመት በዚህ እንዲቆዩ መደረጉ ሲሆን፤ ሁለተኛው አምስት ዓመት ሳይሞላቸው መግባት አለመቻላቸው ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከትምህርትቤት ግንባታ ጋር በተያያዘ የሪፎርም ሥራዎችን እያከናወናችሁ እንደሆነ ተሰምቷል። መነሻችሁ ምን ነበረ? ምን ያህሉስ ተገነቡ?**

**ዶክተር ቶላ፡-**ከላይ እንዳልኩት መነሻችን ጥናት ነው። ምን ያህል ያስፈልጋሉ በምን ያህል በጀት የሚለው ነው። በዚህም ለመንግስትና ለህብረተሰቡ ተከፋፍሎ ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶችንና አዳሪ ትምህርትቤቶችን መንግስት እንደሚሰራ የተሰጠ ሲሆን፤ ቅድመ መደበኛውንና ተጨማሪ ትምህርትቤቶችን ደግሞ በሕዝቡ ተሳትፎ የሚሰራበትን መንገድ ፈጥረናል። በዚህም በሕዝብ ተሳትፎ ብቻ ከሦስት ሺህ በላይ ትምህርትቤቶች በዓመት ውስጥ ማጠናቀቅ ችለናል። ለዚህ ደግሞ በሕዝቡ ገንዘብ መዋጮነት የተመሰረተው በኦሮምኛው ተጃጅለ ለሙማ (የዜግነት አገልግሎት) ተሳትፎ ትልቁን ድርሻ የሚወስድ ነበር።

የመጀመሪያ ሙከራ የተካሄደው በተጨማሪ ክፍሎች ላይ ሲሆን፤ 30 ሺህ ትምህርትቤት ለመገንባት አቅደን 34 ሺህ ትምህርትቤቶችን ገንብቶ አስረክቦናል። በተጨማሪም መጻሐፍትን ማሰባሰብና ተማሪዎችን ማገዝ ላይም ትልቅ ሥራ ማከናወንም ተችሎበታል። ለአብነት መጸሀፍ የመጀመሪያ ዓመት 2 ሚሊዬን ቀጣይ ሶስት እያለ እስከ አምስት ሚሊዬን መጻሐፍ መሰብሰብና ማገዝ ተችሏል።

ሕዝቡ ሦስት ሺህ አቅደን ከዚያ በላ የሠራም ነው። ይህም ሰባት ነጥብ አምስት ቢሊዬን ብር ወጪ የተደረገበት ሲሆን፤ በሦስት ዓመት ውስጥ 12ሺህ ያስፈልገናልና ይህንን ለማሳካትም እየተጋ ነው። ስድስት ሺህ በዚህ ክረምት ለማጠናቀቅም እየተሰራ ነው። በመጪው ዓመት ደግሞ የቀረውን 2300 እንደምንጨርስም እምነት አለኝ። አሁን ያለው የወጪ መጠን 30 ቢሊዬን ብር ሲሆን፤ አንዱ የሚሰራው አምስት ቢሊዬን ነው። ይህ ወጪ ግን ለሕዝቡ ከብዶት እንደማያውቅ እያሳየ ነውና ሊመሰገን ይገበዋል።

ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቤትን በተመለከተ ለጨፌው ቀርቦ ውሰኔ ተሰጥቶት 100 ትምህርትቤቶች ተፈቅደው ተጠናቀዋል። ስድስት ቢሊዬን በመመደብም ነው ተግባሩ የተከናወነው። ይህ ሲሆን ደግሞ የትምህርትቤቱን ምቹነት በማምጣትና ለብዙ ዓመት እንዲያገለግል ሆኖ ነው የተገነባው። ለምሳሌ፡- ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ሲገነባ 12 ሄክታር ላይ ማረፍ አለበት የሚል ውሳኔ ተላልፏል። በኋላም ተጨማሪ ክፍል ሲያስፈልግ በዚያው መልኩ የሚሰራ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ደረጃውን የጠበቀ ትምህርትቤት ለመገንባት ጥናት እንደተካሄደ ተሰምቷል። ውጤቶቹ ምን ይመስሉ ነበር? ከተማሪ፣ ከመምህራንና ማህበረሰቡ ጠቀሜታ አንጻርስ ጥናቱ ምን አመጣ?**

**ዶክተር ቶላ፡-**በክልሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤትን ብቻ ብናነሳ ቀደም ሲል 1400 ትምህርትቤቶች ነበሩ። አሁን የተሰሩት ደግሞ 100 ናቸው። ሁለቱን ስናነጻጽር በፊት የነበሩት በብዙ መልኩ ጥራት የላቸውም። እናም በቀላሉ ስለሚፈርሱ ለተማሪም ሆነ ለመምህራኑ ምቹ አይደሉም። የተሟላ ቤተሙከራና ቤተ መፅሐፍት በሌለበት ማስተማርም መሆነ መማር በምንም መልኩ ውጤታማ ሊያደርግ አይችልም። ለሥራም ቢሆን ማራኪነት የላቸውም። በዚያ ላይ እነርሱን ለመገንባት ዓመታት ተቆጥረዋል። እናም የተሻለ እንጂ ከዚህ የወረደ ትምህርቤት እንደማይገነባም ተወስኗል።

100 ትምህርትቤት መሥራት ብዙ ለውጥ ያመጣል ተብሎ አይታሰብም። ሆኖም በርካታ ጥቅሞች እንዳሉት ግን አይካድም። ምክንያቱም ተማሪንና መምህራንን ብቻ ሳይሆን ማህበረሰቡንም ጭምር የሚጠቅም ሆኖ ተገንብቷል። ጥቅሙን ከመነሻው ጀምሮ ብናነሳውም አንዱ የሥራ እድል መፍጠሩ ነው። 150ሺህ ሰው የተጠቀመበት ሆኖ አልፏል። ወደ ሁለት መቶ ሺህ ተማሪን በእነዚህ ትምህርትቤቶች ማካተት ደግሞ ከተማሪው ጥቅም አንጻር ስናየው ዘርፈ ብዙ ጥቅም አለው። አንዱ ረጅም መንገድ ሳይሄዱ የሚፈልጉትን ነገር እያደረጉ እንዲማሩ ማስቻሉ ሲሆን፤ ከተጨማሪ ወጪም ይታደጋቸዋል።

ምቹ የመማር ማስተማር ሥርዓትና አየር መፍጠር በራሱ ትልቅ እድል የሚሰጥም ነው። ምክንያቱም ተማሪም ሆነ መምህራኑ ወደ ትምህርትቤት ሲመጡ ፈልገው እንጂ ተገደው አይሆንም። ደስተኛ ሆነው ጊዜያቸውን በዚያ እንዲያሳልፉም ይሆናሉ። የተሸለ የመወዳደር እድል እንዲኖራቸውም ያደርጋቸዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ከሸኔ የሽብር እነቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የወደሙ ትምህርት ቤቶች ምን ያህል ናቸው ? ከዋና ግባችሁ ባሻገር በጦርነት የወደሙ ትምህርት ቤቶችን መገንባት ላይስ ምን አይነት እንቅስቃሴ እያደረጋችሁ ነው?**

**ዶክተር ቶላ፡-** እንደአገር ችግር ነው ብዬ የማነሳው ጉዳይ መንፈሳዊ ቅናት አለመኖሩን ነው። የአመለካከት ችግር እጅግ በአገር ላይ ሰፍቷል። ከዚህ ካልተወጣም ውድድር ይኖራል ብዬ አላምንም። ምክንያቱም እንደ ክልል ሥራዎች ሲሰሩ ተሞክሮችን ከመቀስም ይልቅ ማጥላላት ይቀድማል። እንደውም አልሙ፤ ከጦርነቱ ባሻገር ሥራ ስሩና አገርን በጋራ እንለውጥ ሲባል ‹‹ያልተነካ ግልግል ያውቃል›› የሚሉም አይጠፉም። ምክንያታቸው ደግሞ ኦሮምያ ምንም አይነት ችግር እያስተናገደች አይደለም የሚለው ነው። ይህ ግን ትክክል እንዳልሆነ ልባቸው ያውቀዋል። በሸኔ ከዓመት እስከዓመት ስቃዩን የሚበላው የኦሮምያ ክልል ነው።

ኦሮምያ ክልል ምንም አይነት መና አልወረደለትም። ክልሉ በራሱ አቅም በጀቱን እንያሳደገ የሚሳራ ነው። አሁንም ይህንኑ ከማድረግ ወደኋላ አይልም። ችግር ከተባለ ኦሮምያ በሚያጎራብታቸው ሁሉ ተፈትኗል። የተፈናቀሉም በጣም በርካታ ናቸው። የሞቱም እንዲሁ። ጉዳያችን ትምህርት በመሆኑ እርሱን ብቻ እንኳን ብናነሳ ከባድ የሚባሉ ፈተናዎችን እንደ ክልል ተጋፍጠን አልፈናል።

በአሁኑ ወቅት ብቻ የወደሙ ትምህርቤቶች ከ1000 በላይ ናቸው። የተዘረፉትም በዚያው ልክ ይሆናሉ። መዝረፍ ካልቻሉ ደግሞ ያቃጠሏቸውም እንዲሁ ቀላል አልነበሩም። እነዚህን መገንባት ደግሞ ግዴታ ነውና በተቻለ መልኩ እየተሰራባቸው ይገኛል። በእርግጥ የፈረሱ ትምህርትቤቶች ግንባታን በሚመለከት ትምህርትሚኒስቴር ወስዷል። ስለዚህም በቢሮው በኩል የሚደረጉ ነገሮች ተማሪዎችን ባሉበት ሁኔታ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ማስቻል ነው። ይህም እየተደረገ ይገኛል። ከስነልቦና ማማከር ሥራ ጀምሮ ተግባራቱ እየተከናወኑም ናቸው። በተጨማሪም በክልሉ ማህበረሰብ ተሳትፎ እንዲኖር ለማድረግ ገንዘብ የማሰባሰቡ ተግባር ቀጥሏል።

ለምሳሌ፡- ከሱማሌ ክልል ብቻ አንድ ሚሊዬን ሰው ተፈናቅሎ ፤ በባሌ በኩልም ከዚህ ተመጣጣኝ የሚሆን ሰው ቤት ንብረቱን ትቶ ክልሉን ችግር ውስጥ ከቶት ነበር። በተመሳሳይ በወለጋ በኩል ደግሞ ከሦስት መቶ ሺህ በላይ ሰው ተፈናቅሏል፤ በጉጂና ጌዲዮ እንዲሁ ያህል ሰው ከቀየው ወጥቷል። እናም እነዚያን የማቋቋምና ተማሪዎቹን የማገዝ ሥራ የቢሮውም ኃላፊነት ስለነበር አድርጎታል። በቀጣይም ብዙ ሥራዎች እንዳሉበት ይታመናል። ቤተሰብ ሳይቀር የሚታገዝበትን መንገድ እየፈጠርን የሸኔን አላማ አክሽፈናል።

ሸኔ በፈጠረው የጸጥታ ችግር ምክንያት ስድስት ትምህርቤቶችን መገንባት አልተቻለም። ለዚህም ማሳያው ምዕራብ ሸዋ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ምዕራብ ወለጋ ናቸው። ይሁን እንጂ ይህም ሆኖ ሥራ አልቆመም። ማንኛውም ችግር መፍትሄ አለው ብለን እናምናለንና በሌሎች አካባቢዎች ተግባራቶቹ ወደፊት እንዲጓዙ አድርገናል። በእቅዱ መሰረትም እየሄዱ ናቸው። ለምሳሌ፡- ሥራው ከመጀመሩ በፊት አምስት ግቦችን ለማሳካት በዕቅድ ተይዞ ተሰርቷል።

እነዚህ እቅዶች የመጀመሪያው በትምህርትቤቶቹ ግንባታ ወቅት 150 ሺህ ወጣቶች የሥራ እድል ያገኛሉ የሚለው ነው። ሌላው ይህ ክልል ገና ብዙ ፕሮጀክት ይሰራል። ለዚህ ደግሞ ብቃት ያላቸውን ኮንትራክተሮች መፍጠር ይገባልና በትምህርት ቤቶች ግንባታ ውስጥ ወጣቶች ሙያ እንዲቀስሙ ተደርጓል። ሦስተኛው አቅም ያለው አማካሪ ድርጅትን መለየትና ለቀጣይ ለመጠቀም ማመቻቸት ሲሆን፤ ይህንንም ማሳካት ተችሏል። አራተኛው አንድን ፕሮጀክት በጥራትና በጊዜ እንዲሁም በተቀመጠው በጀት ማጠናቀቅ መቻል ሲሆን፤ ስኬታማ የሆንበት ተግባር ነበር።

አምስተኛው ለአገልግሎት ብቁ የሆነውን ትምህርትቤት ግብዓቱን አሟልቶ ወደ ሥራ ማስገባት ሲሆን፤ ሁሉም በሚባል ደረጃ ተሟልተው ለ2015 ዝግጁ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ አጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የሚያስተላልፉት መልክት ካለ ?**

**ዶክተር ቶላ፡-** መልእክቶቼ ሁለት ነገሮች ብቻ ናቸው። አንደኛው አወንታዊ ተመልካች እንሁን ፤ የአስተሳሰብ ችግራችንን እንፍታ የሚለው ሲሆን፤ ሁለተኛው በመንፈሳዊ ቅንአት ተመርተን እርስ በእርስ በልማቱ በመወዳደር አገራችንን እናሳድግ የሚለው ነው። ሁሉም ጋር ችግርም መፍትሄም አለና ያንን እያዩ በእኩል መራመድ ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡ ስለሰጡን ማብራሪያ በድርጅቱ ስም እጅግ አድርገን እናመሰግናለን**

**ዶክተር ቶላ፡-** እኔም እንግዳ ስላደረጋችሁኝ አመሰግናለሁ።

# ‹‹በሕዝቡ ውስጥ ያስተዋልነው ነገር ቢኖር ለሰላም ያለውን ጥማት ነው››

**ዶክተር ዮናስ አዳዬ**
**የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር**

አስቴር ኤልያስ

የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከፖለቲካ ወገንተኝነት፣ ከማንኛውም የመንግስት ወይም ሌላ አካል ተጽዕኖ ነጻ የሆነና ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው አካል ነው። ዋና ዓላማውም መሰረታዊ የሆኑ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ያሉ ልዩነቶችን በማጥበብ በተቻለ ሁሉ እርስ በእርስ መግባባት እንዲኖር ማድረግ ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ኮሚሽኑ እስካሁን ስላከናወናቸው አንኳር ጉዳዮችና በ2015 በጀት ዓመት ሊተገብራቸው ስለያዛቸው እቅዶች አስመልክቶ ከሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሰላም ጥናት ተባባሪ ፕሮፌሰር ከዶክተር ዮናስ አዳዬ ጋር ቆይታ አድርገን ያጠናቀርነውን እነሆ ለንባብ ብለናል ።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን የዝግጅት ምዕራፉን አልፎ ወደተግባር እየገባ ይገኛል፤ ስለሆነም ኮሚሽኑ ምን ያህል በእቅዱ መሰረት እየተጓዘ ነው ?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** በጣም ጥሩ፤ ቀደም ሲል የነበረውን ለማስታወስ ያመቸን ዘንድ ዝግጅታችን ትኩረት አድርጎ ሲንቀሳቀስ የነበረው አምስት ምዕራፎችን ይዞ ነው። የመጀመሪያው ቅድመ ዝግጅት የሚባለው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ዝግጅት ነው፤ በሶስተኛ ደረጃ የተያዘው ሒደት ሲሆን፣ አራተኛው ደግሞ ትግበራ ነው። የመጨረሻው ቀደም ሲል የተጠቀሱት መሰራት አለመሰራታቸውን ሊያሳይ የሚችል ክትትልና ግምገማ ነው። ስራችንን የጀመርነው በእነዚህ አምስቱ ምሰሶዎች ስር ነው። በእርግጥ አንዳንዶች እነዚህን አምስቱን ምሰሶዎች ሶስትም እንዲሁም አራትም አድርገው ይከፍሏቸዋል። እንደዛም ማድረግ ይቻላል። እኔ በአገራዊ የምክክር ኮሚሽን በሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዘርፉ በኃላፊነትም፣ በተጠያቂነትም እንዲሁም በተጠሪነቱም ስለምሰራ በዚህ መልኩ የከፋፈልኩት ተግባቦቱ የበለጠ ግልጽ እንዲሆን ብዬ ነው።

በቅድመ ዝግጅቱ የተሰሩ ስራዎች በጥቅሉ ለስራው የተመረጥን አስራ አንዳችን ከተለያየ ቦታ የመጣን እንደመሆናችን የመጀመሪያው እርምጃ እርስ በእርስ መተዋወቅ ነበር። ይህ ጉዳይ በቀላሉ የሚታይ ሳይሆን በጣም ወሳኝና አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል።

እንዲህ ማለቴ የራሱ የሆነ ምክንያት ስላለው ነው። ሌላ ቦታ በአግባቡ ሳይተዋወቁ እንዲህ አይነቱን ስራ ጀምረው ከተለያየ ጎሳ የመጡ በመሆናቸው የመጡበትን አካባቢ አመለካከት፣ የድርጅታቸውን አመለካከት እንዲሁም የኃይማኖትን ርዕዮት ዓለም ከማንጸባረቃቸው የተነሳ ብሔራዊ ፕሮጀክቱ ራሱ የተነሳበትን ግብ ሳያሳካ የቀረበት ሁኔታ እንዳለ የሌሎች አገሮች ተሞክሮዎች ያሳያሉ።

በመሆኑም እንደእሱ አይነት ችግር በአገራችን እንዳይደገም ለማድረግ እርስ በእርስ የመተዋወቁን ጉዳይ በጥሩ ሁኔታ አከናውነናል። ለምሳሌ ከአስራ አንዳችን ውስጥ ማን ምን አይነት ዝንባሌ አለው? ምንስ አይነት የስራ ልምድ አለው? በፋይናንስ አካባቢ እውቀት ያለው ማን ነው? አጋርነት ላይስ መስራት የሚችለው ማን ነው? በዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች ላይ ማን ልምድ አለው? በኮሙኒኬሽንና ሚዲያ ላይ እንዲሁም በሕግ ላይ የተሻለ እውቀት ማን ዘንድ ነው ያለው? በተለያየ ጉዳይ ላይ ማን ምን አለው የሚለውን በአግባቡ ለይተን የተመለከትነው ጉዳይ ነው።

እኔ ለምሳሌ እንግሊዝ አገር ሶስተኛ ዲግሪዬን የሰራሁት በሰላም ጥናት ላይ ነው። ቀደም ሲል ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሳስተምር ነበር። ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመሆንም ዲፕሎማሲ ሳስተምርና ሳሰለጥን ነበር። ስለዚህ የእኔ ዝንባሌ ወደሰላም ግንባታ እንዲሁም ግጭት አፈታት ላይ ስለሆነ እኔ እና አምባሳደር መሃሙድ ድሪር በኮሙኒኬሽንና ሚዲያ ውስጥ ተመድበናል፤ ሌሎችም እንዲሁ በአምስቱ ምሰሶዎች ስር እንደየዝንባሌያቸው ተመድበው ስራቸውን በማከናውን ላይ ይገኛሉ። ይህ ስራችን ደግሞ በጋራ የምንሰራበት እንደኮሚሽን የተሻለ እንዲሆን የሚያስችል ስለሆነ ነው።

በጥቅሉ እርስ በእርስ ከተዋወቅንና እንደየዝንባሌያችን ስራ ከተከፋፈልን በኋላ ምክክር የሚለው አንኳሩ ጉዳይ ምንድን ነው? ምክክር ከሽምግልና፣ ከውይይት፣ ከድርድር፣ ከሙግት እንዲሁም ከዳኝነት የሚለየው በምንድን ነው? የሚለውንና ትንሽ ግር የሚያሰኘውን ጽንሰ ሐሳብ በመረዳት ደረጃ እየተመካከርን ለመማማር ብዙ ጊዜ ወስደናል። በዚህም መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮችን አውቀናል። በሒደት ደግሞ እያወቅንና እየተማርን እንሄዳለን። እኔም በአሁኑ ወቅት ከሰላም ጥናት ጋር በተያያዘ የተባባሪ ፕሮፌሰርነት ደረጃ ላይ እገኛለሁ። በመሆኑም በምክክሩ ጉዳይ ላይ ስንጽፍ ብሎም ስናስተምር ቆይተናል። ሌሎቹም እንደየችሎታቸው እንዲሁ እየሰሩ ነው። ምን ምን አይነት እውቀትና ክህሎት አለው የሚለውን በይበልጥ ለመረዳት መቀራረቡ ጠቅሞናል።

**አዲስ ዘመን፡- ከትውውቁ በኋላ የመጀመሪያ የሆነው ስራ ምን ነበር?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** እርስ በእርስ ከተዋወቅን በኋላ የምንሰራበትን አውድና አገርን ማወቅ ሌላው ጉዳይ እንደመሆኑ ያቀናነው ወደዚያ ጉዳይ ነው። በእርግጥ ኢትዮጵያን ይወክላሉ ያልናቸው በተለይም የኃይማኖት መሪዎችን ምክንያቱም ብዙ ጥናቶች የሚያሳዩት 98 በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድም በሌላ በኩል ኃይማኖተኛ ነው በሚል ነው። በአብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል ዘንድ ፈሪሃ ፈጣሪ እንዳለ እንገነዘባለን። ስለዚህ ሕዝቡን የማወቂያ የመጀመሪያው መንገዳችን ሕዝቡን መወከል የሚችሉ መንፈሳዊ መሪዎችን ማግኘት ነበረብን። ስለሆነም ከመንፈሳዊ መሪዎች፣ ከኃይማኖት አባቶች፣ ከአገር ሽማግሌዎች፣ ከዋቄፈናዎች፣ ከአባገዳዎች፣ ከሰላም እናቶች፣ ከሴቶች ማህበራት ተወካዮች፣ ከወጣት ማህበር ተወካዮች ከሁሉም የኢትዮጵያ ክልል በሚያስብል ደረጃ የመጀመሪያ ስራችን አድርገን ከእነርሱ ጋር መተዋወቅ ነበረብንና ከእነርሱ ጋር ተዋወቅን። መተዋወቅ ብቻም ሳይሆን እነርሱም ከእኛ ጋር እንደሚሰሩ ቃል ገብተዋል።

በቀጣዩ ጊዜያችንም ኢትዮጵያን ማወቅ እንደመሆኑ የተለያዩ ተፎካካሪ ፓርቲዎችም እንዲሁም ከገዥው ፓርቲም ጋር ስለአገራችን በመምከርና በመነጋገር እንዲሁም ምክክር ስላስፈለገበትም ምክንያት በአግባቡ በመወያየት እንዴት መደጋገፍ እንዳለብን ስንመካከር ነበር። በዚህም ብዙዎቹ ፍኖተ ካርታ ሰርቶ እስከመስጠትና በዛ ላይ ምክር እስከመለገስ ደርሰዋል። አንዳንዶቹ ካላቸው ልምድና ክህሎት ተነስተው የሚያስተምሩና ወደኋላ የቀረን ሲመስላቸው የሚገስጹን ነበሩ። ይህ መልካም ድጋፍና ትብብር እየጨመረ መጥቷል። ከሲቪክ ማህበራትም ጋር እንዲሁ ስንመካከር ነበርና ቅድመ ዝግጅታን ይህን ይመስል ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- ከቅድመ ዝግጅታችሁ አንዱ የሌሎች አገሮች ተሞክሮ ምን ይመስላል የሚለው ነውና ኢትዮጵያን ያጋጠማት አይነት ተቀራራቢ ችግር ያጋጠማቸውና ጉዳዩን የፈቱበትን መንገድ በምን መልኩ ዳሰሳችሁ?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** ሌሎች አገሮች ዘንድ ምን ተሰራ የሚለውንም አይተናል፤ ለምሳሌ የየመን ለምን ስኬታማ አልሆነም? የቱኒዚያ ደግሞ ምን ስለተጠቀሙ ነው የተሳካው? የሚለውን ለማየት ሞክረናል። ከእኛም ጋር ካለው ጉዳይ ጋር አወዳድረናል። የደቡብ አፍሪካና ኬንያ የተካሄደውም ልክ እንደቱኒዚያ ሁሉ የተሳካ ነበር። በከፊል ደግሞ የቤኒንም ተሳክቷል። የሱዳን ግን ሙሉ በሙሉ ውድቅ ሆኗል። ይህ ለምን ሆነ? ኢትዮጵያ ከዚህ ምን ትማራለች? የሚለውን በቲዮሪ ደረጃ (በመሰረተ ሐሳብ ደረጃ ማወቅ ነበረብን)።

ይህንንም የየአገሮችን ተሞክሮ ከወሰድን በኋላ የገባነው ከቅድመ ዝግጅት ወደዝግጅት ምዕራፍ ነው። ይህም መነሻ ያደረገው ከአዲስ አበባ መውጣት ነው። እኔ እና ሁለት የስራ ባልደረቦቼ ጅግጅጋ የተጓዝን ሲሆን፣ ሌሎቹም የስራ ባልደረቦቻችን እንዲሁ ወደተለያዩ የአገራችን ክፍል ተጉዘዋል። በዚህ መልኩ ከአፋርና ከትግራይ ክልል በስተቀር ሁሉንም አዳርሰናል። ወደተቀሩት ክልሎችም ለመድረስ በዝግጅት ላይ ነን።



ፎቶ - ሀዲስ አብርሃ

**አዲስ ዘመን፡- ወደተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች ስትደርሱ በተጨባጭ የሰራችኋቸው ስራዎች ምንድን ናቸው?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** ወደተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ሔደን በዋናነት የሰራነው ከሕዝቡ ጋር መምከር ነው። በተለይ ደግሞ እኛንና የመጣንበትን ዓላማ በስፋት ከገለጽን በኋላ ምክክር የተባለው ነገር በራሱ ምን እንደሆነ አስረድተናል። በተለይ በ21ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ምክክር ለምን አስፈለገ የሚለውን በአግባቡ ለማሳወቅ ሞክረናል። እኛ የሰለቸን ጦርነት፣ ድህነት፣ ጉስቁልና ነው። በዋናነት ደግሞ የሰለቸን ነገር መከፋፈል ነውና በአንድነትና በትብብር መስራት የምንችለው ምን ቢሆን ነው በሚል አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ አዲስ ማህበራዊ ውል እንዲኖር መፈለጉን ገልጸንላቸዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሰላም እንዲኖር፣ ሰላምን እንዴት በሰላማዊ መንገድ ማምጣትና ባህል ማድረግ እንደሚቻል? እስካሁን ድረስ ለነበረን ውድቀት፣ ውድመት፣ ውስጣዊ ፍልሰትና ለመሳሰሉ ችግሮች መሰረታዊ ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ችግሮቹን የምንቀርፈውስ እንዴት አድርገን ነው? ዋና ዋና አንኳር የሚባሉ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? ከእናንተ ጋርስ እንዴት አድርገን እንወያያለን? የሚሉ መሰረታዊ ነገሮችን አንስተናል፤ ይህንንም በስፋት ለመጀመር ከቀበሌ አንስቶ ወረዳ፣ ዞን፣ ክልል በመጨረሻም በአገር አቀፍ ደረጃ ለማካሄድ እቅድ መያዛችንንም አሳውቀናል።

በየክልል ያሉ መስተዳድሮች ከምክትል ኮሚሽነሩ ጋር የሚገናኙበትን አገናኝ መኮንን ማቋቋም ነበረብንና ይህንንም አቋቁመናል፤ እዛ ውስጥ የምናገኛቸው ወጣት መሪዎችን፣ ሴቶችን፣ የአገር ሽማግሌዎችን፣ የኃይማኖት መሪዎችን እንዲሁም በአካባቢያቸው ተሰሚነት ያላቸውን ሁሉ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ምንስ ያጋጠማችሁ ነገር አለ? ሲያጋጥማችሁ የሚችሉ የተለያዩ አመለካከቶች ይኖራሉና እነሱን ያስተናገዳችሁት በምን አይነት መንገድ ነው? ምንስ መልካም ነገር አይታችኋል?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** ያየነውና ያስተዋልነው ነገር በጣም የሚያስደነግጥ፣ በጣም የሚያስደምም በሌላ በኩል ደግሞ ኩራት ሊሆን የሚችለውን የሕዝብ ተነሳሽነትን ነው። በተለይ ከሰጠን ድጋፍ ተነስተን በሕዝቡ ውስጥ ያስተዋልነው ነገር ቢኖር ለሰላም ያለውን ጥማት ነው። እኔ እንደኮሚሽነርነት የተጣለብኝን የኃላፊነት ክብደት ለማስተዋል ችያለሁ። ይህ እውነት ነው፤ እኔ የምናገረው ለዲፕሎማሲ ወይም ለማሳመን አይደለም። እያንዳንዳችን የሰላምን ጥማት አይተን ለአገራችን ደግሞ ምን ያህል እንደቆረጥን የሚያሳይ የህብረተሰብ ክፍል ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ሕዝቡም ሲል የነበረው፤ ‹‹ኢትዮጵያ በጭራሽ አትፈርስም›› ነው። ደግሞም ይህ የሚያሳየው በጋራ መኖርን ብቻ ሳይሆን ወደፊት የመመልከትንም ሁኔታ ነው። ዛሬ በችግር ውስጥ ቢታለፍም የወደፊቱ ግን ብሩህ እንደሆነ የሚያምን ሕዝብ ነው። ሕዝቡ ሲናገር የነበረው ለልጅ ልጁ የሚያወርሰውን ኢትዮጵያን እንደሚፈልግ ነው። ደግሞም ለልጅ ልጅ ልትወረስ የምትችል ብሩህ ኢትዮጵያ እንድትኖር የሚያስፈልገውን መስዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል ዝግጁ መሆኑን የሚያሳይ አቋም አለው። ይህ አስተሳሰብ በየሄድንበት ቦታ ሁሉ ያጋጠመን ነው። እንዳልኩሽ በተለይ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ‹‹እኛ በአመለካከት ብንለያይም ለአገራችን ሲባል ግን መመካከር እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ እናምናለን›› ሲሉ ነው እየገለጹልን ያለው። ለዚህ ምክንያታቸው መቃወም ሆነ መፎካከርም የምንችለው አገር ስትኖር ነው የሚል ነው። ስለሆነም በአገራችን ጉዳይም ሆነ በውይይቱ ላይ ሁላችንም በጋራ እንቆማለን ሲሉ ነው በእርግጠኝነት ከእያዳንዳቸው ሲነገር የሰማነው።

ለምሳሌ እኔ ለዚህ ኮሚሽን በአባልነት በሚመረጥበት ወቅት የነበርኩት በጀርመን አገር ሙኒክ በምትባል ከተማ ነው። በወቅቱም በጀርመን የመገኘቴ ምስጢር በአፍሪካ ሰላምና ደህንነት ጉዳይ ላይ ጥናት ለማቅረብ ከመጡ አፍሪካውያን መካከል ኢትዮጵያን ወክዬ ነበር። ተደውሎ የተነገረኝ እዛ በነበርኩበት ወቅት ነው።

በመሆኑም በዝግጅት ምዕራፋችን አስቀድመንም እንደገለጽነው የሶስት ዓመት እቅድ ይዘን ነው እየተንቀሳቀስን

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

ያለነውና ተጠሪነታችን ለፓርላማው እንደመሆኑ ለእሱ አቅርበንና ከፓርላማውም ሆነ ከሕዝቡም ግብዓት አግኝተን አጠናቀናል። አሁንም ወደተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በማምራት የመተዋወቂያ ጊዜያችንን እንዳጠናቀቅን ስትራቴጂካዊ እቅዳችንን በአጭሩ ካቀረብን በኋላ ከእነሱም ጠቃሚ የሆነ ግብዓት ማግኘት ችለናል። በተመሳሳይ ስትራቴጂካዊ እቅዳችንን በተለያዩ የአገራችን ክፍል በስፋት ለማሰራጨት ዝግጅቱ አለን። ይህ ዲያስፖራውንም ጭምር የሚያካትት ነው። ለዚህ ደግሞ ምክንያታችን የሒደቱ ባለቤት ራሱ ሕዝቡ ስለሆነ ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆን ስለምንፈልግ ከእነርሱ ጋር በመስራት ላይ እንገኛለን።

በዋናነት የመን ውስጥ በተካሄደው ሒደት ላይ ገንዘቡም እቅዱም ተዘጋጅቶ የተሰጣቸው በውጭ ኃይሎች ነበር። ከዚህ የተነሳም ሳይሳካ በመቅረቱ ወደቀ። የእኛ እንደዛ እንዳይሆን በሒደቱም ጭምር ከመጀመሪያ እስከመጨረሻው ሕዝቡ ባለቤት እንዲሆን እንፈልጋለን። ለዚህም ደግሞ በሚዲያ ሁሉ በግልጽ እየተነገረ ነው። ሕዝቡ ሒደቱን በግልጽ የሚያውቅ ከሆነ መካተትም መወገደም ያለበት ጉዳይ በግልጽ ሊናገር ይችላል። ገንቢ የሆነም አስተያየት በሚገባ መስጠት ይችላል።


የቱኒዚያው የተሳካበት ምክንያት ሒደቱ ራሱ አራት ሲቪል ማህበራት ከሕዝቡ ጋር በመነጋገርም ጭምር በመካሄዱ ነው። ስኬታማ መሆን የቻሉትም ሕዝብ በሕዝብ ሆኖ በመስራቱ ነውና እኛም ከእነርሱ ተሞክሮ ስለወሰድን በሚደረገው ሒደት ሁሉ ሕዝቡ የራሱን የባለቤትነትና የበላይነት መብቱን እንዲያውቅም ስለፈለግን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በሚመጣው 2015 ዓ.ም የእቅዳችሁን 60 በመቶ ለመስራት እንደወጠናችሁ ይታወቃል፤ ስራችሁን የምትጀምሩት ከምንድን ነው? 60 በመቶውንስ ለመሸፈን የሚያስችል መደላደል አለ ብላችሁ ታስባላችሁ?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** የዩኒቨርሲቲ ሕይወትሽን እንደምታስታውሺው በተፈጥሮ ሳይንስም ይሁን በማህበራዊ ሳይንስ የምርምር ስራሽን የምትጀምሪው መላምት አስቀምጠሽ ነው። የምታስቀምጪው መላምት መጨረሻ ላይ ስላለው ግብሽ ጠቋሚ ነው። ጠቅላላ ሂደትሽም ያንን እውነትነቱ አሊያም ሐሰትነቱን ለማረጋገጥ ነው። የሚነበቡ ነገሮች ሁሉ ላስቀመጥሽው መላምት ግብ መሳካት የሚያግዙ ነው የሚሆኑት። በተመሳሳይ ያቀድናቸው እቅዶች አሉ፤ አሁን ፍኖተ ካርታ አዘጋጅተናል። በየቦታውም አገናኝ መኮንኖችን ሾመናል። እንዲሁ ስብሰባዎች እንዲካሄዱ አድርገናል። እነዚህ እንዳቀድናቸው ኅዳር አጋማሽ አካባቢ የመጀመሪያ ዙር አገር አቀፍ ውይይት ማካሄድ የምንችል ከሆነ፤ ከእነዛ ውስጥ ደግሞ የአጀንዳ መረጣ ለምሳሌ የመጀመሪያ የአጀንዳ ሐሳብ ማፍለቅ አለ፤ ከእነዚህ ከፈለቁ አጀንዳዎች መካከል ግማሹ በክልል ገሚሱም በወረዳ ደረጃ ሊመለሱ የሚችሉ ይሆናሉ። ግማሹ ደግሞ በአጠቃላይ ኢትዮጵያን የሚመለከት በመሆኑ አገራዊ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ሕዝቡ እንደሚያነሳው እነዚህ ሁሉ ልክ በወንፊት እንደሚጣራ ሁሉ ተጣርተው ወደላይ ከመጡ በኋላ የመጀመሪያውን ዙር ስብሰባዎችን እናካሂዳለን፤ ከዚያ በኋላ የመጀመሪያውን ዙር ግምገማ ማካሄድ ከቻልን ካሉን ስራዎች 60 በመቶውን ማጠናቀቅ እንችላለን የሚል መላ ምት አስቀምጠናል። ይህ የሚከናወን ከሆነ ከሕዝቡም ሆነ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች እንዲሁም ከሁሉም አካላት የምንፈልጋቸው ጉዳዮችም ከተሟሉ ምክክሩም በዚህ ሁኔታ የሚካሄድ ከሆነ እስከ 2015 ዓ.ም ድረስ ያስቀመጥነውን ግብ ማሳካት እንችላለን።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ ሒደት ማዕከል የሚያደርገውና የሚያካትተው እነማንን ነው?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** በተገላቢጦሽ የማይገቡት እነማን ናቸው? ቢባል ብዬ አስባለሁ። በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1265/2014 አንቀጽ 3 ላይ የተቀመጡ መርሆዎች አሉ። የመጀመሪያው አካታችነት ነው። ይህ አካታችነት ሁሉንም የሚያካትት ነው። እኛ እንደኮሚሽን ለምሳሌ እነማን ናቸው የሚካተቱት? ቢባልና ሌላው ቀርቶ የኢትዮጵያ ፓርላማ በአሸባሪነት የፈረጀውን ሁሉ ያካትታል ቢባል መልሴ አዎ! ሁሉም ይገባል ነው። በዚህ ጉዳይ ደግሞ መንግስትም ሕዝብም ያምነናል። ምክንያቱም እኛ በኮሚሽኑ ውስጥ ስንገባ ስልጣን አሊያም ደመወዝ ፍለጋ አይደለም። የምንፈልገው በነጻነት ሕዝብን ማገልገል ነው። ፍላጎታችን ከማንም ሳንወግን በገለልተኛነት ማገልገል ነው። ስለሆነም ከዚህ ሒደት ማንም ወደኋላ የሚቀር አካል አይኖርም። መሪውም ተመሪውም የሚገኙበት ነው። ስለዚህም ጥያቄሽ በተገላቢጦሽ እነማናቸው የማይካተቱት ቢባል ምላሹ ማንም የሚል ነው የሚሆነው። በኃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በዘር፣ በስልጣን በየትኛውም ነገር ልዩነት ሳይፈጥር ሁሉንም አካታች ነው የሚሆነው።




**አዲስ ዘመን፡- ህዳር አጋማሽ ላይ እንጀምራለን ያላችሁት ውይይት ላይ የሚነሱ ዋና ነጥቦች የሚባሉት የትኞቹ ናቸው? የሚጀምረውስ በእነማን ነው? አወያዮቹስ?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** የውይይቱን አንኳር ነጥቦች ከማንሳታችን በፊት በመጀመሪያ እነማን ናቸው ተወያዮቹ? አወያዮቹ? አመቻቾቹ? ቃለ ጉባኤ ያዦቹ? ታዛቢዎቹ ቀጥሎ ደግሞ አጀንዳው ምንድን ነው? አካሄዱስ እንዴት ነው? እነዚህ መሰረታዊ ጥያቄዎች ካነሳሻቸው ጥያቄዎች ጋር የተያያዙ ናቸው። አወያዮቹም ሆኑ ታዛቢዎቹና መሪዎቹ ራሱ ሕዝቡ የሚያምናቸውና በአካባቢው ታማኝነት ያላቸው እንዲሁም ተሰሚ የሆኑ ከራሱ ከሕዝቡ የሚመረጡ ናቸው። አመቻቾቹ ደግሞ እንዴት ማወያየት እንደሚቻል ስልጠና የወሰዱ ናቸው፤ ምክንያቱም ምክክር እውነትን ፍለጋ ወይም መጓዣ ሒደት ነው። ምክክር ሲባል ዝም ብሎ ድርድር ወይም ሽምግልና አይደለም፤ እውነትን ፍለጋ መንገድ ነው።

የአዋጁ መግቢያ ላይ ልብ ብለሽ ከሆነ ‹በኢትዮጵያ የሚገኙ የተለያዩ የፖለቲካና የሐሳብ መሪዎች እንዲሁም የኅብረተሰብ ክፍሉ መካከል እጅግ መሰረታዊ በሆኑ አገራዊ ጉዳዮች ላይ የሐሳብ ልዩነትና አለመግባባት የሚታይ በመሆኑ ይህንን ልዩነትና አለመግባባት ለመፍታት ሰፋፊ አገራዊ የሕዝብ ምክክሮችን አካታች በሆነ መንገድ በማካሄድ አገራዊ መግባባት መፍጠር አስፈላጊ ነው› ይላል። ስለሆነም እነዚህን የሚወክሉና መሰል አጀንዳዎች በመሰረታዊ ልዩነቱ ለምሳሌ መሰረታዊ ልዩነት ሲባል በራሱ ኢትዮጵያ እንደ አገር ትቀጥል ወይስ አትቀጥል? እንዲሁም ኢትዮጵያውያን አንድ ላይ እንኑር ወይስ አንኑር? እነዚህ መሰረታዊ ልዩነት የሚባሉ አይነት ናቸው። ይህ አይነቱ ብቻ አይደለም፤ ለምሳሌ በመኖር አለመኖር ጉዳይ ላይ እንኳ ልዩነት አለ። እነዚህን የሚወክሉ አጀንዳዎች ከህዝብ ከመረጥን በኋላ ውይይቱ መካሄድ ያለበት በእነዚህ ላይ ነው።

ማን ይወያይ? ወደሚለው ሲመጣ የሚያገባቸው ሰዎች ሁሉ የሚመረጡበት ነው። ውይይቱ ሲካሄድ ደግሞ ታዛቢዎች በግልጽ የሚመለከቱበት ሁኔታ አለ። ተወያዮቹ ሲናገሩ በድምጽም በምስል የሚወስድ አካልም ይኖራልና በአጭሩ አካሄዳችን ይህን ይመስላል።

**አዲስ ዘመን፡- አስቀድመው ወደሌሎቹ ክልሎች መሄዳችሁን ጠቅሰዋል፤ የቀራችሁ ሁለት ክልል ሲሆን፣ እነሱም አፋርና ትግራይ ናቸው፤ ወደእነዚህ ክልሎች በተለይ ደግሞ ወደትግራይ መቼ ለመሄድ አሰባችሁ?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** ለአፋር ደብዳቤ ጽፈን ልከናል። መልስም በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን። በተመሳሳይ ደግሞ ወደ ትግራይ ያሰብነው ጉዳይ አሁን ከተፈጠረው ምቹ ሁኔታ አለመኖር ጋር በተያያዘ በእንጥልጥል ላይ ነው ያለው።

**አዲስ ዘመን፡- ከህዝቡ ምን ትጠብቃላችሁ?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** የመጀመሪያ ከሕዝቡ የምንፈልገውና የምንጠብቀው ቀና አመለካከትን ነው። የምንሻው መንፈሳዊ ሞራላዊ ድጋፋቸውን ነው። ይህ ትልቁ ነገር ነው። በአመራር ላይ፣ በተለይ ሰላም ግንባታ ላይ ከችሎታሽም የበለጠ የአንቺን ከፍታ የሚወስነው አመለካከትሽና አስተሳሰብሽ ነው የሚባል አባባል አለ። በመሆኑም ትልቁ ነገር ይቻላል ብሎ ማሰብ ነው። ችግራችንን መፍታት እንችላለን፤ ለዚህ ደግሞ ጉልበቱ አለን ብሎ ማሰቡ የመጀመሪያው ወሳኙ መንደርደሪያ ነው። አገራችን ኢትዮጵያ የአባባል ሀብታም እንደሆነች ይታወቃል።

አንድ ሰው ገና ከቤቱ ሳይወጣ የሚሄድበትን አቅጣጫ ሳይወስን ከተንቀሳቀሰ ሁሉም አቅጣጫ መንገዱ እንደሆነ ነው የሚያስበው። አስቀድሞ ወስኖ ለወጣ ሰው ግን አካሄዱም ሆነ ግቡ ግልጽ ነው። ስለዚህም በመጀመሪያ ደረጃ አስተሳሰባችንና አካሄዳችንን ካስተካከልን ምንም እንኳ ዛሬ ፈተናዎች ቢጋረጡብንም፤ ግጭቶችም ቢያጋጥሙንም ይህንን ማለፍ እንችላለን፤ ደግሞም ዛሬ ሁሉ ቦታ ሰላም ነው። ነገር ግን አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ግጭቶችን በማየት ተስፋ ሳንቆርጥ በእሳት ውስጥም ቢሆን እንኳ መራመድ እችላለሁ ማለትን ባህል ማድረጉ ተገቢ ነው። ተስፋ የሕይወት መንኮራኩር፤ የሕይወት ሞተርም ጭምር በመሆኑ ከሕዝቡ በመጀመሪያ የስነ ልቦና ዝግጅታቸውን እንፈልጋለን።

ሚዲያዎችም ቢሆኑ ሲዘግቡ የቃላት አጠቃቀም ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ እንሻለን። ለሕዝቡ አዎንታዊ የሆነ ኃይል እንጂ አሉታዊ የሆኑ ነገሮችን ከማንጸባረቅ መራቁ ተመራጭ ይሆናል። በተለይ ደግሞ የሚዲያን ድጋፍ በጣም እንፈልጋለን፤ ምን አይነት ድጋፍ ከተባለ ለምሳሌ ምክክር ምንድን ነው? ከድርድርስ የሚለየው በምንድን ነው? የሚለውን ለሕዝቡ በአግባቡ ማስጨበጥ አንዱ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላምን በሰላማዊ መንገድ ማምጣትን እንዴት ባህል ማድረግ ይቻላል? እንዴትስ አድርገን ነው የሰላምን ባህል በአገራችን የምንገነባው? የሚለውንም ከቤተሰብ ጀምሮ፣ አጸደ ሕጻናት ብሎም በቤተ እምነቶችና በሌሎችም ዘንድ ግንዛቤው እንዲኖር ማድረግ ከሚዲያው የሚጠበቅ ተግባር ነው። በተለያዩ ቦታዎች ትንሽ ልዩነት ሲኖር ወደ መሰዳደብና ወደ መገዳደል መሄድ ሳይሆን ወደመነጋገር መምጣትን ባህል ማድረግ እንዲኖር ሚዲያው እንዲሰራ እንፈልጋለን።

ሌላው ደግሞ ቁሳዊ ድጋፎችን እንሻለን። ለምሳሌ ገንዘብ የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ። ሎጂስቲክ የሚያስፈልግበት ቦታ አለ። እስካሁን ከነበረው የበለጠ የሕዝቡን ቅን ትብብር እንፈልጋለን። ከመንግስትም በኩል ያለው ለምሳሌ በአዋጁ የተደነገጉት ጉዳዮች በተባለው መመሪያ መሰረት ለኮሚሽነሮች የሚያስፈልገው ድጋፍ ከደህንነት ጥበቃ ጀምሮ እንዲሟሉልን እንሻለን።

ተፎካካሪ ፓርቲዎች እጅግ ከፍተኛ ድጋፍ እያደረጉልን ነው። ይህንኑ ድጋፋቸውን ሳያቋርጡ እንዲቀጥሉ እንፈልጋለን። አኩርፈው የወጡም ማለትም አልተወከልንም ያሉ ሰዎች ቆም ብለው በማስተዋል እንደገና ወደንግግሩ እንዲመጡ (በእርግጥ ይህ ተጀምሯል) እና አዎንታዊ ተሳትፏቸውን እንዲያደርጉ እንፈልጋለን። ያለችን አንድ የሆነችው ኢትዮጵያን በጋራ እንድንገነባ እንሻለን። በጥቅሉ ሁላችንም በሐቀኝነትና በአዎንታዊ አስተሳሰብ ልክ እጅ ለእጅ ተያይዘን ለታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድባችን እንዳደረግነው አይነት መረባረብና አንድነት ሁሉ አገራችንንም ለማዳን እንድንነሳሳ በአክብሮት ጥሪዬን አቀርባለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ኮሚሽኑ ለሰላም የበኩሉን እያደረገና ያቀደውንም ተግባራዊ እንዲሆን እየተንቀሳቀሰ ነው፤ ይህ ባለበት ሁኔታ ግን ከአንዳንድ ምሁርም ሆነ ከማህበረሰብ አንቂዎች ዘንድ በማሕበራዊ ትስስር ገጽ ላይ ያልተገቡ መልዕክቶች ሲስተዋሉ ይችላሉና ይህ እንዳይሆን እነዚህን አካላት ከወዲሁ ምን ማለት ይፈልጋሉ?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** እነዚህን አካላት እግዚአብሔር ይባርካችሁ ማለት እፈልጋለሁ። ምክንያቱም ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚለው፤ ታላቁ ጌታ በመስቀል ላይ ሲሰቀል ያልተገባ ነገር የሚያደርጉትን አይቶ ‹የሚያደርጉትን አያውቁምና አባት ሆይ ይቅር በላቸው› የሚል አይነት ምላሽ ነው የምንሰጣቸው። ሰላምን በሰላማዊ መንገድ ሲባል ምን እንደሆነ ለመግለጽ ያህል ለሰላም መንገድ የለውም፤ ወደሰላም መድረሻ መንገድ እራሱ ሰላም እንደሆነ ነው የምንናገረው። ሌላው ደግሞ ተቃውሞ ቢኖር ምንም አያስደንቀንም። ምክንያቱም ምክክር የእውነት ፍለጋ መንገድ ነውና። ስለዚህ ኑ! አብረን እንወያይ፤ ዛሬ ያስቆጣን፤ በአሉታዊ መንገድ እንድንጽፍ ያደረገን ሁልጊዜ በዛው አይቀርምና፤ ነገ ለውጥ ይኖራል። ስለዚህም ላለችን አንድ አገር አብረን እንስራ እንላለን። ጨለማውን ፈርተን ብርሃን ከማየት አንጉደል እንላቸዋለን። ልዩነቶቻችንንም በንግግርና በምክክር መፍታት እንችላለን። ትልቁ የስልጣኔ ምልክት ባኮረፉ ቁጥር ጫካ መግባትና መሳሪያ ማንሳት ሳይሆን በተጠይቅያዊ አካሄድ ተወያይተን መፍታትም ስልጡንነት ነው እንላለን።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ምንም ያህል ተቃውሞ ቢያጋጥመን እንኳን ተቃውሞ እንደመስፈንጠሪያ አቅም እንጠቀምበት እንደሆን እንጂ ከግባችን የሚያስቀረን አይሆንም። ደግሞም ተቃዋሚ በመኖሩም ነው መመካከሩ አስፈላጊ ሆኖ ስራ መስራት የተጀመረው። ስለሆነም በመቃወማቸው እናመሰግናለን፤ ለዚህም ነው እግዚአብሔር ይባርካቸው ስል መልስ መመለስ የጀመርኩት። የሚቃረን ነገር ካለም አብረን እንፍታ እንላለን። ሁላችንንም አገራችንንም ፈጣሪ አምላክ ይባርክ እላለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር ዮናስ፡-** ሰላም ይብዛልን፤ እኔም አመሰግናለሁ።

# ዓለም አቀፍ



## እሥራኤል በፈጸመችው የአየር ጥቃት የፒአይጄ ሁለት አመራሮች ተገደሉ

በጋዜጣው ሪፖርተር

እሥራኤል በጋዛ ሰርጥ ባደረሰችው የአየር ጥቃት የፍልስጥኤም እስላማዊ ጂሃድ ቡድን (ፒአይጄ) ሁለት አመራሮችን ጨምሮ በርካቶች መገደላቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

የተገደሉት የቡድኑ አመራሮቹ ካሊድ መንሱር እና ጣይር ጃብሪ ይባላሉ። በተጨማሪ በጥቃቱ የተገደሉ በርካታ የቡድኑ ተዋጊዎችና ፍልስጥኤማውያን መኖራቸው በዘገባው ተገልጿል።

ከአርብ ጀምሮ ወደ 400 የሚጠጉ የፍልስጥኤም ሮኬቶች እና ሞርታሮች በእሥራኤል ላይ መተኮሳቸውን የእሥራኤል ባለሥልጣናት መናገራቸው ይታወሳል።

በምላሹ እሥራኤል ወታደራዊ ዘመቻ ማካሄድ ጀምራለች። በዘመቻው የአየር ጥቃት የጀመረችው እሥራኤል ዘመቻው ያስፈለገው የፍልስጥኤም እስላማዊ ጂሃድ ቡድን በደቀነው ከፍተኛ ስጋት ነው ብላለች።

'ብሬኪንግ ዳውን' አሊያም መሰባበር የሚል የኮድ ስም በተሰጠው የእሥራኤል ወታደራዊ ዘመቻ ለአንድ ሳምንት ሊቆይ እንደሚችል ባለሥልጣናቷ አስጠንቅቀዋል።

ባለፈው አመት ግንቦት ወር ለ11 ቀናት በዘለቀው እና ከ200 በላይ ፍልስጥኤማውያን እንዲሁም በርካታ እሥራኤላውያን ከተገደሉበት ግጭት ወዲህ ይህ በቅርቡ በእሥራኤልና በጋዛ መካከል የተከሰተ አሳሳቢ ግጭት አድርጎታል።

በሁለተኛው ቀን የእሥራኤል አፀፋዊ ጥቃት በደቡባዊ ጋዛ ራፋህ በሚገኝ መኖሪያ ቤት ላይ በፈጸመችው የአየር ጥቃት ከፍተኛ የፒአይጄ መሪ ካሊድ መንሱርን መግደሏን አስታውቃለች።

ከጋዛ ውጪ ወታደራዊ ጥቃቶችን ፈጽሟል በማለት እሥራኤል የምትከሰው ካሊድ መንሱር ከዚህ ቀደም በእሥራኤል ጦር ከአምስት የግድያ ሙከራዎች ተርፎ ነበር።

ከእሱ ሞት በፊት አርብ ዕለት ከፍተኛ የፒአይጄ አመራር የሆነው ታይሲር ጃባሪ በእሥራኤል የአየር ጥቃት ተገድሏል።

እንዲሁም በጋዛ በተፈጸመው የአየር ጥቃት ድብደባ በርካታ የቡድኑ አባላት ከመገደላቸው በተጨማሪ እሥራኤል ተቆጣጥራለች ባለችው የዌስት ባንክ በተደረገ ከበባ 19 የሚሆኑ የፒአይጄ አባላት በቁጥጥር ስር መዋላቸውን እሥራኤል ገልጻለች።

የጋዛ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለፍልስጥኤማውያን ሞት እንዲሁም ለቆሰሉት 203 ሰዎች የእሥራኤል ወረራን ተጠያቂ አድርጓል።



## የሶማሊያ ፓርላማ 26 የካቢኔ አባላትን ሹመት አፀደቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የሶማሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ከተሾሙ 41 ቀናትን ያስቆጠሩት ሀምዛ አብዲ ባሬ ያቀረቧቸውን 26 የካቢኔ አባላት ሹመት የአገሪቱ ፓርላማ አጽድቋል።

ካቢኔው የአልሸባብ የቀድሞ ምክትል መሪ ሙክታር ሮቦው አቡ ማንሱርንም ማካተቱን ሲ ጂ ቲ ኤን ዘግቧል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲሾሙላቸው የጠየቁትን 26 የካቢኔ አባላት ያቀረቡት ከአገሪቷ ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ መሐሙድ ጋር በመምከር መሆኑን ቀደም ሲል ጠቁመው ነበር።

ሹመቱ የጸደቀው የአገሪቷ ፕሬዚዳንት የሆኑት ሀሰን ሼክ መሐሙድ፣ የድርቅ አደጋን ለመግታት፣ የደኅንነት ሥጋትን ለመቅረፍ፣ የአገሪቷን ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማረጋገጥ እና ለሶማሊያ ወጣቶች የሥራ ዕድል ለማመቻቸት ያቀረቡትን አጀንዳ መፈጸም እንዲቻል ይሠራሉ ተብሎ ዕምነት ተጥሎባቸው ነው ተብሏል፡፡

ለሹመት የቀረቡት የካቢኔ አባላት የትምህርት ደረጃ እና የሥራ ልምድ ከግምት ውስጥ መግባቱም ተመላክቷል፡፡

ሶማሊያውያን ከአዲሱ መንግሥት ጋር እንዲተባበሩ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ጠይቀዋል።

እ.አ.አ በግንቦት ወር አጋማሽ ላይ በሶማሊያ ምክር ቤት በተደረገው ምርጫ ፕሬዚዳንት ሆነው የተመረጡት ሐሰን ሼክ መሐሙድ የአገሪቷ ፓርላማ አባል የሆኑት ሐምዛ አብዲ ባሬን በጠቅላይ ሚኒስትርነት መሾማቸው የሚታወስ ነው።

በወቅቱ ሹመቱን ተከትሎ አስተያየታቸውን የሰጡት አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር የሶማሊያን አንድነት በማስጠበቅ ሀገሪቱን የማዳን ተግባር ላይ እንደሚያተኩሩ ገልጸው እንደነበር ቢቢሲ ዘግቧል።

ሐምዛ አብዲ ባሬ በሶማሊያ መንግሥት ውስጥ የተለያዩ የሥልጣን እርከኖች ላይ ሠርተዋል። እአአ ከ2019 እስከ 2020 ድረስ የጁባላንድ የምርጫ ኮሚሽን ሊቀመንበር ባገለገሉበትም ወቅት ነው ስማቸው የገነነው።

እአአ ከ2014 እስከ 2015 የቤናዲር ክልል ርዕሰ መስተዳድር እና የሞቃዲሾ ከንቲባ ለሆኑት ሐሰን መሐመድ ሁሴን አማካሪ ሆነው አገልግለዋል።


### የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት አቶ መሀመድ ሰይድ እና በፍ/ባለዕዳ ወ/ሮ ሃያት ሙሳ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 253939 በ13/09/2013 ዓ.ም እና በመ/ቁ 191069 በ11/03/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 01 ሩዋንዳ አካባቢ ውስጥ የሚገኝ ፓርሴል 7 በካርታ ቁጥር ቦሌ 9/15/1/11/22469/19347/01 የሆነ ካርታ ያለው በወ/ሮ መስታወት አማረ ማሞ ስም የተመዘገበ G+2 የሆነ ሕንፃ (ቤት) የይዞታው ስፋት 500 ካ/ሜ የሆነ የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 2,116,000 (ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ አስራ ስድስት ሺህ ብር) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ጥቅምት 25 ቀን 2015 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ8፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡ የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናት ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3:30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጎብኘት የሚችሉ ሲሆን፤ እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ CPO ማስያዝ ይኖርበታል። ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡
በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጎድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬቱ የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ፍ/ቤቶች**
**የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት**

### የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለሙብት አቶ ኤልያስ የኑስ እና በፍ/ባለዕዳ ሀጅ በሽር መሀመድ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 86032 ቀን በ10/3/2014 ዓ.ም በመ/ቁ 76360 በ3/12/2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቤ.ቁ 1042 የሆነው ቤትና መጋዘን ኮ/ቀ 06/19/1389/00 የቦታ ስፋት 568 ካ/ሜ ያህል አዋሳኞች በሰሜን የቀበሌ፣ በደቡብ ከመንገድ በምስራቅ ቀበሌ በምዕራብ አስካለ ገ/ማርያም ሆኖ በአጠቃላይ ይዞታ ውስጥ /ቦታው/ የስፍር መንገድ 41 ካ/ሜ የሚነካ ሆኖ የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 1,264,000 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ስልሳ አራት ሺህ) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ህዳር 1 ቀን 2015 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ4፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡ የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፤ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናት ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3:30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጎብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ CPO ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም። በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት።
በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጎድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬቱ የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ፍ/ቤቶች**
**የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት**

### የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክ/ከ ወረዳ 03 የቤት ቁጥር አዲስ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0052967775 ዊንታና አየነው ከተመዘገብኩበት ቦሌ ክ/ክ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፈቃድ በማግኘት ካሳተምኩት ደረሰኝ ውስጥ የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ያልተሰራበት ቁጥር 00444 (አንድ ቅጠል) ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራበትው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት ቦሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ዊንታና አየነው**

### የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ን/ስ/ላ ክ/ከ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 1085 የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0004064751 ሀይማኖት ኤፍሬም ሽፈራው ከተመዘገብኩበት ን/ስ/ላ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፈቃድ በማግኘት ካሳተምኩት ደረሰኝ ውስጥ የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ የተሰራበት ቁጥር 0200 እና ቁጥር 0201 ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት ን/ስ/ላ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ሀይማኖት ኤፍሬም ሽፈራው**

### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም ፡- አበበ ደምሴ ሶማ<br>የአመልካች አድራሻ፡- ወረዳ 03 የቤት ቁጥር 923, ቦሌ, አዲስ አበባ ኢትዮጵያ | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር፡- LTM/12529/2014<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን፡- 05/11/2014 E.C. | | |
| 3 | ምልክት<br>ሶያም ኢንጂነሪንግ SOYAM ENGINEERING Your construction Colleague | 4 | የምልክቱ መግለጫ፡-የቃልና ምስል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት፡- ብርቱካናማ እና ቡናማ |
| | | 6 | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ፡- ኢንጂነሪንግ (ENGINEERING, Your construction Colleague) |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ፡- 37 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ከውሃ ኤሌክትሪክ እና ኤሌክትሮ መካኒካል ሥራ በስተቀር (ምድብ 37) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፈቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

**ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-332 2/12/2014 (8/8/2022)**

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ስፖርት



ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!












# ወርቅ የታፈሰበት ሌሊት

**ቦጋለ አበበ**

የዘንድሮው የውድድር አመት ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ የተለየ ሆኖ እየተገባደደ ይገኛል። ከሳምንታት በፊት በ18ኛው የኦሪገን የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና አስደናቂ ውጤት በማስመዝገብ አሜሪካንን ተከትሎ በታሪኩ ሁለተኛ ሆኖ ያጠናቀቀው የኢትዮጵያ ቡድን ጣፋጭ ድል ሳይረሳ ሌላ ተጨማሪ አስደሳች ውጤት ተመዝግቧል። የኦሪገን ቻምፒዮና በተጠናቀቀ ማግስት ወደ ደቡብ አሜሪካዋ ኮሎምቢያ ያቀናው የኢትዮጵያ ወጣት የአትሌቲክስ ቡድን በካሊ የዓለም ከ20 አመት በታች የዓለም ቻምፒዮና ሌላ ታሪክ ማስመዝገብ ችሏል።

በውድድሩ ታሪክ ስድስት ወርቅ፣ አምስት ብርና አንድ የነሐስ ሜዳሊያ በማስመዝገብም ከዓለም ሦስተኛ ከአፍሪካ ደግሞ ቀዳሚ ሆኖ ማጠናቀቅ ችሏል። ላለፉት ስድስት ተከታታይ ቀናት ሲካሄድ በሰነበተው የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ቻምፒዮና በ19 አትሌቶች በሁለቱም ፆታ በ10 የውድድር ተግባራት ብቻ የተሳተፈው የአትሌቲክስ ቡድን በድምሩ በ12 ሜዳሊያዎች ከዓለም አገራት አሜሪካንን እና ጃማይካን ተከትሎ 3ኛ ደረጃን ይዞ አጠናቋል። ይህም ውጤት እስከ ዛሬ ከተካሄዱት የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ቻምፒዮናዎች ከፍተኛው ሲሆን ከተሳተፉበት ውስን ውድድሮች አንፃር ውጤቱ በርካቶችን ያስደሰተ ሆኗል።

በውድድሩ ኢትዮጵያ ይዛ ካጠናቀቀችው ደረጃ ባሻገር አራት ወርቆችና ሁለት የብር ሜዳሊያዎች ቻምፒዮናው ከትናንት በስቲያ ሌሊት ሲጠናቀቅ የተመዘገቡበት መንገድ በርካቶችን አስደስቷል። እነዚህ ሜዳሊያዎች በአንድ ሌሊት አንድ ሰዓት ባልሞላ ሰዓት ውስጥ ሲመዘገቡ በወንዶች ስምንት መቶ ሜትር ወርቅ፣ በወንዶች 3ሺ ሜትር መሰናክል ወርቅና ብር፣ በሴቶች 1500 ሜትር ወርቅና በሴቶች አምስት ሺ ሜትር ወርቅና ብር የኢትዮጵያ ሆኗል።

ከቀናት በፊት በ1500 ሜትር የብር ሜዳሊያ ያጠለቀው ወጣቱ አትሌት ኤርሚያስ ግርማ በ800 ሜትር ተጨማሪ ወርቅ በማጥለቅ በቻምፒዮናው የጎላ ኢትዮጵያዊ አትሌት ሆኗል። በ3ሺ ሜትር መሰናክል ወንዶች ሳሙኤል ዱጉና የወርቅ ሜዳሊያውን ሲያጠልቅ ሌላኛው ኢትዮጵያዊ ወጣት አትሌት ሳሙኤል ፍሬው በድንቅ ብቃት የብር ሜዳሊያውን ወስዷል። ከባድ ፉክክር ባስተናገደው በ5ሺ ሜትር ሴቶች ውድድር መዲና ኢሳ እና መልክናት ውዱ በተመሳሳይ ወርቅ እና ብር ሜዳሊያ ሲያጠልቁ፣ በ1500ሜ ሴቶች ደግሞ በአትሌት ብርቄ ሀየሎም (4:04.27) የቻምፒዮናውን ክብረወሰን በማሻሻል ጭምር የወርቅ ሜዳሊያ ማሸነፍ ችላለች።

ከፍጻሜው ቀን አስቀድሞ በነበሩ ሌሎች ውድድሮች ኢትዮጵያ በ5 እና 3ሺ ሜትር ወንዶች በአዲሱ ይሁኔ እና መልኬነህ አዘዝ የወርቅ፣ በ3ሺ ሜ መሠናክል ሴቶች በሲምቦ አለማየሁ፣ በ1500 ሜትር ወንዶች በኤርሚያስ ግርማ እና በ3ሺ ሜትር ሴቶች በፅዮን አበበ የብር ሜዳሊያዎችን ያሸነፈች ሲሆን፣ በተጨማሪም በሴቶች 3ሺ ሜትር መሰናክል በአትሌት መሠረት የሻነህ የነሐስ ሜዳሊያ ማግኘቷ ይታወቃል።

ይህንን ውጤት ተከትሎም ኢትዮጵያ በሜዳሊያ ሰንጠረዡ በስድስት ወርቅ፣ አምስት ብር እና አንድ የነሐስ በድምሩ በ12 ሜዳሊያዎች፡ ከአሜሪካ እና ጃማይካ በመቀጠል ከዓለም ሦስተኛ ከአፍሪካ ደግሞ በቀዳሚነት ውድድሯን ፈጽማለች። በ19 ወጣት አትሌቶች እና በ10 የውድድር ዓይነቶች ተሳትፎ ብቻ የተገኘው ይህ አስደናቂ ውጤት በቻምፒዮናው ታሪክ የኢትዮጵያ የምንጊዜም ከፍተኛው ሆኖ ተመዝግቧል።

## ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የሀገራት የሉዓላዊነታቸው ፈተና እየሆነ የመጣው የሳይበር ግጭትና መፍትሔው

**ደበል ካሳ**

የሳይበር ምህዳር ከፈጠራቸው ዋና ዋና ተቃርኖዎች መካከል አንደኛው ምህዳሩ ዓለምን እርስ በእርስ በማስተሳሰርና ወደአንድ መንደር እንድትመጣ በማድረግ በዓለም ዙሪያ ያልተገደበ ወዳጅነትን መፍጠር እንደቻለው ሁሉ በዚያው ልክ የጥቅም ግጭቶችና የእርስበእርስ ሽኩቻዎች እንዲበዙ ማድረጉ ነው። የሳይበር ምህዳሩ በዓለም ዙሪያ ስለፈጠረው የእርስ በእርስ መተሳሰርና ወዳጅነት ከዚህ ቀደም በነበሩት ዝግጅቶቻችን በተደጋጋሚ ልናስቃኛችሁ ሞክረናል። ዛሬ ተራውን ያደረግነው ምህዳሩ እየፈጠረው ስለሚገኘው ሉላዊ ግጭት ነው።

ዓለም በበይነ መረብ እርስበእርስ እየተሳሰረች በመጣች ቁጥር ምህዳሩን ባልተገባ መንገድ ለመጠቀም በሚፈልጉ አካላት የተነሳ ሳይበራዊ ግጭቶች እየተበራከቱ መምጣታቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተለያየ መንገድ የራሳቸውን ጥቅም ለማስፈጸም የሚፈልጉ አካላት ገሚሶቹ ገንዘብ ለማግኘት፣ ገሚሶቹ የራስን ፖለቲካዊ ግብ ለማሳካት፣ ሌሎቹ ደግሞ ጠላቴ የሚሉትን አካል በመበቀል ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ለማድረስና ሀገራዊ ቀውስ ለመፍጠር ሳይበር የፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም በመላው ዓለም ጥቃቶችን በመፈጸም ግጭትን ይፈጥራሉ።

በተለይም በሀገራትና በመንግሥታት ላይ ኢኮኖሚያዊ አለመረጋጋትን በመፍጠር፣ ፖለቲካዊ ቀውስ በመፍጠር ዲፕሎማሲያዊ ተቀባይነታቸውን በማሳጣት፣ ባህልና ማንነታቸውን በመሸርሸርና ማህበራዊና ማህበረ ሥነ ልቦናዊ ቀውስ በመፍጠር፣ የሳይበር ሽብር በመፍጠርና ሀገራዊ ሉዓላዊነትን ለማሳጣት የታለሙ ግጭቶችና ጥቃቶች እየተበራከቱ መምጣታቸውን መረጃዎች ያመላክታሉ። በዚህ ረገድ ቻይናና አሜሪካን፣ ሩስያና አሜሪካን፣ እስራኤልና ኢራን፣ አሜሪካና ኢራንን በዋና ማሳያነት ማንሳት ይቻላል።

የሳይበር ምህዳሩ ልቅ፣ ድንበር የለሽና ለቁጥጥር አስቸጋሪ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለስርቆት፣ ለወንጀልና ለደህንነት ጥቃት በከፍተኛ ደረጃ ተገላጭ የሚያደርግ ምቹ ሁኔታን መፍጠሩ ደግሞ በሀገራት ሉዓላዊነት ላይ ለሚደርሱ ጫናዎች አመቺ ሆኗል። ምህዳሩ የራስን ህልውናና ደህንነት ብሎም ሀገራዊ ሉዓላዊነትን በማስጠበቅ ረገድ፤ ከጠላት የሚሰነዘርን ጥቃት በመመከትና መልሶ በማጥቃት፣ በወታደራዊ ኃይል ግንባታና በጦርነት መስክ ያለውን አሰላለፍም እየቀየረው መሆኑን ምሁራን ይገልጻሉ።

በዚህ የተነሳ በሀገራት መካከል በሚፈጠር አካላዊ ግጭትና ጦርነት ሳይቀር የሳይበር ምህዳሩ አስተዋጽኦ እየጨመረ መጥቷል። ምድር ላይ የሚደረግ ጦርነትን ጭምር በበላይነት ለማጠናቀቅ ከጦር መሳሪያና ከሎጅስቲክስ እኩል መረጃም ወሳኝ ሚና ያለው መሆኑ ግልጽ እየሆነ መጥቷል። አውታረ መረብንና የኮምፒዩተር ትስስርን መሠረት ያደረገው የሳይበር ዘመን ፈጣን የመረጃ ልውውጥና ስርጭት ሥርዓት ደግሞ በጦርነት ውስጥ የሚካሄዱ ውጊያዎችን ከምንጊዜውም በላይ በመረጃ ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ ስለሚያደርግ ከጦር መሳሪያና ከሎጅስቲክስ በላይ ድልና ሽንፈት የሚወሰነው በሳይበር ምህዳሩ ኃይል ይሆናል።

በመሆኑም ሀገራት ፊታቸውን ወደሳይበር ተኮር የወታደራዊ ኃይል ግንባታ ሥርዓት እያዞሩ ይገኛሉ። በዚህ ረገድ ቻይና በግንባር ቀደምትነት እየተንቀሳቀሰች መሆኗን መረጃዎች ያመላክታሉ። ይህንን በማድረጓም ሀገሪቱ በዓለም የኃይል ሚዛን አሰላለፍ ከፍተኛ ተፅዕኖን እየፈጠረች ትገኛለች። ከጊዜ ወደጊዜ የምዕራባውያንን የበላይነት የሚገዳደር አልፎ ተርፎም ከእነርሱም የሚበልጥና እነርሱን ጭንቀት ውስጥ የሚያስገባ ኃይል ልትገነባ ችላለች። በጦር መሣሪያና በወታደር የተኩስ ልውውጥ ከሚደረገው ከተለምዷዊው ጦርነት በአሻገርም የአውታረ መረብ ግንኙነትን በማጥፋትና መረጃን በመጥለፍ ወሳኝ የደህንነትና የኢኮኖሚ መሠረተ ልማቶችን በማውደም የሚፈጸም የሳይበር ጥቃትም ራሱን የቻለ የጦርነት አውድ እየሆነም መጥቷል።

በኢትዮጵያም ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ጋር ተያይዞ የራሷን ጥቅም ብቻ ለማስጠበቅ የምትፈልገውና ከኢትዮጵያ ጋር አላስፈላጊ ግጭት ውስጥ የገባችው ግብጽና በግድቡ ላይ ፖለቲካዊ ፍላጎት ያላቸው ሌሎች ሀገራት ከሀገራችን ጋር የሳይበር ግጭት ውስጥ መሆናቸው ይታወቃል። በዚህም በኢትዮጵያ ላይ ፖለቲካዊ ጫና ለመፍጠር ያለመ የሳይበር ጥቃት የሚፈጽሙ አካላት መኖራቸውም የማይዘነጋ ሃቅ ነው። በዚህም የግድቡ የመጀመሪያ ዙር ውሃ ሙሌት ከመከናወኑ ጥቂት ጊዜያት ቀደም ብሎ መቀመጫቸውን ግብፅ ያደረጉ የሳይበር ወንጀለኞች ከሰኔ 10 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ለአራት ተከታታይ ቀናት በኢትዮጵያ ላይ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጫና ለመፍጠር ያለመ የሳይበር ጥቃት ለማድረስ ሞክረው በኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር አማካኝነት ሙከራው መክሸፉ ይታወሳል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሀገራችን ባለፈው አንድ ዓመት ስታካሂደው በቆየችው ህልውናንና ሉዓላዊነትን የማስጠበቅ ጦርነት የሳይበር ጦርነት አካል በሆነው የሃሰተኛ መረጃ ስርጭትና የሀገሪቱን ስም የማጥፋትና መልካም ገጽታን የማጠልሸት ፕሮፓጋንዳ ምዕራባውያንና ሌሎች የኢትዮጵያ ጠላቶች ከኢትዮጵያ ጋር ለገቡበት ያልተገባ የሳይበር ግጭት ማሳያ ነው። በህልውና ዘመቻው ሂደት ሲያደርሱት የነበረው ተፅዕኖም ምን ያህል እንደነበረ የሚታወስ ነው። እናም መረጃን መሠረት ያደረገው የሳይበር ምህዳር የሀገራት ሁለንተናዊ ዕድገት መፍጠሪያ አቅምና ዋነኛ የኃይል መወዳደሪያ መድረክ ብሎም የደህንነታቸው ማስጠበቂያ ዋስትና እየሆነ በመምጣቱ ሀገራችን ኢትዮጵያም ምህዳሩን ደህንነቱ አስተማማኝ በሆነ መንገድና ሁለንተናዊ ኃይል ሊፈጥርላት በሚችል መልኩ ለመጠቀም የጀመረችውን ሥራ አጠናክራ መቀጠል ይጠበቅባታል።

በመሆኑም የሳይበር ግጭት ሉዓላዊነትንም አደጋ ላይ ለመጣል የሚደረግ ሙከራ በመሆኑ የራሳቸውን ጥቅም ለማስፈጸም የሚፈልጉ አካላት ከሚጠቀሟቸው ስልቶች በተጨማሪ በእኛ በኩል ለሳይበር ደህንነት ስጋትና ጥቃት ተጋላጭ እንድንሆን የሚያደርጉን መንስኤዎች መለየትና ተገቢውን የመከላከል እርምጃ መውሰድ እጅጉን አስፈላጊ ተግባር ይሆናል። እነዚህም ለሳይበር ደህንነት የማይመጥን የአስተሳሰብ፣ የአመለካከትና የተግባር ዝግጁነት፣ የሳይበር ተጋላጭነትንና ጥቃትን ለመከላከል የሚያስችሉ ተፈላጊ አሠራሮችንና ስትራቴጅዎችን አለመዘርጋት፣ የደህንነት ንቃተ ሕሊናና ባህል አለመኖር ነው። በዘርፉ የሰለጠነ ብቁ የሰው ኃይል አለማፍራትና የቴክኖሎጂ ጥገኝነት ዋነኞቹ ናቸው። ስለሆነም እንደ ሀገር ብቁ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋትና በአግባቡ በመተግበር፣ የራስን የቴክኖሎጂ አቅም በመገንባትና የሰው ኃይልን በማሟላት ብሎም አስፈላጊውን የሳይበር ንቃተ ህሊና በመገንባት የሳይበር ግጭቶቹ ሊፈጥሩ ከሚፈልጉት ሉዓላዊነትን የመጣስ አጥፊ ድርጊት ራስንና ሀገርን መጠበቅ ይቻላል።